እግዚአብሔር የሚቀናው በጣም ስለሚወደን፣ ጉዳታችን ግድ ስለሚ
ለው ብቻ ነው። የፈለግነውን እንድንመርጥ ሙሉ ነጻነት ሰጥቶናል። ከፊ
ለግን ፍጹም ሕይወት የሌላቸውና ሕይወት ሊሰጡን የማይችሉትን ጣዖ
ታት ለማምለክ ብንመርጥ ምርጫችንን ያከብራል። ጭቃና አሸዋ የሞላበ
ትን የውሃ ጉድጓድ እጆቻችን እስኪደሙ ድረስ፣ ደክሞን እስኪናቆም
ድረስ ለራሳችን መቆፈር ብንመርጥ አይከለክለንም። የፈቀድነውን ግድ
ረግ እንችላለን። ይሁን እንጂ ይህን ስናደርግ ሊረዳን፣ የተጠማውን ሕይ
ወታችንን ሊያረካ ፈልጎ እጁን ዘርግቶ የሚጠብቀንን ጌታ ገፍተነው፣ ረግ
ጠነው፣ በመስቀሉ ላይ ተፍተን መሄዳችን እንደሆነ ግን ማወቅ አለብን።
ሁለተኛው ሕግ፣ "...በማናቸውም ምሰል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ አትስገድ
ላቸውም ሊለን፣ ሕያው የውሃ ምንጭ የሆነውን ጌታን
ትተን፣ ውሃ መያዝ የማይችሉትን ቀዳዳ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች
ለራሳችን እንዳንቆፍር፣ ሊያስጠነቅቀን ነው። ይሆንን ሕግ የሰጠን ሊጠቅ
መን አስቦ እንጂ፣ ሊጎዳን ወይም ደስታችንን ሊቀንስ ፈልጎ አይደለም።

Join our official telegram Channel for more
@AmharicSpritualBooks

ምዕራፍ አምስት

3ኛው ትዕዛዝ

የከበረ ስሙን አክብሩ!

"የአግዚአብሔር የአምላክህን ስም ያለ አግባብ አታንሣ፤
አግዚአብሔር ስሙን ያለአግባብ የሚያነሣውን
በደል አልባ አያደርገውምና።"
(አሪት ዘፀአት 20፥7)

ነፍስ ያለውና ነፍስ የሌለው ፍጡር ሁሉ ተለይቶ የሚታወቅበት የጋ
ራና የራሱ የሆነ የግል መጠሪያ ስም አለው። የተሰጣቸው የግል ስም ማንነ
ታቸውንና ምንነታቸውን ይገልጻል። አንዳንድ ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ስም
ሲጠራ፣ እዕምሯችን ስማቸውን ከድርጊታቸው ወይም ከታሪካቸው ጋር
ያያይዘዋል። ለምሳሌ፥ ሞሐመድ አሊን ከቦክስ ጋር፣ ታይገር ዉድስን
ከጎልፍ ጨዋታ፣ እዶልፍ ሂትለርን ካለቁት ስድስት ሚሊዮን አይሁዳው

ያን ጋር እናያይዘዋለን። የአንዳንድ ታዋቂ ሰዎች ስም ሲጠራ እንዳንድ ጥሩም ሆነ መጥፎ ትዝታዎች ወደ አዕምሯችን ብቅ ማለታቸው አይቀ ርም። ለምሳሌ የማዘር ትሬሳ ስም ሲጠራ ሰው ሊኖረው የሚችለውን ርህ ራሄና ደግነትን እንድናስብ ያደርገናል። ይሁዳ እሰቆሮቱ ጌታውን በሰላሳ ብር የሸጠ ሰው በመሆኑ፣ "ይሁዳ" የሚል ስም ሲጠራ በአዕምሯችን የሚ መላለሰው የሰውን "ከዳተኛነት" ነው። ለዚህ ነው ወላጆች ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ "ይሁዳ" የሚለውን ስም የማያወጡላቸው። እንዲሁም የብዙ ሰዎች መጥፊያ ምክንያት የሆኑት ዓለም ያወቃቸው፣ ታሪካቸውን በሰው ደም እያጠቀሱ የጻፉ፣ ያደፈና የተበላሸ ታሪክ ያላቸው እነሂትለር፣ ሙሶ ሎኒ፣ የፈረንሳዩ ቻርለስ ዘጠነኛው፣ ኢትዮጵያዊው መንግሥቱ ኃይለማር ያም፣ ለማቸውን ከታሪካቸው ጋር ስለምናያይዘው፣ በክፉም ሆነ በደግ ስማቸው ሲጠራ በውስጣችን የተለያየ ስሜት እንደሚሰማን፣ እንዲሁም ሰው ምን ያህል ጨካኝና ርህራሄ የጎደለው ፍጡር የመሆን ዝንባሌ እንዳ ለው እንድናስብ ያደርገናል።

ወላጆች ለልጆቻቸው ስም የማውጣት ሥልጣን አላቸው

ወላጆች ካለባቸው ኃላፊነት ውስጥ አንደኛው ለልጆቻቸው ስም ማው ጣት ሲሆን፣ ለእንዳንዶቹ ቀላል አይደለም። ስምዕራቡ ዓለም የተለያዩ ሰዎችን በዝርዝር የያዘ መጽሐፍ ሰላለ፣ እንዳንድ ወላጆች በቅድሚያ የሚሰማማቸውን ስም ከመጽሐፉ ውስጥ መርጠው ለልጆቻቸው ስም ያወ ጣሉ። ከዚያም ውስጥ መምረጥ ካቃታቸው ከቤተ ሰብ፣ ከዘመድ፣ ከጓደኛ ህሳብ ይጠይቃሉ። ይህን ዓይነቱን ዝግጅት ቀደም ሲል ቢጀምሩም፣ ህጻኑ እስከሚወለድበት ቀን ድረስ ለልጃቸው የሚሰማማቸውን ስም የማያገኙ ወላጆች አሉ። ስማቸውን ካደጉ በኋላ ከለወጡት ጥቂት ሰዎች በስተቀር፣ ብንወደውም ሳንወደውም፣ ሁላችንም የምንጠራበት ስም ከወላጆቻችን የተሰጠን እንጂ፣ ለራሳችን ስም ያወጣን የለንም። ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ላይ ያላቸውን ሥልጣን ወይም መብት የሚገልጹበት እንደኛው የሚጠሩበትን ስም በማውጣት ነው። ሰው በሚሰጠው ስም የማይጠራ ለራሱ ስም የማውጣት ሙሉ ሥልጣን ያለው፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ኃያሉ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሚያሳዝነው አንዳንድ ሰዎች እውነትነት የሌለውን ዓይነት ስም ለእግዚአብሔር ለመስጠት (ለማውጣት)

የሚሞክሩ ሰዎች መኖራቸው ነው። ይሁን እንጂ እውነተኛውን ባህሪው ንና ሕልውናውን የሚገልጽ አይደለም።

አንዳንድ ወላጆች ከልጆቻቸው ማንነትም ሆነ ጠባይ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለውን ዓይነት ስም አውጥተውላቸው መሰማት በጣም የተለመደ ነው። ለምሳሌ በቀላሉ የምትናደድ ሆና "ትዕግሥት"፣ ፉንጋ ሆና "ቆንጂት"፣ ኮሳሳ ሆኖ "አንበሴ"፣ ፈሪ ሆኖ "ጎበዜ" የሚል ስም የተሰጣቸው አሉ። በሕይወታቸው የሚወዱት ወይም የሚያደንቁት ሰው ካለ፣ ያንን ሰው ለማስታወስ ሲሉ ብቻ ለልጃቸው የዚያን ሰው ስም ይሰጡ ታል። በጦርነት ጊዜ የወለዱትን ልጅ፣ "ሰላም" ብለው በመጥራት ምኞታ ቸውን ይገልጻሉ። እንዲሁም በሁከትና ሽብር በሆነበት ዘመን የተወለደ ውን፣ "አሸብር"፣ በመሰከረም ወር የተወለደችውን "መስከረም"፣ በፋሲካ ዕለት የተወለደውን "ፋሲካ" በማለት ስም ማውጣት የተለመደ ነው። ወላ ጆች ልጆቻቸው አድገው ወደ ፊት ምን እንደሚሆኑ ባያውቁም፣ ልጆቻ ቸው እንዲሆኑላቸው የሚፈልጉትን፣ ወይም ምኞታቸውን በሚሰጧቸው ስም የሚገልጹ አሉ። ለምሳሌ፥ ሀብታሙ፣ ግዛቸው፣ ጌታቸው፣ ድፋባ ቸው፣ ሙሉ እመቤት፣ ሙሉ ወርቅ፣ የእኔ ወርቅ በማለት ስም ያወጡላ ቸዋል።

አንዳንድ ወላጆች ደግሞ ትርጉም ያለው ስም ለልጆቻቸው ያወጣሉ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ተስፋ መሠረት ሣራ እንደምትጸንስና ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ስትሰማ፣ ሁኔታው አሰደንቋት ሳቀች። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ተስፋውን ጠብቆ ጸንሳ ወንድ ልጅ ወለደች። "አብርሃም ሣራ የወለደችለትን ልጅ ስሙን ይስሀቅ አለው" (ዘፍ. 21፥3)። "ይስሀቅ" ማለትም "የደስታ ሳቅ" ማለት ነው። ልጅ ሳትወልድ ብዙ ዘመን የጠበቀ ችው ሃናም ልጅ ስትወልድ፣ "...ከእግዚአብሔርን ለምኜዋለሁ ሰትል ሳሙኤል አለችው" (1 ሳሙ. 1፥20)። እንዲሁም የልጃቸው ስም ከአባ ታቸው ስም ጋር አብሮ እንዲሄድ በማለት ብቻ ለልጆቻቸው ስም የሚያ ወጡም አንዳንድ ወላጆች አሉ። ለምሳሌ እኔ ከማውቃቸው አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፣ አታልፍም መንግሥቱ፣ ቤተ መንግሥቱ፣ አታላይ ዓለም የመሳሰሉ ናቸው። ስለዚህ ስማቸው ከእነርሱ ባህሪና ማንነትም ሆነ ምንን ነት ጋር ግንኙነት ስለሌለው፣ ስማቸው ምንም ማለት አይደለም።

በጥንት ዘመን አይሁዳውያን ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ ግን በአሁኑ ዘመን እንዳለው ዝም ብለው ሳይሆን፣ ሰሙ ከሰውየው ማንነትና ባሕሪ

ጋር አብሮ የሚሄድ ነበር። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ስማቸው ከተጠቀሱት ውስጥ ለአንዳንዶች ስም ያወጣላቸው እግዚአብሔር ራሱ ነበር። *"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙም አማኑኤል ተብሎ ይጠራል። አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው"* (ማቴ. 1፥23)። በእንድ ወቅት ባህሪያቸውና ሁኔታቸው ሲለወጥ፣ ስማቸውም ይለወጥ ነበር። ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረው "አብርሃም" መጀመሪያ ይጠራበት የነበረው ስም "አብራም" የሚል ነበር። *"አብራም"* በአንድ ወቅት ላይ *"ከእንግዲህ ወዲያ ስምህ አብራም መባሉ ቀርቶ አብርሃም ይሆናልI የብዙ ሕዝቦች አባት አድርጌሃለሁና"* በማለት ስሙን ለወጠው (ዘፍ. 17፥5)። እንዲሁም እግዚአብሔር አብርሃምን፣ *"ሦራን ከእንግዲህ ሦራ ብለህ አትጠራትምI ሶሪ ከዛሬ ጀምሮ ሣራ ይሁን። እኔ እባር ካታላሁ ከእርሷም ወንድ ልጅ አሰጥሃለሁI የብዙም ሕዝቦች እናት ትሆን ዘንድ እባርካታለሁ የሕዝቦችም ነገሥታት ከእርሷ ይወጣሉ"* (ዘፍ. 17፥16) አለው። ኢየሱስም የስምዖንን ስም ሲለውጥ *"አንተ ጴጥሮስ ነህI በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ..."* አለ (ማቴ. 16፥18)። "ወላዋይ፣ አስተማማኝ ያልነበርከውን ለውጬ ጽኑ፣ ጠንካራና አቋም ያለው ሰው እደርግሃለሁ" ማለቱ ነበር።

ሰው ለእግዚአብሔር ስም የማውጣት ሥልጣን የለውም

መጠሪያ ስም ያለው ሰው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም የሚጠራበት ስም አለው። ከሰው የሚለይበት ነገር፣ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ስም የሚያወጣው፣ ማንነቱንም የሚገልጸው ሰው ሳይሆን እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ማንነቱንም ሆነ ስሙን እርሱ ይገልጽልናል እንጂ እኛ "ስምህ እከሌ ይሆናል" ብለን ስም የማውጣት መብትም ሆነ ሥልጣን የለንም። በዚህም እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ላይ ሥልጣንና ኃያል እንዳለው እንረዳለን። ስሙም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ነው። እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት እንዲያወጣ ሙሴን ወደ ፈርዖን ሊልከው ሲጠራው፣ *"ሙሴም እግዚአብሔር ወደ እስራኤል ልጆች ሄጄ 'የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል' ስላቸው 'ስሙ ማን ነው?' ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላቸዋለሁ? እግዚአብሔርም ሙሴን 'እኔ ያለሁና የምኖር ነኝI ስለዚህም 'ያለና የሚኖር' ልኮኛል ብለህ ንገራቸው አለው"* (ዘፀ. 3፥13-14)። ለዚህ ነው "የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ያለ አግባብ አታንሣI እግዚአብሔር

ስሙን ያለአግባብ የሚያነሣውን በደል አልባ አያደርገውምና" የሚል ጥብቅ ትዕዛዝ የሰጠው። ስሙም በአብራይስጥ ቋንቋ "<u>ይሆቫ</u>" ነው። ጥንት አይሁዶች የእግዚአብሔርን ስም በሚጠሩበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ ጻፎች የእግዚአብሔርን ቃል ሲጽፉ፣ "<u>*ያህዌህ*</u> የሚለውን ቃል መጻፍ ከመጀመራቸው በፊት አንዳንድ የሚጠቡቋቸው ደንቦችና ሥርዓቶች ነበሩ። ይኸውም፣ መጀመሪያ ሰውነታቸውን ይታጠባሉI የክህነት ልብሳቸውን ይለብሳሉI ስሙን ጽፈው ሳይጨርሱ መካከል ላይ ቀለሙ አልቆ ሳይጨርሱት እንዳይቀር፣ በቅድሚያ ብልቃጡ ውስጥ በቂ ቀለም መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው። "ያህዌህ" የሚለውን የእግዚአብሔርን ስም በሚጽፉበት ወቅት፣ ሌላው ቀርቶ ንጉሥ እንኳን ቢመጣ እጅር ጠው መነሳት አይፈቀድላቸውም ነበር። ስሞቹ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕሪ የሚገልጹ ናቸው።

የእግዚአብሔር ስም፣ እንደ ሰው ስም ከባሕሪው ጋር ምን ግንኙነት እደሌለው ሳይሆን ባሕሪውን፣ ኃያልነቱን የሚገልጽ ወይም የሚያሳይ ነው። ዳዊት የእግዚአብሔር ስም ያለውን ታላቅነት ሲገልጽ፣ *"እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ! ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ ግርማዊ ነው! ክብርህ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ ብሎአል"* ይላል (መዝ. 8፥1)። እንዲሁም መዝ. 111፥9 ላይ *"...ስሙም የተቀደሰና የተፈራ ነው"* ይላል። ዳዊት የሚያደንቀውና የሚያመሰግነው ስሙን ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በኃይሉ ሁሉን ነገር ለክብሩ የፈጠረ መሆኑን በመግለጽ ነው። በመፍጠርም ሆነ በመቤገርት ሥራው፣ እግዚአብሔር ለራሱ ስም አበጅቷል። ስዎችን ያዳነው ለክብሩ ነው። ዘማሪው *"እርሱ ግን የኃይሉን ታላቅነት ለማሳወቅ ስለ ስሙ አዳናቸው፣ ቀይ ባሕርን ገሠጸI እርሱም ደረቀI በምድረ በዳ እንደ ሚታለፍ በጥልቅ ውሃ መካከል መራቸው"* ይላል (መዝ. 106፥8-9)።

እግዚአብሔርን በስሙ እንድንጠራው ነጻነትን የሰጠን፣ ከእርሱ ጋር በጣም ቅርብ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረን ስለ ፈቀደ ነው። በስሙ ስንጠራው ሰዎቶ መልስ እንደሚሰጠን ተስፋ ገብቶልናል። ይሄም ትልቅ ዕድል ነው። ስናመልከውም ስሙን እንድንጠራ ይፈቅድልናል። *"ለእግዚአብሔር ዘምሩI ስሙንም ባርኩI ማዳኑንም ንጋ ጠባ አውሩ"* ይላል (መዝ. 96፥2)። እንዲሁም መዝ. 100፥2 ላይ *"በምሲጋና ወደ ደጆቹ፣ በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡI አመስግኑት፣ ስሙንም ባርኩ"* ይላል። እንዲሁም አዲስ ኪዳን ላይ "ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል

በዚያ እሾለሁና" ይላል (የማቴ. 18፥20)። ይሁን እንጂ፣ ብዙዎች ያሰሉ ግባብ በስሙ ሲጠቀሙ ይታያሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ስዎች የተናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማሳመን የእግዚአብሔርን ስም ይጠሩ ነበር። ዋንኩ በእገራችን ሰዎች የተናገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለመግለጥ "ኃይለ ሥላሴ ይሙት" ብለው ይምሉ ነበር። ለማለት ያህል ብቻ ይቀበሉ እንጂ፥ ብዙዎች ብዙ ጊዜ እውነት አለመሆኑን እያወቁ "ኃይለ ሥላሴ ይሙት" የሚሉበት ጊዜ ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን "እንድ ሰው አህያ፣ በሬ፣ በግ ወይም ማናቸውንም እንስሳ በጎረቤቱ ዘንድ በአደራ አስቀምጠ ሳለ እንስሳው ቢሞት፣ ወይም ጉዳት ቢደርስበት፣ ወይም በው ሳያይ ተነድቶ ቢወሰድ፣ በሁለቱ መካከል ያለው አለመግባባት መፍታሄ የሚያገኘው፣ ጎረቤቱ የሌላውን ሰው ንብረት እንዳልወሰደ በእግዚአብሔር ፊት በመማል ነው። ባለቤቱም ይህን መቀበል አለበት..." ይላል (ዘፀ. 22፥10-11)። በተጨማሪ "ብሶሜ በሐሰት አትማሉ፣ በዚህም የአምላካችሁን ስም አታርክሱ፣ እኔ እግዚአብሔር እምላካችሁ ነኝ" በማለት ጥብቅ የሆነ ትዕዛዝ ሰጥቷል (ዘሌዋ. 19፥12)። ይህን ትዕዛዝ ችላ ብለው በሐሰት የሚምሉ ቢኖሩ በሞት እንዲቀጡ ያዛል።

የእግዚአብሔር ስም ኃይል አለው

የእግዚአብሔር ስም ኃይል አለው። ይህን እውነት የተረዳው ዳዊት በጎልያድ ፊት ይዞ የቀረበው ወንጭፍና ድንጋይ ብቻ አልነበረም። ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን አስደናቂና ኃይል ያለውን ስም ይዞ እንደሆነ እናውቃለን። "አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ መጥተህብኛልI እኔ ደግሞ አንተ በምትገዳደረውና የእስራኤል ሠራዊት አምላክ በሆነው ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" አለው (1 ሳሙ. 17፥45)። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ስም ከኃይል ጋር ያያይዘዋል። እግዚአብሔር ሌሎ ዝቡ ማንነቱን ይገልጽ የነበረው በስሙ ልዩ ኃይል እንዲጠቀሙ በመፍቀድ ነበር። ስሙ ኃይል አለውI አጋንንት የክርስቶስ ስም ሲጠራ ይንቀጠቀጣሉI የያዙትን ሰው ለቅቀው ይወጣሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ "ለኢየሱስ ስም ክብርI በሰማይና በምድርI ከምድር በታች ያሉ ሁሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ" ይላል (ፊል. 2፥10)። በስሙ በሽተኞች ይፈወሳሉ። ጴጥሮስ በዚህ ስም ተጠቅሞ ሲወለድ ጀምሮ ሽባ የበረውን ሰው እንደ ፈወሰው

መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ወርቅና ብር የለኝምI ያለኝን ግን እሰጥሃለሁI በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥና ተራመድ" አለው (የሐዋ. 3፥6)። በስሙ ደህንነት አለ። "መዳን በሌላ በማንም የለምI እንድንድንበት ዘንድ የሚገባ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" ይላል (የሐዋ. 4፥12)። በሐዋርያት ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች፣ በኢየሱስ ስም የተደረገውን ታምራት ካዩና ከሰሙ በኋላ፣ በኢየሱስ ስም ምንም ነገር እንዳያደርጉ ሐዋርያትን ያስጠነቅቋቸው እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። በስሙ በመጠቀም ታላቅ ነገር መቀበል እንደሚቻል መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ ተጠቅሶ እናነባለን። "እውነት እውነት እላችኋለሁ አብን በስሜ ብትለምኑት ሁሉን ነገር ይሰጣችኋል" (ዮሐ. 16፥28) ይላል። እንዲሁም "አብ በወልድ ምክንያት እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርግላችኋለሁ። ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ" ይላል። እንዲሁም "አስኩን በስሜ ምንም ነገር አልለመናችሁምI ለምኑ ትቀበላላችሁI ደስታችሁም ፍጹም ይሆናል" ይላል (የዮሐ. ወንጌል 16፥24)።

ይህን የመሰለውን አስደናቂ ስም ያለአግባብ ለናነሳ እግዚአብሔርን ያስቆጣዋል። የሰውን ስም የሚያጠፉ፣ ያለስሙ ስም የሚሰጡ፣ የሰው ስም እንደ ማስቲካ የሚያኝኩ፣ ሌላውን ሰው እንደ ሞራቅ አድርገው የሚስሉ፣ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ተንኮለኞች ናቸው። ሮጠው መቅደም ሲያቅታቸው የሰው ስም በማጥፋት ጠልፈው ለመጣል የሚሞክሩ አሉ። ሰው የሌላውን ሰው ስም ቢያጠፉ፣ ቢያበላሽ ማምለጥ ይችል ይሆናል። የእግዚአብሔርን ስም ግን አጉድፎ ከእግዚአብሔር ማምለጥ የሚችል ማን ይኖራል? እግዚአብሔር ያልሆነውን እንደሆነ፣ ከባሕሪው ጋር ፈጽሞ የማይሄደውን ስም የሚያወጡ፣ እግዚአብሔርን ክፉ፣ ጨካኝ አድርገው የሚስሉት ወይም የሚያቀርቡት ክርስቲያኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዶች ስሙን እንደ አስማት አድርገው ለመጠቀም ሲሞክሩ ይታያሉ። ሰሙ ኃይል የሚኖረው፣ ዝም ብለን ሰሙን በመጥራት ብቻ ሳይሆን፣ በእምነት፣ በፍቅር፣ በመተማመን ስንጠቀምበት ነው። የእግዚአብሔርን ስም አንዳንዶች እንደ ቆሎ ጓደኞቸው አድርገው ሲጠቀሙበት መስማት እጅግ ያሳዝናል። ስሙን ለንጠቀም በእክብሮት፣ በፍርሃት እንዲሁም በመንቀጥቀጥ መሆን አለበት። በእግዚአብሔር ስም የሚነግዱ፣ የሚሸቃቅጡ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሞልተዋል። የእግዚአብሔርን ስም ለንጠራ ልናተርፍበት፣ ልንነ

ግድበት ሳይሆን፣ ልናከብረው መሆን አለበት። እንዲሁም እግዚአብሔር የሌለውን ስም እንዳንስጠው፣ ስሙን በከንቱ እንዳናነሳ አስፈላጊውን ጥን ቃቄ ማድረግ አለብን።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ማንሳት ዋጋ ያስከፍላል

"የእኔን የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ፤ ምክንያቱም እኔ ስሜን በከ ንቱ የሚያነሳውን ሁሉ አቀጣዋለሁ" በማለት ሕግ እስከማውጣት ደረጃ ድረስ የደረሰበት ምክንያት ምንድነው? ብለን መጠየቃችን እይቀርም። የምንኖረው ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም መቀለጃና መጫወቻ በሚያደር ጉበት ዘመን ውስጥ ነው። ቅዱስ የሆነውን ስሙን በከንቱ ሲጠሩ፣ ቅዱስ የሆነውን እግዝአብሔርን መዋጋታቸው እንደሆነ የተረዱት እይመስሉም። "የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ማንሳት" ምን ማለት ነው? ቅድስናውን፣ ኃያልነቱን፣ አምላክነቱን መካድ ነው። የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ ማንሳት፣ ኃያሉን እግዚአብሔርን የሰው እኳያ ወይም ዝቅ አድርጎ ማየት ነው። ከጌታ ውጪ የሆኑ ሰዎች ታላቁን እግዚአብሔር ዝቅ በማድረግ፣ ከእነርሱ በላይ ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ አድርገው ማየትና ማሳየት ይፈልጋሉ።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚያነሱ፣ ኃያል፣ ቅዱስ ተብሎ የሚ ጠራውና የሚገመተውን እግዚአብሔር፣ ከእኔ የሚበልጥ እይደለም" በማለት የራሳቸውን ትልቅነት ማሳየታቸው ነው። በአሁኑ ጊዜ በተለይ በአሜሪካ ሕብረተሰብ ውስጥ በያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የእግዚአብ ሔርን ስም የሚያነድፍ ቃል ሲወረውሩ መስማት አዲስ ነገር አይደለም። ይህ ሲሆን እግዚአብሔር ግድ የለውም ማለት ይሆን? ግድ ስላለው ነው ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ አንደኛው እንዲሆን ያደረገው። እኔና እናንተ ስማችንን ሰዎች ያለአግባብ ቢያነሱ፣ በስማችን ቢቀልዱ፣ የሌለንን ዓይ ነት ስም ቢሰጡን የሚያስቆጣን ከሆነ፣ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔርማ በስሙ በሚቀልዱት ሰዎች ምን ያህል ይቆጣ ይሆን? በወቅቱ በእግዚአብ ሔር ስም ሲቀልዱ ምንም አይድረስባቸው እንጂ፣ እንድ ቀን ግን ብድራ ታቸውን የሚያገኙ፣ የዘሩትን የሚለቅሙ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "በእውነት እሳችኋለሁ፤ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌ ለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጠባታል። ምክንያቱም ከቃ

ልህ የተሥሣ ይፈረድልሃልኣ ከቃልህም የተሥሣ ይፈረድብሃል" ይላል (የማቴ. 12፣36-37)።

እግዚአብሔር "የእኔን የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ፤ ምክንያ ቱም እኔ ስሜን በከንቱ የሚያነሳውን ሁሉ አቀጣዋለሁ" ይሰናል። ይህንን ሦስተኛውን ትዕዛዝ የሰጠን፣ ስለሚወደን ከቅጣት ነጻ እንድንሆን የሰጠን ማስጠንቀቂያ ነው። "ስሜ ከብር የማይገባው ተራ ስም፣ ወይም መቀለጃ አይ ደለም። ነገር ግን ስሜ ታላቅ የሆነ፣ ክብር የሚገባኝ አምላክ ነኝ" ይለናል እንጂ፣ የፈለጋችሁን ዓይነት ስም ብትሰጡኝ ምንም አይደለም እይለንም። እንዲያውም ስሙን ያለአግባብ ወይም በከንቱ የሚያነሳ ሁሉ ተገቢው ቅጣት ይደርስበታል። ይህን የሚያውቀው ጌታ በጣም ስለሚወ ደን፣ ስሙን በከንቱ አንስተን እንድንቀጣ አይፈልግም። እኛም ልጆቻ ችንን ስለምንወዳቸው የሚጎዳቸውን ነገር እንዳያደርጉ ደጋግመን ማስጠ ንቀቂያ እንሰጣቸዋለን። እግዚአብሔርም ልክ እንደዚሁ ነው። የእግዚእ ብሔርን ስም በከንቱ ማንሳት፣ የረከሰና የተበላሸ ቃላት በመጥቀስ ብቻ አይደለም። ብዙዎቻችን ቡተለይ ኢትዮጵያውያን የዚህ ችግር የለብንም። ያለብን ችግር በማያስፈልገው ነገር ሁሉ ላይ የእግዚአብሔርን ስም መጨ መራችን ነው። በእጃችን የያዝነው ዕቃ ሲወድቅብን፣ "ኢየሱስ!..." መስ ማት የማንፈልገውን ነገር ስንሰማ፣ ስንናደድ "...በየሱስ ስም..." ማለት እንደ ልማድ ይዘነዋል። ከዚህ ሁሉ የከፋውና አሳዛኝ የሆነው፣ "እግዚአብ ሔር ነገረኝ..." የሚለው ቋንቋችን ነው። ደስ ያለችውን ሴት፣ "በጣም ስለ ወደድኩሽ ላገባሽ እፈልጋለሁ" በማለት ፈንታ "ሚሱቴ እንድትሆኚ እግዚ አብሔር ነገረኝ..." ይላል።

ስምና ዝና እንደ ውሃ የተጠሙ፣ ራሳቸውን ቅዱስና መልአክ እድር ገው ለማሳየት የሚሞክሩ እንዳንድ ራሳቸውን "እገሊጋይ" ብለው የሚጠሩ ሰዎች፣ "እግዚአብሔር ነገረኝ" የሚለውን ቋንቋ ከመጠን በላይ ሲጠቀሙ በት መስማት በእሁኑ ጊዜ የተለመደ ሆኗል። የሚጠሉትን፣ የሚቀኑበትን፣ ክፉ ነገር እንዲደርስበት የሚመኙሰትን ሰው፣ "...ጌታ ይህን እሳየኝ፤ ዘንዶ ሲውጥህ... እባብ ሲነድፍ፣... ልብህ በቁጣና በመራራነት ተሞልቶ ልብህ ጥላሸት ሆኖ አሳየኝ... በጨለማ ውስጥ ብቻህን ሱትሄድ አሳየኝ..." ይሉታል። አዕምሮውን የሚጠቀም ከሆነ፣ "የእኔን ጉድ ለእንተ ከሚያሳ ይህ ለምን ለእኔ አያሳየኝም?... እግዚአብሔር እኔን ይፈራኛል እንዴ? ወይስ እግዚአብሔር ያሳብቃል እንዴ?" በማለት ፊት ለፊት መልስ ይሰጠ

ዋል። ተናጋሪውን ላለማሳፈረ ከፈለገ ደግሞ ታዝበት ያልፋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ አንድ እርሱ የሚፈልገውን ነገር ያለው የመሰለውን ሰው ደግሞ፣ ቤቱ ድረስ ሄዶ፣ "ጌታ ለእንተ መልዕክት ሰጥቶኝ ልነግረህ ነው የመጣሁት... ሻንጣህን ይዘህ ወደ ሩቅ አገር ሰትሄድ ትታየኛለህ... አሜሪካ በቅርቡ እንደምትሄድ ጌታ ነገረኝ..." ይሉታል። ያ ሰው አሜሪካ የመሄድ ጥማት ያለው ከሆነ፣ "ጌታ ትሄዳለህ... ብሎ ነግሮኛልና በሽበቱም እጠብ ቀዋለሁ" በማለት ባለው ኑሮ ደስ ብሎት እንዳይኖር ልቡ ለረጅም ጊዜ እንደተንጠለጠለ ይቆያል። እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ በእግዚአብሔር ስም የሚቀልዱ፣ በእግዚአብሔር ስም የሚነግዱ አይደሉም? ታዲያ እነዚህን እንከርዳዶችን እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላቸዋል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ኢየሱስ "ተዋቸው አብረው ይደጉ..." በመጨረሻው ቀን ግን ተለይተው ወደ እሳት እንደሚጣሉ ተናግሯል።

በኤርምያስ ዘመን እንደነበረው በአሁኑ ዘመንም "እግዚአብሔር ያላለውን እንዲህ ይላል" በማለት በስሙ ለመጠቀም የሚሞክሩ ሰዎች የሞሉበት ዘመን ነው። *"እግዚአብሔር እንዲህ ሲል መለስI ነብያቱ በእኔ ስም ሐሰት ይናገራሉI እኔ አልላክሁአቸውምI ትእዛዝም አልሰጠኋቸውም አንድ ቃል እንኳ አልነገርሁአቸውምI እየን የሚሉት ራእይ ሁሉ ከእኔ የተገኘ አይደለምI ትንቢታቸው ሁሉ ከአሳባቸው ያፈለቁት ከንቱ ነገር ነው። እኔ ሳልልካቸው በምድራችን ላይ ረሀብም ሆነ ጦርነት አይመጣም እያሉ በስሜ ትንቢት የሚናገሩትን እነዚህን ነቢያት እኔ እግዚአብሔር ምን እንደ ማደርግባቸው ልንገርሀI ይኸውም በጦርነትና በረሀብ እንዲሞቱ አደርጋለሁ። ይሆንንም የተነበዩላቸው ሕዝብ ሁሉ በረሀብና በጦርነት ይሞታሉI ራሳቸውም ሁሉ በኢየሩሳሌም ውስጥ በየመንገዱ ይወድቃልI የሚቀብራቸውም አይኖርም..."* (ኤር. 14፥14-16)። ክርስቶስ "በስሜ የለመናችሁትን ሁሉ አብ ይሰጣችኋል" ሲለን፣ በስሙ እንድንጠቀም ነጻነት ሲሰጠን ወይም ሲያደፋፍረን ነው። ይሁን እንጂ፣ እውነትነት በሌለው ነገር ስሙን እንድንጠቀምበት አይፈቅድልንም።

በእኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም ይሰደብ ይሆን?

አማኞች የእግዚአብሔርን ስም የምናሰድብበት እንደኛው መንገድ፣ በአማኝነታችን ታውቀን፣ ኑሯችን ወይም ሕይወታችን "ነን" ከምንለው

ጋር አብሮ የማይሄድ ሲሆን ነው። በዕለት ሥራችን ከዓለማውያን ጋር ተስልፈን ስንሠራ፣ ሕይወታችንን በየቀኑ የማየት ዕድል አላቸው። ክርስትናችን በዕለት ሥራችን ይታያል? ወይስ ክርስቲያኖች የምንሆነው ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ብቻ ነው? ጳውሎስ "...በእናንተ ምክንያት የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል..." ይላል (ሮሜ 2፥24)። የእግዚአብሔር ስም ለምን እንደሚሰደብ መክንያቱ ሲገልጽ፣ *"እንግዲህ አንተ ሌሎችን የምታስተምር፣ ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ፣ ትሰርቃለህን? አንተ ሰዎች ማመንዘር የለባቸውም የምትል ታመነዝራለህን? አንተ ጣዖትን የምትጸየፍ፣ ቤተ መቅደስን ትመዘብራለህን? አንተ በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታዋርዳለህን?"* ይላል (ሮሜ 2፥21-23)። ከመንግሥቱ ውጪ የሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ልጆች የሚያዩዋቸው፣ እግዚአብሔርን በሚያዩበት ዓይን ነው። ትክክል ባይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሕግ እውነተኛነትና ትክክለኛነት የሚያዩትና የሚለኩት አማኞች በሚያሳዩት፣ ባሳቸው ጽኑ የሕይወት አቋም (ኢንቴግሪቲ) ነው። መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደሚገባው የክርስቶስን ውበት ወይም መልክ የማያንጸባርቅ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ስም በእነርሱ ምክንያት ይሰደባል።

ክርስትናችን በዕለታዊ ሕይወታችን ክርስቶስ በትክክል የማይታይ ከሆነ፣ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን መዋሸታችን ስለሆነ፣ በእኛ ምክንያት የእምላካችን ስም ያለ አግባብ እንዲነሳ ምክንያት መሆናችን ነው። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር ስም ያለአግባብ እንዲነሳ ምክንያቶች ከሆንን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ሦስተኛውን ሕግ መጣሳችን ስለሚሆን፣ በደለኞች መሆናችን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ከላይ በገለጽነው ዓይነት መሥመራችንን እንዳንስት ያስጠነቅቀናል። የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚያነሱትን ሲገልጻቸው፣ *"እግዚአብሔርን እናውቃለን ይላሉI ዳሩ ግን በተግባራቸው ይክዱታልI አስጸያፊዎች፣ የማይታዘዙና ለበጎ ሥራ የማይበቁ ናቸው"* ይላል (ቲቶ 1፥16)። ብዙዎች ሦስተኛውን ትዕዛዝ ችላ በማለት ሰይጣንን ደስ ሲያሰኙት፣ እግዚአብሔርን ግን ሲያሳዝኑት እናያለን። አንዳንዶች "መልካም የሆነ ሕይወት አለኝI ጠጥቼ አልሰከርምI የሰውን ገንዘብ አልሰርቅምI ዝሙት አልፈጽምምI አልፎ አልፎ ግን የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት አምላለሁI ታዲያ ይሄ ምናለበት" የሚሉ አሉ። የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራታቸው ይሆን ያህል ከባድ ኃጢአት

የክርስቶስ መከራ የማይለያቸው እንዳሉ የታወቀ ነው። ክርስቲያን ሁልጊዜ በንግግሩ ንጽሁ መሆን እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ይናገራል። ክርስቲያን መሆናችንን፣ ቤተ ክርስቲያን መሄዳችንን የሚያውቁ ሰዎች፣ ከአፋችን የሚወጣውን ክፉ ወይም ከንቱ ንግግር ሲሰሙ፣ በእኛ ምክንያት ወደ እምነት ለመምጣት ወይም ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል ፈቃደኞች አይሆኑም። ያ ብቻ ባይሆን "የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ያለ አግባብ አታንሣ፤ እግዚአብሔር ስሙን ያለአግባብ የሚያነሣውን በደል አልባ አያደርገውምና" የሚለውን ሦስተኛውን ሕግ መጣሳችን ይሆናል።

ሦስተኛው ሕግ፣ የእግዚአብሔር የአምላካችንን ስም ያለ አግባብ" አንዳናነሳ የሚከከል ነው። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ፈጽሞ አንዳይጠሩ ወይም እንዳያነሱ የተከለከለ ነው ማለት አይደለም። ጥንት አይሁዳውያን ምናልባት "ያለአግባብ የእግዚአብሔርን ስም አናነሳ ይሆናል" በሚል ፍርሃት የእግዚአብሔርን ስም ጨርሶ ላለመጥራት ሙከራ ያደርጉ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ስሙን እንድን ጠራ ሙሉ ነጻነት ሰጥቶናል። የሥነ መለኮት ሊቃውንት እንደገለጹት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ከሰባት ሺ ጊዜ በላይ አንደ ተጠቀሰ ይገልጻሉ። ስሙን እንድናውቀው ብቻ ሳይሆን፣ ስሰሙ እንድን ጠራው ሙሉ ነጻነትም ሰጥቶናል። ስሙን እንድናውቀው የሆነው በነጻነት ስሙን እንድንጠራ፣ ከእርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖረን ነው። እግዚአብሔር የማይፈቅድልን ስሙን ያለአግባብ እንዳናነሳው ነው። የእግዚአብሔር ስም ኃያልና ቅዱስ ስለሆነ፣ ስሙን ዝቅ አድርገን እንድናነሳው አይፈቅድም። የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ ማንሳት፣ ቅዱስ የሆነውን ስሙን ማራከስ ይሆናል። በብሉይ ኪዳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚያነሱበት የተለያዩ መንገዶች ነበሯቸው።

ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚያነሱት እንዴት ነው?

(1) ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚጠቀሙበት አንደኛው መንገድ፥ የእግዚአብሔርን ስም አሰማትን በሚለማመዱበት ዓይነት ሊጠቀሙበት መሞከር ነው። ሰዋንቱ ዓለም መለኮታዊ ከሆነ ኃይል ጋር ለመገናኘት የአስማት ድግምትን ይደግማሉ። ታመው አንደ

ሆነ፣ እንዲፈውሏቸው የአማልክቶቻቸውን ስም ይጠራሉ። ስለ ወደፊቱ ሕይወታቸው እንዲነግሯቸው፣ ወደ ጦርነት የሚሄዱ ከሆነ ድልን እንዲሰጧቸው የአማልክቶቻቸውን ስም ይጠራሉ። ግብጻውያን በዚህ ዓይነት ሙያ የታወቁ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን በዚህ ዓይነት መልክ ሰዎች እርሱን በማባበል የራሳቸውን ፍልጎት ለማስፈጸም እንደ መሣሪያ አድርገው እንዲጠቀሙበት አይፈልግም። ሰዎች ስሙን እንደ አስማት እንዲጠቀሙበት አይፈልግም። *"ብመክልህ ወንድ ወይም ሴት ልጄን በእሳት የሚሠዋ ሟርተኛ፣ ወይም በድግምት የሚጠቁልና መናፍስት ጠሪ ወይም ሙት አነጋጋሪ በመካከልህ ከቶ አይገኝ። እነዚህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነውና፣ ከእነዚህ አጸያፊ ልምዶች የተነሣም አምላክህ እግዚአብሔር እነዚያን አሕዛብ ከፊትህ ያባርራቸዋል። በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ነውር አልባ ሁን"* ይላል (ዘዳ. 18፥10-13)።

ዛሬስ ስዘመናችን የእግዚአብሔርን ስም እንደ አስማት ለመጠቀም የሚሞክሩ ይኖሩ ይሆን? ካሉስ የሚጠቀሙበት በምን ዓይነት ሁኔታ ይሆን? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተሰጠው ስቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ ዓላማውም ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት ሲሆን፣ አንዳንዶች ግን "ጌታ ነገረን፣ እንዲህ ትሆናለህ፣ እንዲህ ሊሆንልህ ነው፣ እዚህ አገር ትሄዳለህ..." በማለት በየቤቱ እየዞሩ እንደ ጥንቆላ የሚናገሩ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ እንዳሉ የታወቀ ነው። የአንድ ሰው አሜሪካ መሄድ ከቤተ ክርስቲያን መታነጽ ጋር ምን ግንኙነት አለው? እንዲህ ተብለውና እንደ አጋጣሚ አሜሪካ የሄዱና ሕይወታቸው የተበላሸባቸው፣ ከጌታ የሸሹ አማኞች ቤታቸው ይቁጠረው። ዛሬ የመገለጥ ስጦታ አለን እያሉ በየቤቱ እየዞሩ የሚሰሉ፣ ሰዎች ጌታን ከልባቸው እንዲያመልኩ በማድረግ ፈንታ፣ ምድራዊ ነገርን በመፈለግ ከጌታ የራቁ ጥቂቶች አይደሉም። እግዚአብሔር ባያባያቸው፣ "እግዚአብሔር አሳየን..." እግዚአብሔር ሳይነግራቸው "እግዚአብሔር ነገረን..." በማለት የእግዚአብሔርን ስም ርካሽ የሚያደርጉ፣ እግዚአብሔርን እንደ ቆሎ ጓደኛቸው የሚያደርጉት ሥሌዎች የበዙበት ዘመን ነው። እግዚአብሔር የንስህ ጊዜ ሊሰጣቸው መታገሱ እንጂ፣ እንደነዚህ ዓይነቶቹን በስሙ የሚነግዱትን አይፈርድባቸውም ማለት አይደለም።

(2) ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚጠቀመው ሁለተኛው መንገድ፣ ሀለተኛ ትንቢት በመናገር ነው። "ነብይ ነኝ" ወይም "የትን ቢት ስጠታ አለኝ" የሚለው ሰው ሁልጊዜ ትንቢቱን የሚጀመረው፣ "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ብሎ እንደሆነ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ሳይል "ብሏል" ማለት "ውሸት" ወይም "ቅጥፈት" ነው። እግዚአብሔር ስሙ በውሸት እንዲጠራ አይፈልግም። ነብዩ በእግዚአብሔር ስም የውሸት ትንቢት እንዲተነብይ አይፈልግም። እግዚአብሔርን ያስቀይመዋል እንጂ አያስደስተውም። እግዚአብሔር ሳይልካቸው "እግዚአብሔር ልኮኛል"፣ ሳይነግራቸው "እግዚአብሔር ነግሮኛል..." ሳያሰያቸው "እግዚአብሔር አሰይቶኛል ስለሚሉት ሀሰተ ኞች ነብያት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶ እናነባለን።

ሀለተኛ ትንቢት፣ "የትንቢት ስጦታ አለኝ" የሚለው ሰው የራሱን አጀ ንዳ ወይም ፍላጎት ለመፈጸም፣ የእግዚአብሔርን ስም በውሸት የሚ ጠቀምበት መንገድ ነው። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ስንመረምር፣ በዘመናት ሁሉ ብዙ ሀሰተኞች ነብያት መጥተው አልፈዋል። በእኛም ዘመን ብዙዎች አሉ። ሕዝቡ መሰማት የሚፈልገውን እያሸተቱ፣ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" በማለት የእግዚአብሔርን ስም ያለአግ ባብ ወይም በውሸት የሚጠቀሙ አሉ። የእግዚአብሔር ቅርብ ወዳ ጆች በመምሰል ዝና ለማትረፍ፣ ተቀባይነትን ለማግኘት፣ በእግዚአብ ሔር ስም ምድራዊ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ እግዚአብሔር ያላለ ውን አለ በማለት የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚያነሱ በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች አሉ። ይሁን እንጂ፣ በሀሰት የሚተነብዩትም ሆነ የሚተ ነበይላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ በማንሳት ሦስተ ኛውን ሕግ መጣሳቸውን የተገነዘቡት አይመስልም። በቤተ ክርስቲ ያንም ውስጥ ሆነ፣ በየጓዳው የምንሰማቸው የሀሰት ትንቢቶች፣ በክር ስቲያኖች መካከል የሚታየው የሞራል ድክመት ምን ያህል አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ያሳየናል።

(3) ለዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚጠቀሙበት ሦስተኛው መንገድ፣ በሀሰት መማል ነው። የተናገሩት ወይም ያቀረቡት መረጃ እውነተኛ መሆኑን ለማሰመን፣ በፍርድ ቤትም ሆነ ከፍርድ ቤት ውጪ የሚምሉ አሉ። በኤርምያስ ዘመን እውነተኛ የሆኑ ሰዎች የጠ ቀቡበት ዘመን መሆኑን ኤርምያስ ሲገልጽ፣ "ሕያው እግዚአብሔርን

ቢሉም፣ የሚምሉት በሀሰት ነው" ይላል (ኤር. 5፥2)። የተናገሩት ነገር እውነት ነው ስለማለት የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ መማል በጥንትም ዘመን የተለመደ ነበር። የእግዚአብሔርን ስም ጠርተው ሲምሉ፣ እው ነት ለመናገራቸው እግዚአብሔር ምስክር ይሁን ማለታቸው ነው። የሚያሳዝነው የእግዚአብሔርን ስም መጥራታቸው ብቻ ሳይሆን፣ "እውነት ነው" ያሉት ነገር እውነተኛነት የሌለው መሆኑ ነው። ይሄም ሦስተኛውን ሕግ "የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሳ" የሚለውን መጣ ሳቸው ነው። በዚህ ዓይነት ስዎች ስተው እንዳይገኙ፣ እግዚአብሔር *"ስሜ በሐሰት አትማሉ፤ በዚህም የአምላካችሁን ስም አታርክሱ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ"* በማለት ያስጠነቅቃል (ዘሌ. 19፥12)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ለዎች የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚያነሱት ከላይ በገለጽናቸው ሦስት ዓይነት መንገዶች ነበር። በሦስቱም ዓይነት ለዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ የሚያነሱበት ዋናው ምክንያት የእግዚአብሔርን ስም ለማክበር ሳይሆን፣ ራሳቸውን ለመጥቀም ሲሉ ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር "የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ አታ ንሱ" የሚለውን ትዕዛዝ የሰጠን። "ያለአግባብ አታንሱ" ብቻ ሳይሆን፣ "...ያለአግባብ የሚያነሣውን በደል አልቦ..." የማያደርገው መሆኑን ይገል ጻል። ሦስተኛውን ሕግ የሚለብር፣ ወይም ያለአግባብ የእግዚአብሔርን ስም የሚያነሳ ከበደል ንጹህ አይደለም ይበል እንጂ፣ ምን ዓይነት ቅጣት መቀጣት እንዳለበት ግን በዝርዝር አይገልጽም። የኢየሱስን ስም ያለአ ግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን አደጋ ለመገንዘብ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ታሪካቸው ስለተጻፈው በሰባት ወንድማማቾ ላይ የደረሰውን አደጋ ማስታወስ ይጠቅማል። ጳውሎስ በኤፌሶን አገልግሎቱ ብዙ አስደናቂ ነገ ሮች በክርስቶስ ስም ያደርግ ነበር። ብዙ በሽተኞች ይፈወሱ ነበር። በአጋ ንንት የተያዙትም ነጻ ይወጡ ነበር። *"እግዚአብሔር በጳውሎስ እጅ እጅግ የሚያስደንቅ ታምራትን ያደርግ ነበር። መሐረብ ወይም ሰውነቱን የነካ ጨርቅ እንኳ ወደ ሕመምተኞች ሲወሰዱ በሽታቸው ይለቃቸው ነበር፤ ርኩሳን መናፍስትም ይወጡ ነበር"* ይላል (የሐዋ. 19፥12)። ይሆንን የተመ ለከቱ ለባት ወንድማማቾች አጋንንት ለማስወጣት *"ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እንድትወጡ አዛችኋለሁ እያሉ የጌታን የኢየሱስን ስም ርኩ ሳን መናፍስት በያዟቸው ሰዎች ላይ ለመጥራት ሞክሩ፤ ...ርኩስ መንፈ ሱም 'ኢየሱስን አውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ እናንተ ግን እነ*

ማን ናችሁ' አላቸው። ከዚያም ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ዘሎ ያዛቸው በረታባቸውም፤ እጅግ ሰላየለባቸውም ቤቱን ጥለው ዕራቁታቸውን ሸሹ" ይላል (የሐዋ. 19፥13-16)። ይሄም ሁኔታ ልብ ሳይባል ያለፈ ነገር አልነበረም። "...በኤፌሶን በሚኖሩት የአይሁድና በግሪክ ሰዎች ሁሉ ዘንድ በታወቀ ጊዜ፣ ሁሉም ፍርሃት ያዛቸው፤ በዚህም የጌታ የኢየሱስ ስም ተከበረ። ካመኑትም ሰዎች ብዙዎቹ እየቀረቡ ክፉ ሥራቸውን በግልጥ ተናዘዙ። ሲጠነቁሉ ከነበሩትም መካከል ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በማም ጣት በሕዝብ ፊት አቃጠሉ፤ ዋጋቸውም ሲሰላ ሃምሣ ሺ ብር ያህል ሆኖ ተገኘ። በዚህ ሁኔታ የጌታ ቃል በኃይል እያደገና እያሸነፈ ሄደ" ይላል (የሐዋ. 19፥17-20)።

እንዲሁም በዘሌዋውያን መጽሐፍ ላይ አንድ ወጣት የእግዚአብሔርን ስም በመሳደቡ ምክንያት ከፍተኛ ቅጣት እንደ ደረሰበት ታሪኩን እናነባለን። ወጣቱ "እግዚአብሔርን ሲሳደብ ስምተናል" በማለት ከሰሰው። ሙሴ ፊት ባቀረቡበት ወቅት፥ *"እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ አውጣው፤ ሲሳደብ የሰሙት ሁሉ እጃቸውን በራሱ ላይ ይጫኑበት፤ ማኅበሩም ሁሉ በድንጋይ ይውገረው። አስራኤላውያንን እንዲህ በላቸው ማንም ሰው አምላኩን ቢሳደብ ኃጢአት ሠርቶአልና ይጠየቅበታል። የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደብ ማንኛውም ሰው ይገደል፤ ማኅበሩ ሁሉ ይውገሩት፤ መጻተኛም ሆነ የአገር ተወላጅ የእግዚአብሔርን ስም ከሰደበ ይገደል"* አለ (ዘሌዋ. 24፥13-16)።

የእግዚአብሔርን ስም በአግባቡ ማንሳት (መጥራት) እንዲችሉ እግዚአብሔር ለሰዎች ሙሉ ነጻነትን ሰጥቷቸዋል፥

(1) *አንደኛው በጸሎታቸው ወቅት የእግዚአብሔርን ስም እንዲጠቀሙ ፈቅዷል።* እንዲያውም ደቀ መዛሙርቱን ስለ ጸሎት ሲያስተምራቸው፣ "ስምህ ይቀደስ" ብለው እንዲጸልዩ ነግሯቸዋል። እግዚአብሔርን ስናመልክ፣ የተቀደስ ስሙን ከፍ ከፍ እንድናደርግ በቃሉ ታዘናል። ስሙ የተባረከ፣ የተቀደሰ፣ ከስም ሁሉ በላይ በመሆኑ ከፍ ከፍ ልናደርገው ይገባል። ማርቲን ሉተር የእግዚአብሔርን ስም ማክበር ምን እንደሆነ ሲጽፍ፣ "በጸሎት፣ በምስጋና፣ በአምልኮት ታላቅ ስሙን ከፍ ማድረግ ነው" ይላል። ዘማሪው *"ሰሰሙ የሚገባ ክብር፣ ለእግዚአብሔር ስጡ፤ በቅድስናው ግርማ ለእግዚአብሔር ስገዱ"* ይላል (መዝ. 29፥2)። *"ለሰሙ ክብር ዘምሩ ውዳሴውንም አድምቁ"* (መዝ. 66፥2)። *"ከዙር ስሙ ለዘላለም ይባረክ፤ ምድርም ሁሉ በክብሩ ይሞላ። አሜን! አሜን!"* (መዝ. 72፥19) ይላል። ዳዊትም *"ነፍሴ ሆይ! እግዚአብሔርን ባርኪ፤ የውስጥ ሰውነቴም ሁሉ ቅዱስ ስሙን ባርኪ"* ይላል (መዝ. 103፥1)።

(2) *የእግዚአብሔርን ስም ሰናከብር እግዚአብሔር ራሱን ማክበራችን ነው።* ጳውሎስም *"በእርሱ በኩል ለእግዚአብሔር አብ ምስጋና እያቀረባችሁ በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት"* ይለናል (ቆላ. 3፥17)። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት ክብርና ምስጋና የሚገባውን የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ እንዳናነሳ፣ ስሙን መጠቀምያ፣ የራሳችንን አጀንዳ ማስፈጸሚያ እንዳናደርግ፣ እግዚአብሔርን በውሸት ለማክበርም ሆነ ለማስከበር፣ በሙን ጠርተን ያላደረገውን "አደረገ"፣ ያልተናገረውን "ተናገረ" በማለት ስሙን ያለአግባብ እንዳናነሳ እንጠንቀቅ። እግዚአብሔርን ይህንን ትዕዛዝ የስጠን፣ በቃላችን እንድናጠናው ብቻ ሳይሆን፣ በሕጉ መሠረት እንድንኖር ነው። በዘመናችን ይሄ ሁሉ የውሸት ትንቢት ተሰፋፍቶ እያየ "እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?" በማለት ብዙዎች ይጠይቃሉ። ዝም ማለቱ ባይሆን፣ ለበዳዮቹ የንስሀ ጊዜ ለመስጠት ሲል መታገሱ ብቻ እንደሆነ እንወቅ።

ምዕራፍ ስድስት

አራተኛው ትዕዛዝ

ሚዛናዊ ኑሮ ኑሩ

"የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፤ ስድስት ቀን ሥራ፤ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። እንተ፣ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ ከብትህም፣ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ፣ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታልና ቀድሶታልም።"
(ኦሪት ዘጸአት 20፥8-11)

ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ በሰፊው የተገለጸው ከላይ የሰማነው አራተኛው ትዕዛዝ ሲሆን፣ በውስጡ ሦስት ክፍሎችን ይዟል። ይኸውም፣

◆ 1ኛው~ ቁጥር 8 ላይ "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ" የሚለው ሲሆን፥ ይሄም የሰንበትን ቀን ማክበር እንዳለብን የሚያዝ ነው።

◆ 2ኛው~ ቁጥር 9 እና 10 ላይ የተጠቀሰው ሲሆን፥ ያም ስንበትን በምን ዓይነት ሁኔታ መከበር እንዳለበት የሚገልጽ ነው።

◆ 3ኛው~ ቁጥር 11 ላይ "...እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታልና ቀድሶታልም" የሚለው ሲሆን፣ ይሄም ስንበትን ማክበር ያስፈለገበትን ምክንያት የሚገልጽ ነው።

በዚህ ሩጫና ጥድፍያ በሞላበት ዓለም ውስጥ የሚኖሩ የዘመኑ ሰዎች፥ "ጊዜ የለኝም... ጊዜ አጣሁ... ሰዓቱ አልበቃ አለኝ.." ሲሉ መስማት ለብዙ ዎቻችን ይህን ያህል አዲስ ነገር አይሰማም። "በዚህ ሳምንት ውስጥ አንድ ተጨማሪ ቀን ባገኝ ሥራዬን ሁሉ አጠናቅቄ እጨርስ ነበር... በቀኑ ውስጥ ጥቂት ተጨማሪ ሰዓት ቢኖረኝ፣...መጽሐፍ ቅዱሴን ማንበብ፣ መጸለይ እችል ነበር..." በማለት ምኞታቸውን ሲገልጡ ስንሰማ፣ ብዙዎች ምን ያህል የጊዜ እጥረት እንዳሰባቸው መረዳት እንችላለን።

ተፈጣሪ የሆነው ሰው ውስን በመሆኑ፣ ያሰው ነገር ሁሉ የተትረፈረፈ ባይሆን ተውስኖ የተሰጠው ነው። ያለው ህብት፣ ያለው ጉልበት፣ ያለው ጊዜ የተወሰነ ነው። "አለኝ! የእኔ ነው" የሚለው ነገር ሁሉ ውስን ነው። "ጉልበት አለኝ" ቢል ጉልበቱ የተወሰነ ነው። "ገንዘብ አለኝ" ቢል፣ ገንዘቡ ውስን ነው፤ እንዲሁም "ጊዜ አለኝ" ቢል፣ ጊዜው ውስን ነው። በቀን ውስጥ ሰዐው ተወስኖ የተሰጠው 24 ሰዓት ብቻ ስለሆነ፣ ያንን እብቃቅቶ መኖር አለበት። ይሁን እንጂ ተጨማሪ ገንዘብ የማግኘት ዕድል እንኳን ቢኖረው፣ ተጨማሪ ጊዜ ቢሰጠው፣ "ይበቃኛል" የሚል ባሕሪ ስለሌለው፣ ሌላ ተጨማሪ ህብት፣ ተጨማሪ ጊዜም ሆነ ገንዘብ መፈለጉ የማይቀር ነው። ያልተወሰን ህብትም ሆነ ያልተወሰን ጊዜ ያለው፣ ወሰን የሌለው ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ህብቱ ወሰን የለውም፤ ጉልበቱ ወሰን የለውም፤ ያለው ጊዜ ገደብ የለውም።

ስለዚህ ሰው በቀን ውስጥ ተመድቦ የተሰጠውን 24 ሰዓት ያለአግባብ ባያባክን እብቃቅቶና አደላድሎ መጠቀም መቻል አለበት። ሰው ጊዜውን አብቃቅቶና አደላድሎ መኖር ያልቻለ መሆኑን የሚያውቀው እግዚአብሔር፣ በምህረትና በፍቅር የተሞላው ጊታ፥ የልጆቹ ደስታና ዕርካታ ማጣት ግድ ስለሚለው፣ ለዚህ ችግራችን ብልሃት ፈጥሮልናል። ይኸውም ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት እንድንኖር ነው። ከሰባት ቀናት ውስጥ ስድስቱን ቀን እንድንሠራ፣ አንዱን ቀን ግን እንድናርፍ ይሆንን መመሪያ ሰጥቶናል።

በዚህ እርሱ ወስኖ በሰጠን የሰንበት ቀን፣ ከዕለታዊ ሥራችን የምናርፍበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ የሕይወታችን መሪና ጌታ የሆነውን እምላክ የምናመሰግንበትና እንዲሁም በእውነትና በእምነት እርሱን የምናመልክበት የአምልኮት ጊዜ እንዲሆንልን ይፈልጋል።

የሰንበትን ቀን ማክበር ጊዜን ማባከን አይደለም

የሰንበትን ቀን ማክበር ጊዜን ማባከን፣ ሰንፍናን ማስተናገድ መሰሉ የሚታያቸው አንዳንድ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። በሰንበት ቀን በእምልኮት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ፈንታ የበለጠ የመሸሺያ ምክን ያት የሚሆንባቸው ብዙዎች አሉ። በሰንበትን ቀን ቤተ ክርስቲያን ሄደው ጌታቸውን ከማምለክ ይልቅ፣ ጊዜውን ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ይጠቀ መብታል። የታወቀው አሜሪካዊው ቢሊየነር፣ ቢል ጌትስ በእግዚአብሔር ለምን እንደማያምን ተጠይቆ ሲመልስ፣

> ማይማኖት ጊዜን በአግባቡ እንድንጠቀምበት አያደርግም። ይሄም ትልቁ የሃይማኖት ድካም ነው። ዕሁድ ጥዋት ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ ይልቅ፣ በዚያ ጊዜ ውስጥ ሌላ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ልሠራበት እችላለሁ" አለ።

የሰንበትን ቀን ማሰብ፣ እግዚአብሔር ወስኖ በሰጠን ቀን ማረፍ፣ እን ዲሁም ጌታን ማምለክ በአንዳንድ ሰዎች ዓይን ሲታይ ጊዜ ማባከን ይም ሰል እንጂ፣ ሕጉን ያወጣው ጌታ ጠቃሚነቱን አይቶ መሆኑን ብዙዎች የተረዱት እይመስሉም። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከሰጠው አሥ ርቱ ትዕዛዛት መካከል አንደኛው የሰንበትን ቀን እንዲያስታውሱና እንዲ ያከብሩ ነው።

"የሰንበትን ቀን እስቡ" ሲላቸው ለእስራኤላውያን ሰንበት የማያውቁት እዲሰ ነገር እንዳልሆነ እንረዳለን። የሚያስቡት ከዚህ በፊት የሚያውቁት ሲሆን ነው። በበረሃ ጉዟቸው ዘመን ከሰምንቱ ውስጥ ሰድስቱን ቀን እግዚ አብሔር መና ከሰማይ እያወረደላቸው ይለቅሙ ነበር። በሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ወይም የሰንበት ቀን ስለሆነ፣ መና ስመሰብሰብ እይጠቀሙበ ትም ነበር። "እርሱም እንዲህ አላቸው፤ 'የነገው ዕለት ለእርሱ ተለይቶ የተ ቀደሰ የዕረፍት ቀን እንዲሆን እግዚአብሔር አዝዞአል፤ ስለዚህ ዛሬውኑ

የምትጋግሩትን ጋግሩ፤ የምትቀቅሉትንም ቀቅሉ፤ የተረፈው ለነገ ይቀ መጥ' አላቸው (ዘፀ. 16፥23)። ሲና ተራራ ሲደርሱ ከዚህ በፊት የሚያው ቁት ነገር በመሆኑ ነው እግዚአብሔር "የሰንበትን ቀን አስታውሱ" ያላ ቸው። የሚያስታውሱትም አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በየሳምንቱ ነበር። ይህ ሕግ እነርሱን ብቻ ሳይሆን እኛንም ስለሚመለከት፣ እኛም በዚሁ ዓይነት በየሳምንቱ የሰንበትን ቀን ማሰታወስ አለብን። እኛ ሰዎች፣ የእግዚአብ ሔርን የመፍጠርም ሆነ የመቤዠት ሥራውን የመርሳት ዝንባሌ አለን። ስለዚህ፣ እንደፈጠረንና እንደቤዠን ወይም እንዳዳነን በማስታወስ ማመሰ ገንን እንዳንረሳ ነው አራተኛውን ትዕዛዝ የሰጠን። አራተኛው ሕግ፣ የአግ ዚአብሔርን ጸጋ በማሰብ እንድናመሰግንበት የተሰጠን ነው።

"አስብ" የሚለው ቃል የረሳኸውን ማስታወስ ብቻ ሳይሆን፣ መላው ሕዋሳታችን እግዚአብሔርን በማመስገን ውስጥ እንዲሆኑ የሚጠይቅ ነው። የሰንበትን ቀን የምናከብረው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? በሳምንቱ ውስጥ ስድስቱን ቀን እንድንሠራ፣ አንዱን ቀን እንድናርፍ ነው። "...ስድ ስት ቀን ሥራ ተሰጥሀንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው" ይላል። ሰሥራ የመደበው ስድስት ቀን ሲሆን ለዕረፍት ግን አንድ ቀን ብቻ ሲመድብ፣ የሥራን አስፈላጊነት፣ ወይም ሳይሰሩ ሰመኖር መሞከር የእግዚአብሔርን ሕግና ደንብ መጣስ እንደሆነ መረዳት ያስችለናል።

ሥራ መሥራት ዕርግማን አይደለም

አንዳንድ ሰዎች ሥራን እንደ ዕርግማን የሚቆጥሩት አሉ። በዕለት ተዕራቸው ላይ ተሰልፈው ሲለፉ፣ ከፉ በሆነ አለቃ ያለአግባብ ሲገፉ ምርር ብሏቸው አዳምን ይወቅሳሉ። "አዳም ኃጢአት ባይሠራ ኖሮ በሥራ አንደከምም ነበርኮ ቁጭ ብለን እንበላ ነበር" ብለው የሚያማርሩ አሉ። ይሁን እንጂ፣ መሥራት በአዳም ምክንያት የመጣ እርግማን እንዳ ልሆነ ማወቅ አለብን። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ያለሥራ ቁጭ ብሎ እንዲበላ እንዳልሆነ በግልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን በዔደን የአትክልት ቦታ አኖረው፤ ይሆን ንም ያደረገው ሰው የአትክልትን ቦታ እንዲያለማና እንዲንከባከበው ነው"

ይላል (ዘፍ. 2፥15)። እግዚአብሔር ይህን ያሰው አዳም በኃጢአት ከመው ደቁ በፊት መሆኑን በግልጽ እናያለን።

የመጀመሪያው ሰው አዳም እግዚአብሔር ካሰመረለት መሰመር ሲወጣ ወይም እግዚአብሔር "አታድርግ" ያለውን ነገር "እምቢ!" ሲል፣ ምንጊዜም እምቢተኛውን ሳይቀጣ የማያልፍ በመሆኑ፣ ለአዳምና ሔዋን እንዲሁም ለእባቢቱ ተገቢውን ቅጣት ሰጣቸው። አዳምን "አንተ በፈጸምከው ክፉ ሥራ ምክንያት ምድር የተረገመች ትሁንሃ ምድር በቂ ምግብ እንድ ትሰጥህ ዕድሜህን ሙሉ በብርቱ ደክም ትሠራለህ" አለው (ዘፍ. 3፥17)። እዚህ ላይ የተረገመችው ምድር እንጂ፣ ሥራ መሥራት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምድር ስለተረገመች በቀላሉ ፍሬ ስለማትሰጥ፣ የሚፈልገውን ያህል ፍሬ ለማግኘት፣ ሰው በኃይል መሥራት አለበት። ስለዚህ እኔና አናንተ የተፈጠርነው ያለሥራ ቁጭ ብለን እንድንኖር ሳይሆን ሠርተን በላባችን እንድንኖር ስለሆነ፣ ሥራ መሥራት እርግማን ሳይሆን የተቀደሰ ነው። ሥራን እንደ ዕርግማን እያዩ፣ ቁጭ ብለው ለመብላት የሚመኙ አሉ። አንዳንዶቹም ሲያፍሩ፣ "የእኔ አምላክ ቁጭ እድርጎ እያንቀባረረ ያበላኛል ያኖረኛል" ይላሉ። ሥራ ሳይሠሩ ቁጭ ብሎ መኖር በረከት ሳይሆን፣ እር ግማን ነው።

ሳይሠሩ ማረፍ የለም

አራተኛው ሕግ "የሰንበትን ቀን እንቀድሰውና እናስበው ዘንድ" ያዛል። ሰባተኛውን ቀን ለመቀደስና ለማሰብ ግን በቅድሚያ ሰድስቱን ቀን እንደ ሚጠበቅብን ያህል በእግባቡ መሥራት አለብን። ቅደም ተከተሉን ሳን ለቅ፣ ይኸውም መጀመሪያ ሠርተን፣ ቀጥሎ ማረፍ አለብን። በሥራ ሳን ደክም እንዲሁ ማረፉ የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ መጠበቃችን አይሆንም። በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔርን ሕግ ሙሉ በሙሉ የምንጠብ ቀው፣ በሰንበት ቀን በማረፋችን ብቻ ሳይሆን በዕለታዊ ሥራችንም ትጋት በማሳየታችንም ጭምር ነው። ስለዚህ እኔና አናንተ የእግዚአብሔርን በረከት የምናገኘው በተመደብንበት ዕለታዊ ሥራችን ላይ ተሰልፈን በታ ማኝነት በመሥራት ጭምር ነው። እግዚአብሔር ቢፈልግ አንዱን ቀን ብቻ ሳይሆን፣ ሰባቱንም ቀን የሰንበት ቀን፣ ወይም የዕረፍት ጊዜ ሊያደር ገው ይችል ነበር። ነገር ግን ስድስት ቀን ሠርተን በሰባተኛው ቀን እንድና

ርፍ እደረገ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚያሠራ፣ ለሠራተኞቹ አስፈላጊ ውን ዕረፍት የማይሰጥ ጨካኝ ጌታ እንዳልሆነ አራተኛው ሕግ ያሳየናል። "ስድስቱን ቀን ሥሩና ሰባተኛውን ቀን እኔን ለማክበርና ለማመስገን ጊዜ ውን ተጠቀሙበት" ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር የደነገጋቸው ሕጎች አሉ። ከነ ዚህ ሕጎች ውስጥ አንደኛው ሰው ሠርቶ በላቡ እንዲኖር መሆኑን ከላይ ጠቅሰናል። እግዚአብሔር ለአዳም "ምድር በቂ ምግብ እንድትሰጥህ ዕድ ሜህን ሙሉ በብርቱ ደክም ትሠራለህ" አለው ይህ ሕግ ለእኛም ይሠ ራል። እግዚአብሔርን ቅር የሚለው፣ ተራ ሥራ መሥራታችን ሳይሆን፣ ቁጭ ብለን በሌላው ሰው ድካምና ላብ ለመኖር ሰንሞክር ነው። የእግዚአ ብሔር ዕቅድና ዓላማ ያለበት ነገር ሁሉ የተቀደሰ ስለሆነ፣ ሠርቶ መብ ላትም የተቀደሰ ነው። ጳውሎስ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይ ሠሩ የሚኖሩትን አንዳንድ አማኞችን ሲመክር፣ "...እነዚህ ሰዎች በግልግ ባቸው ነገር እየገቡ ሌሎችን ከመገከ በቀር ምንም ሳይሠሩ የሚኖሩ ናቸው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በሥርዓት አንዲኖሩና ሠርተው የራሳቸውን ምግብ እንዲበሉም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እናዛቸዋለንሃ እናሰጠነትቃቸዋ ለንም ይላል (2 ተሰ. 3፥11-12)።

በትጋት መሥራታችን፣ በሥራ ዓለም ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሳችን እግዚአብሔርን ቅር የማያሰኘው ከሆነ፣ አንግዲያውስ ችግራ ችን ምኑ ላይ ነው? እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኘው፣ ከርስትናችን በዕለታዊ ሥራችን ላይ ሳይታይ ሲቀር፣ ለማደግ ወይም ለመኖም ሰንል ሌላውን ጨፍልቀን ሰንሄድ፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ጊዜ ሰንከል ከል፣ ታዋቂነት፣ ሥልጣንን ብዙ ገንዘብ ለማግኘት፣ "እከሌ!" ተብሎ ለመጠራት ብቻ ከክርስትና ሕይወት ውጪ የሆነ ሥራ ሥንሠራ እግዚአ ብሔርን ቅር ይለዋል። የምንፈልገው በዕለታዊ ሥራችን እግዚአብሔር እንዲከብር፣ እንደ ጥሩ አምባሳደር እርሱን የምንወክለው፣ በመልካም ሥራችን ስሙን የምናስመሰግን ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር በፊት ሥራችን ቀድሞ የማይገኝ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በሥራችን ደሰ ይለዋል። እግዚአ ብሔር ለእኔና ለእናንተ ያለው ዓላማ ምን እንደሆነ በጳውሎስ አማካኝነት ሲነግረን፣ "በጸጥታ ለመኖር እንድትጣጣሩ፣ የራሳችሁን ጉዳይ እንድታ ስቡ፣ ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁም በገዛ እጃችሁ እንድትሠሩ ነው። በዚህ

ዓይነት በማያምኑ ሰዎች ዘንድ የተከበራችሁ ትሆናላችሁ፤ የማንም ጥሻ ሳትሆኑ ራሳችሁን ችላችሁ ትኖራላችሁ" ይለናል። (1 ተሰሎ. 4፥11-12)።

የእግዚአብሔር ቃል "በገዛ እጃችሁ እየሠራችሁ ለመኖር እንድትጣጣሩ" ሲል፣ የማንም ጥገኞች እንዳንሆን፣ ራሳችንን ችለን እንድንኖር፣ ሲመክረን ነው። አንዳንዶቻችን በቀን ስምንት ሰዓት በመሥራታችን "ደከመን" ብለን በእግዚአብሔር ላይ የምናጉረመርምበትና የምናማርር በት፣ ሥራችንን እንደ እርግማን የምንቆጥርበት ጊዜ አለ። ከእኛ ያነሱ ጥቃቅን ፍጥረታት የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት ምን ያህል ሰዓት በት ጋት እንደሚሠሩና እንደሚለፉ ስንረዳ ራሳችንን እንታዘባለን። ስንፍና ሰሚጫጫነን ሰዎች ከጉንዳኖች እንድንማር የእግዚአብሔር ቃል ይመክ ረናል። "ሰነፎች ሰዎች ከጉንዳኖች አኗኗር ትምህርት መቅሰም ይገባቸዋል። ጉንዳኖች መሪ አለቃ ወይም ገዥ የላቸውም። ነገር ግን በዚያ ጊዜ ሞኒያ ፈልጋቸውን ምግብ ይሰበስባሉ። ታዲያ ሰነፍ የሚተኛው እስከ መቼ ነው? ...ደሀንነትና ሞጣት የጦር መሣሪያ እንደታጠቀ ወንበዴ በድንገት ይደርስ ቢታል" ይላል (ምሳሌ 8፥6-11)። ስለዚህ፣ ጌታ ባስቀመጣችሁ ቦታ ሆና ችሁ በጌታ ፈቃድ ውስጥ መሆናችሁን ተረድታችሁ በሥራችሁ ደስ ይበ ላችሁ። ባላችሁበት የሥራ መስክ ውስጥ ክርስትናችሁ ሲታይ አብረዋችሁ ለሚሠሩት ዓለማውያን መልካም ምስክሮች መሆናችሁን አትዘንጉት።

የምትኖሩት፣ የምትሠሩት እውነትነት በሌላቸው፣ በሚያታልሉና በሚያጭበረብሩ ሰዎች መካከል ነው። በየቀኑ ከነናችሁ ሆነው የሚሠሩ ሠራተኞች የሚያደርጉትን ትክክል ያልሆነ ነገር ታውቃላችሁ። ሰምሳሌ ሰዓት እሳልፎ መግባት፣ ሰምሳ ሰዓት ከተፈቀደው በላይ መውሰድ፣ ሰዓቱ ሳይደርስ ከሥራ መውጣት፣ ሳይታመሙ "ታምሚአለሁ" ብሎ በመቅረት የሚባክነው ጊዜ በጣም ብዙ ነው። እግዚአብሔር እኔና እናንተን በዚህ ጨለማ በሆነው ዓለም ውስጥ ያስቀመጠን በጥሩ ምሳሌነታችን ብርሃን እን ድንሆን ነው። ለመሆኑ ክርስቲያኖች በሥራ ዓለም ውስጥ ክርስትናቸውን ይኖሩበታል ወይ? በክርስትና ሕይወት ያላቸው ውበት በግልጽ ይታያል ወይ? እያንዳንዳችን ሰዚህ ጥያቄ እውነተኛውን መልስ መስጠት አለብን። የሚያሳዝነው፣ ዓለማውያንና ክርስቲያኖች በሥራቸው ላይ ያላቸው ታታ ሪነትም ሆነ ታማኝነት ይሆን ያህል የማይባላለጥ መሆኑ ነው። የእግዚአብ ሔር ዓላማና ፈቃድ፣ ክርስቲያኖች በሥራ ዓለም ውስጥ በሕይወታቸው

ውስጥ የክርስቶስ ውበት ኖሯቸው በዓለማውያን ዘንድ ተከብረው እንዲኖሩ ነው።

"የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባር ሆንም ሁሉ አድርግ። ሰባተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው የሚለው አራተኛው ትዕዛዝ (ሕግ)፣ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ አንደኛው ከላይ የገለጽነው "ስድስት ቀን ሥራ" የሚሰው ክፍል ሲሆን፥ በዚህ ውስጥ የሥራን ክቡርነትና አስፈላጊነት ተመልክተናል። ሁለተኛው ደግሞ "ሰባተውኛውን ቀን ግን ለአምላክህ የተሰጠ የሰንበት ቀን ስለሆነ፣ ምንም አትሥራበት" የሚለው ነው። እዚህ ላይ ማወቅ ያለ ብን እውነት ቢኖር የሥራን አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን፣ በሥራ ምክንያት እግዚአብሔርን የምናመልክበትንና የምናከብርበትን ቀን እንዳናጣ የሚያ ስጠነቅቅ ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች ሚዛናቸውን ካልጠበቁ፣ ጤናማ የሆነ፣ ዕድገት ያለበት መንፈሳዊ ሕይወት መኖር አንችልም።

በሥራችን የምንፈልገው ምንድነው? ታዋቂነት፣ ሥልጣን፣ ብዙ ገን ዘብ፣ ከሌሎች በልጠ ለመታየት፣ "እከሌ!" ተብሎ ለመጠራት ይሆን? ከላይ የዘረዘርናቸውን ሁሉ ማግኘት ኃጢአት አይደለም። በሥራ ዓለም ከፍተኛ ደረጃ መድረስ እግዚአብሔርን ቅር አያሰኘውም። ይሁን እንጂ፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ጊዜ እንዳንሰጥ ዕንቅፋት የሚሆንብን ከሆነ፣ እርሱን የምናመልክበት ጊዜ የሚያሳጣን ከሆነ፣ አራተኛውን ሕግ (ትዕዛዝ) መጣሳችን እንደሆነ ማወቅ ይገባናል። በሳምንት 40 ሰዓት በመሥራት ፈንታ 70 ወይም 80 ሰዓት ብንሠራ ብርቱ ሠራተኞች ያሰኘናል እንጂ፣ "ሰነፎች" ተብለን አንጠራም። ይህም መንፈሳዊነት የሌለው ይምሰል እንጂ መንፈሳዊ ሕይወታችንን የመንካት ኃይል አለው። 70 ወይም 80 ሰዓት ስንሠራ የሥጋችን አቅም ውስን ስለሆነ ይደክመውና መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣ መጸሰይ፣ በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ስለማንችል፣ ቤተ ክርስቲያን መሄዳችን ይቀራል። ቤተ ክርስቲያን ብንሄድም ዕንቅልፍ ዕንቅልፍ ስለሚሰን እንደሚገባው የእግዚአብሔርን ቃል መሰማት አንች ልም። በዚህ ዓይነት ሰመንፈሳዊ ሕይወታችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማግኘት ስለማንችል ቀስ በቀስ መንፈሳዊ ሕይወታችን እየደከመ መምጣቱ አይቀርም። አራተኛው ሕግ በሚያዘው መሠረት ስድስት ቀን በመሥራት ፈንታ ሰባቱንም ሩን ሥንሠራ ሰጊዜው የምንፈልገውን ገንዘብ ማግኘት ያስችሰን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳችንንና መንፈሳዊ መጽሐፍትን የምናነብ

በትን፣ ከጌታ ጋር በጸሎት የምናሳልፍበትን፣ ከአማኞች ጋር ህብረት የም ናደርግበትን ለዓት ስለሚሻማብን፣ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይጎዳል። ችግሩ ያለው ሥራ መሥራታችን ላይ ሳይሆን፣ አኔና እናንተ ጊዜያችንን በአግባቡ በመጠቀም ሚዛናዊ የሆነ ኑሮ መኖር ባለመቻላችን ነው።

ለንበትን መጠበቅ ቁጥን ለይተን ለእግዚአብሔር መስጠትና እርሱን ማክበር ማለት ነው።

- "ሰንበታቴን ጠብቁ፣ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ" ይላል (ዘሌ. 19፡3)። እንዲሁም
- "ሥራ የምትሠሩበት ስድስት ቀን አላችሁ፣ ሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ጊዜ፣ የተቀደሰ ጉባኤ ዕለት ነው። የእግዚአብሔር ሰን በት ስለሆነ በምትኖሩበት ሥፍራ ሁሉ ምንም ዓይነት ሥራ አት ሥሩበት" ይላል (ዘሌ. 23፥3)።

በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ በሰንበት ቀን ቤተ መቅደስ በመሄድ ሰንበትን ያከብር እንደነበረ እናስታውሳለን። "...እንደ ልማዱም በሰንበት ወደ ምኩ ራብ ገባ፣ ሊያነብም ተነሣ" ይላል (ሉቃ. 4፥16)።

- ሰንበት የሚለው ቃል የመጣው ከዕብራይስጥ ቋንቋ "ሸባት" ከሚ ለው ሲሆን፣ ቀጥተኛ ትርጉሙም "ማቆም" ወይም "መጨረስ" ማለት ነው።

"ሸባት" የሚለው ቃል ሁለት ዓይነት አሳብን ይዟል። አንደኛው፣ የሳምንቱ መጨረሻ መሆኑን ይገልጻል። በአብራውያን ዘንድ የሳምንቱ መጨረሻ "ቅዳሜ" ቀን ነው። "ሸባት" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሌላው አሳብ፣ እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ጨርሶ ያቆመበትን ሰባተኛ ውን ቀን የሚያመለክት ነው። ይሄ "ሸባት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር በመፍጠር ሥራው ሳይ ስለ ደከመው ከድካሙ ያረፈ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ኃያል፣ ምንጊዜም የማይ ደክመው አምላክ በመሆኑ ነው።

እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ሥራውን ጨርሶ ሲያርፍ፣ የፈጠራ ቸው ሰዎችም ይህንኑ መንገድ እንዲከተሉ፣ ይኸውም ስድስት ቀን ሠር ተው፣ በሰባተኛው ቀን እንዲያርፉ ይፈልጋል። ስለዚህ ሰባተኛው ቀን እንደተለመደው የሥራ ቀን አይደለም። የመዝናኛና የማገገሚያ፣ ከልማ

ዳዊ ሥራ ገለል ብሎ የእግዚአብሔርን ጸጋና በጎነት የማሰቢያ ቀን ነው። ቶማስ ዋትሰን የተባለው ጸሐፊ፣

> "በሰንበት ቀን እድካሚ ሥራ የሚሠራ፣ ያ ሰው መንፈሳዊነት የሌ ለው፣ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ወይም ቅር የሚያሰኝ ሰው ነው። በሰንበት ቀን ዓለማዊ የሆነ ሥራ የሚሠራ፣ በሰይጣን እርሻ ውስጥ የሚያርስ ነው። ያ ሰው ነፍሱን ያረክሳል። እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን የሰጠው ሰው ልቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲያኖሳና ከአምላኩ ጋር እንዲነጋገርበት፣ መልካም የሆነ ሥራ እንዲሠራ በት ነው። በዚህ ዕለት ዓለማዊ የሆነውን ሥራ መሥራት ከቡር የሆነውን ነፍሱን ዝቅ ማድ ረግ ነው" አለ።

የለንበትን ቀን "እግዚአብሔር ባርኮታል፣ ቀድሶታልም" ሲል፣ የተቀ ደሰ (ቅዱስ) ሆኗል ማለት ነው። "ቅዱስ" የሚለው ቃል "ሆሊዮስ" ከሚለው የግሪክ ቋንቋ የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም "የተለየ" ማለት ነው። ፍጹም መሆን፣ ወይም እንከን የሌለበት ከሚለው ጋር የተያያዘ አይደለም። ቅዱስ የሚለውን ቃል በትክክል ያልተረዱ ሰዎች ቀን እንዴት ቅዱስ ይሆናል ብለው መጠየቃቸው አይቀርም። ስለዚህ ለንበት ቅዱስ የሆነው፣ ከሌሎች ቀኖች ውስጥ ለእግዚአብሔር እንዲሆን የተለየ፣ ሰዎች የዕለት ሥራቸውን የማይሠሩበት ቀን በመሆኑ ነው። ለንበት ቅዱስ የሆነበት ምክንያት፣ ከሌሎች ቀናት የተለየ፣ "የጌታ ቀን" ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ ነው። እስራኤላውያን ለንበትን የሚያከብሩት የዕረፍታቸው ጊዜ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ቃሉን የሚሰሙበት፣ የሚጸልዩበት፣ ጌታቸውን የሚያመ ልኩበት፣ ወይም ወደ እርሱ የሚቀርቡበት ቀን በመሆኑ ነው። ይሁን እንጂ፣ ይሄ አራተኛው ሕግ በብዙዎች ዘንድ ችላ የተባለ ሕግ ነው።

በብሉይ ኪዳን የለንበትን ቀን አለማክበር ከፍተኛ ቅጣት ያስከፍል እንደነበረ እናውቃለን። "እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩበት ጊዜ አንድ ሰው በሰንበት ቀን ዕንጨት ሲለቅም ተገኘ። ዕንጨት ሲለቅም ያገኙትም ሰዎች ሰውየውን ወደ ሙሴ፣ ወደ አሮንና ወደ መላው የእስራኤል ማኅበር አመጡት፤ በሰውየው ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ግልጽ የሆነ ነገር ባለመኖሩ በጥብቃ ሥር እንዲቆይ አደረጉት። ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን 'ሰውየው ይመትት፤ መላውም ማኅበር ከሰፈር ውጭ በድንጋይ ይውገረው' አለው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሙሴን በዘዘው መሠረት ማኅበሩ ሰውየውን ከሰፈር አውጥቶ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ

ወገረው" (ዘኁልቁ 15፥32-36) ይላል። እንጨት መልቀም ስውን እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል ወንጀል ሆኖ ለምን ታየ? ይህን ያህል ማንን ይጎዳል? ይሄ ትልቅ ጭካኔ አይደለም ወይ? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ወንጀሉ "እንጨት መለቀሰው" ላይ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱን አለማክበር ስለሆነ ነው። አራተኛው ትዕዛዝ የሚያዘው ምንድነው? ስንበትን ማክበር ከሆነ፣ የምናከብረው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ስድስት ቀን ሠርተን፣ በሰባተኛው ቀን እንድናርፍና እርሱን እንድናመልክ ነው። *"ሥራ የምትሠሩበት ስድስት ቀን አላችሁ፣ በሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት፣ የተቀደሰ ጉባኤ ዕለት ነው። የእግዚአብሔር ሰንበት ስለሆነ፣ በምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ ምንም ዓይነት ሥራ አትሥሩበት"* ይላል (ዘሌ. 23፥3)።

ሰንበትን ለምን እናከብራለን?

እግዚአብሔር ይህን አራተኛውን ትዕዛዝ የሰጠበት ምክንያት ምን ይሆን? ምክንያቱን ለመረዳት ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ሠርተን እንድናርፍ የታዘዝነው፣ ሠርቶ ያረፈውን እግዚአብሔርን እንድናገለግል ነው። ስንበትን ማስታወስ ያለብን ምክንያት ምንድነው?

1. *አንደኛ ምክንያት "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ፈጥሮ፣ በሰባተኛው ቀን ስላረፈ፣ የሰንበትንም ቀን ስለባረከውና ስለቀደሰው"* ነው (ዘፀ. 20፥11)። አራተኛው ሕግ፣ ከሌሎች ሁሉ በጣም የቆየ፣ ወይም ቀደም ሲል የነበረ ነው። ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረበት ጊዜ የነበረ በመሆኑ ነው።

2. የሰንበትን ቀን ማክበር ያለብን ሌላው ምክንያት እግዚአብሔርን እንድናመልክ የሚያሳስብ በመሆኑ ነው። መንፈሳዊውንና ሥጋዊ ሕይወታችንን የሚያድስ በመሆኑ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን ትዕዛዝ የሰጠን ሊጎዳን፣ ወይም ስንስት ሊቀጣን፣ መንገዳችንን ጠባብ ሊያደርግብን ሳይሆን፣ ለጥቅማችን እንዲሆን ነው። ስለዚህ ነው ኢየሱስ *"ሰንበት ሰለው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረም"* ያለው (ማር. 2፥27)። ሥራ ክቡር መሆኑን የምንረዳው፣ እግዚአብሔር ራሱ ስለሚሠራ ነው። ሥራ መሥራት ያለብን፣ የሚሠራውን እግዚአብሔርን መስለን በመፈጠራችን ነው። የምንመስለውም በመሥራታችን ብቻ ሳይሆን በማረፋችንም ጭምር ነው። እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ሲጨርስ ያረፈ መሆኑን እናውቃለን። *"እግዚአብሔር ይሠራ የነበረውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ላይ ፈጽሞ ዝበርI ስለዚህ ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ። እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከውI ቀደሰውምI ካከናወነው የመፍጠር ሥራው ሁሉ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነውና"* ይላል (ዘፍ. 2፥2-3)። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ሌላ ነገር ከመባረኩ በፊት መጀመሪያ የባረከው ሰባተኛውን ቀን እንደሆነ እንረዳለን። ስንበትን የምናከብረው፣ እግዚአብሔር ስለባረከው ነው።

"ስንበትን አክብር" የሚለውን አራተኛው ሕግ እግዚአብሔር ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ አንዱ እንዲሆን ለምን እንዳደረገው መረዳት የሚያስቸግራቸው፣ ጥያቄ የሚሆንባቸው ብዙዎች ናቸው። እስቲ ልብ ብለን እናስብ፣ እግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያስባቸውን መሠረታዊ የሆኑ መመሪያዎች፣ እርሱ ራሱን ደስ የሚያስኘውን፣ ለሕዝቡ በጣም አስፈላጊ ነው የሚለውን በራሱ እጅ፣ ሰድንጋይ ላይ ቀርጾ መስጠቱ ያስደንቃል። ብዙ አስቸጋሪና አሳሳቢ የሆኑ ብዙ ነገሮች በሞሉበት ዓለም ውስጥ አራተኛውን ሕግ ይኸውም "ስንበትን አስታውሱ" ማለቱ በጣም ያስደንቃል።

ለምንድነው? "ስንበትን አስብ" የሚለውን አራተኛው ሕግ፣ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ሥፍራ ያገኘው? "አትሰረቅ...አትግደል...የጎደኖሆን ሚስት አትመኝ..." ከሚለው ጋር አብሮ የቀረበው ብለን መጠየቃችን አይቀርም። "ለንበት ለልጆቹ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ነው" ያለበት ምክንያት ምን ይሆን? ብዙዎቻችን ይህን ትዕዛዝ አጥብቀን እንመለከተውም። በዚህ ዓለም የተመደበልን ጊዜ አጭር ስለሆነ፣ እንዲሁም ጌታ ባስቀመጠን ሥፍራ ብዙ የሚሠራ ነገር አለ ብለን ስለምናስብ ያለዕረፍት ለመሥራት እንሞክራለን። ለአንዳንዶቻችን ከሌሎቹ ሕጎች የበለጠ በሕይወታችን ድክመት የሚታይብን በዚህኛው ትዕዛዝ ላይ ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ ችላ ማለታችን እየቀጠለ ሲሄድ አልፎ አልፎ ዋጋ መክፈላችን አይቀርም። አንዳንድ ያልጠበቅናቸው ነገሮች በሥጋችን፣ በስሜታችንና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ጉዳት ሊድርስ ይችላል። እግዚአብሔር እኔና

እናንተን በጣም ስለሚወደን፣ የሚጎዳንን ነገር ስንፈጽም እያየ ዝም ብሎ እያልፈንም። ብዙዎች አልፎ አልፎ "አሁንስ አበዛኸው...ብዙ ሰዓት ትሠራለህ... ዕረፍት ያስፈልግሃል..." የሚል ምክር ቢሰጡንም በጅ የማንል ሰዎች አለን። ይሆን እውነት ሳናውቅ ቀርተን ሳይሆን፣ ችግራችን የምና ውቀውን በተግባር ላይ ማዋል አለመቻላችን ነው።

እግዚአብሔር አራተኛውን ትዕዛዝ (ሕግ) የሰጠን በጣም ስለሚወደን አንዳንድ በጎ ካልሆኑ ነገሮች ሊጠብቀን እንደሆነ ግልጽ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ሕግጋቶች ትኩረት የሚያደርጉት በጣም ከሚወደን ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። እርሱን እንደኛ እንድናደርገው ይፈልጋል። በእኛና በእርሱ መካከል ምንም ነገር እንዲኖር አይፈቅድም። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ እንዲኖረን አይፈል ግም። በልባችን ውስጥ እንደ አምላክ ካስቀመጥናቸው ጣዖቶቻችን ጋር ደባል ሆኖ መኖር አይፈልግም። እንዲሁም፣

ሰሙን የሚያስደብ (በክፉ የሚያስጠራ) ምንም ነገር ሊኖር አይገባም። እውነተኞች ሆነን ራሳችንን መጠየቅ ያስብን ጥያቄ፣ "...በእርግጥ በሕይወቴ ውስጥ ጌታ እንደኛ ነው? ከእርሱ ጋር ባለኝ ግንኙነት ጣልቃ ያስገባሁት ነገር አለ? ችግር ሲያጋጥመኝ፣ በመከራ ውስጥ ሳልፍ አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙኝ ፊቴን የማነሳው ወደ እርሱ ነው? ብቸኛ ስሆን፣ ሁሉ ነገር ችክ ሲልብኝ፣ ሲሰለቸኝ፣ በውስጤ ባዶነት ሲሰማኝ ፊቴን የማነሳው ወደ እርሱ ነው? ፍላጎቴን ያሚሉልኛል ብዬ በአዕምሮዬ የፈጠርኳቸው ከእርሱ ውጪ ሌሎች አማልክቶች ይኖሩኝ ይሆን?" ብሰን መጠየቅ አለብን። መጠየቅ ብቻ ሳይሆን፣ እውነተኛውን መልስ መስጠት አለብን። ራሳችንን በትክክል ማየት ካቃተን ደግሞ "ጌታ ሆይ! ልቤን መርምርና ድካሜን አሳየኝ" ልንለው ይገባል።

አራተኛው ሕግ (ትዕዛዝ)፣ ለዘመኑ ሰው ትልቅ ጥያቄ ሊፈጥርበት እንደሚችል ግልጽ ነው። የሚኖረው የማያቋርጥ ትግል፣ ጥድፍያና ዕረፍት እንዲሁም ሰዕንቅልፍ እንኳን በቂ ጊዜ የማያገኝበት ዓለም ውስጥ ሰለሆነ፣ ይሆን ሕግ ተቀብሎ እንደ ሕጉ መኖር እንዴት ይቻላል? ብሎ መጠየቁ የማይቀር ነው። ብዙዎች በሳምንቱ ውስጥ በተለያየ ሥራ ስለሚባክኑ ጊዜ በማጣት የሚያስፈልጋቸውን ሽቀጣ ሽቀጦችን የሚገዙት ዕሁድ (በሰንበት ቀን) ስለሆነ፣ ዕቃዎቹን የሚሸጡላቸው ሰዎች የግድ በሰንበት ቀን መሥራት ሊኖርባቸው ነው። ብዙዎች በሰንበት ቀን ከቦታ ወደ ቦታ

ስለሚጓጓዙ አውቶብሱን የሚነዱት፣ ዓይሮፕላኑን የሚያበሩት፣ ወይም መኪናቸው ውስጥ ጋዝ የሚሞሉላቸው፣ እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጧቸው ሰዎች የግድ በሰንበት ቀን መሥራት ሊኖርባቸው ነው። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ሊሄዱ፣ የሚሰብኩላቸው፣ የሚያስተምሯቸው፣ የቤተ ክርሰቲያኑን በር የሚከፍቱላቸው፣ እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች ሁሉ ሥራ በመሆናቸው፣ በነዚህ ሥራ ላይ የተሰለፉት ሰዎች ሁሉ ሰንበትን ማፍረሳቸው አይሆንም ወይ? ታዲያ በዚህ ዘመን ሰንበትን ማክበር ወይም መጠበቅ የሚቻለው እንዴት ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን ከጨረሰ በኋላ አረፈ ሲል፣ እግዚአብሔር ደክሞት ዕረፍት ሰላሰፈለገው አይደለም። ቀደም ሲል "ሰንበት" የሚለውን ቃል ሰንገልጽ፣ ዕረፍት የሚለው አሳብ ከድካም ጋር ያልተያያዘ እንደሆነ ሰማሳየት ሞክረናል። እግዚአብሔር ፍጹም ታላቅና ኃያል በመሆኑ በባሕሪው የድካም ስሜት የሚሰማው አምላክ አይደለም። እግዚአብሔር ሁልጊዜ በሥራ ላይ ነው፤ አይደክምም፣ አይታክትም። በሰባተኛው ቀን አረፈ ሲል፣ የመፍጠር ሥራውን ፈጸመ ማለት ነው።

ሥራ ምንድነው?

አራተኛውን ሕግ (ትዕዛዝ) አመዛጋቢ የሚያደርገው "ዕረፍትና" እንዲሁም "ሥራ" ምን እንደሆነ በግልጽ መረዳት ካለመቻል የመጣ ነው። "ሥራ" ምንድነው? ሥራ ምን እንደሆነ የፊዚክስ ሊቆች የሚሰጡት ገለጻ አራተኛውን ትዕዛዝ ወይም ሕግ ለመረዳት እኛን ይህን ያህል አይጠቅመንም። ሥራ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር አይገልጽልንም። በመጠኑም ቢሆን ሥራ ምን እንደሆነ ሀሳብ የሚሰጠን ኤርምያስ 17፥19-27 ላይ የተጠቀሰው ነው። "...በሰንበት ቀን ሸክም ተሸክማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች እንዳታስገቡ ሰራሳችሁ ተጠንቀቁ..." ይላል። የአይሁድ ሊቃውንት ሥራ ምን እንደሆነ ራሳቸው ያወጡት ዝርዝር መግለጫ አላቸው። ሰምሳሌ፣ በአይሁድ ሕግ መሠረት ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው ከአንድ እስክ ሁለት ሺ ሜማ በእግራቸው መሄድ ይችላሉ። ሦስት ሺ ሜማ ቢሄዱ ግን ሰንበትን ማፍረሳቸው ይሆናል። በሰንበት ቀን በአንድ እጃቸው ቋጠሮ መቋጠር ይፈቀድላቸዋል፤ በሁለት እጃቸው ግን ቢቋጥሩ ሰንበትን ማፍረሳቸው ይሆናል። የተጉበት ትራሰ ካልተመቻቸው፣ እጃቸው ሳይነካው

በራሳቸው ማሰተካከል ይችላሉ፤ በእጃቸው ግን ቢያስተካክሉ ሥራ መሥራታቸው ስለሆነ፣ ሰንበትን ማፍረሳቸው ይሆናል። በሰንበት ቀን ከሁለት ደብዳቤ በላይ መጻፍ አይፈቀድላቸውም። የእግራቸውን እውራ ጣት ጥፍር መቁረጥ አይችሉም። በአደጋ ምክንያት አጥንታቸው ቢሰበር፣ ያን የተሰበረውን ሀኪም ዘንድ ሄደው ማስተካከል አይፈቀድላቸውም። ለሕይወቱ የሚያሰጋ በሽታ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰታመመው ሰው ሀክምና መስጠት ሰንበትን ማፍረስ ይሆናል። በክርስቶስ ዘመን የነበሩትን፣ ከላይ በአጭሩ የጠቀስናቸውን ዓይነት ወግ አጥባቂ ፈሪሳውያንን ኢየሱስ ቢጎይል ቢቆጣቸውና ቢገስጻቸው፣ ወይም ቢነቅፋቸው፣ ቁጣውም ሆነ ነቀፋው ከመሰመር የወጣ አይደለም።

ኢየሱስ ስለ ሰንበት የነበረው አቋም ከፈሪሳውያን በጣም የተለየ ነበር። በሰንበት ቀን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በእንድ እርሻ መካከል ሲያልፍ፣ ደቀ መዛሙርቱ እሸት ቀጥፈው በሉ። ፈሪሳውያን ይህን አይተው፣ "ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ቀን ሰምን የተከለከለ ነገር ያደርጋሉ?" ብለው ጠየቁት። ኢየሱስም በብሉይ ኪዳን ዘመን ዳዊት በጣም ቡተራበበት ጊዜ ምን እንዳደረገ ከነገራቸው በኋላ፣ *"ሰንበት ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረምI ስለዚህ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታዋ ነው"* አላቸው (የማር. 2፥27)። ኢየሱስ ይህን ዓይነቱን መመሪያ ብዙ ጊዜ ይሰጥ ነበር። ፈሪሳውያን የሚሰጡትን አስተያየትና ነቀፋ ቢያውቅም ኢየሱስ በተለያየ ጊዜ በሰንበት ቀን በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙትን በሽተኞች ከነበረባቸው በሽታ ይፈውስ ነበር። በሰንበት ቀን በሽተኞችን መፈወሱን ለሚቃወሙት ፈሪሳውያን፣ *"ከእናንተ አንዱ፣ ልጁ ወይም በሬው በሰንበት ቀን ጉድጓድ ቢገባበት ፈጥኖ የማያወጣው ማን ነው?"* ብሎ ይጠይቃቸው ነበር (ሉቃ. 14፥5)። ፈሪሳውያን በሕጋቸው መሠረት "እንስሳውም ሆነ ሰው ሕይወቱ ለሞት የሚያደርሰ ወይም አስጊ ሁኔታ ውስጥ ካልሆነ፣ መፈወስ ሰንበትን አለማክበር ነው" ይሉ ነበር። ኢየሱስ ሰንበትን ይመለከተው የነበረው የሃይማኖት ሥራት ብቻ አድርጎ ሳይሆን ጠቃሚነቱን ነው። ሰንበት የተፈጠረው ሰውን ለመጥቀም እንጂ አግዚአብሔርን ለመጥቀም አይደለም። የሰንበትን ቀን ማክበርና መጠበቅ ሸክም የሚሆን ከሆነ፣ ጠቃሚነት ስለሌለው ዓላማውን የሳተ ይሆናል።

ሰንበትን በትምሕርተ መለኮት አንጻር ለጊዜው መመልከታችንን ትተን ለሰውነታችን አረፍት መስጠት ምን ያህል ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው

ብንመረምር፣ ይሀንን ሕግ የሰጠውን ጌታ አናደንቀዋለን። ሥጋን ማሳረፍና ከድካም እንዲያገግም ማድረግ ለጤንነታችን በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የህክምና ባለሞያዎች ይገልጻሉ፥

- *ያለማቋረጥ ወይም ያለዕረፍት በመሥራታቸው ምክንያት በጃፓን አገር ያሉ መካከለኛ ሥራ አስኪያጆች በድካም ምክንያት የሚሞቱት ወጣቶች ቁጥር መጨመር የጃፓን መንግሥትን አሳስቢ ሁኔታ ውስጥ ጥሏል።*
- *ሰድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ቀን ማረፍ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ታሪክ ይመሰክራል። በፈረንሳይ ርዕዮተ ዓለም ዘመን በሰባተኛው ቀን በማረፍ ፈንታ በአሥረኛው ቀን ሠራተኛው እንዲያርፍ በመደረጉ በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት ትልቅ ነው።*
- *የክርስትና እምነት ጠላት የነበረው ቮልቴርሃ "ክርስትናን ለማስወገድ የክርስቲያኖችን ሰንበት ወርውረን መጣል አለብን" አለ። ይሄም መሐሪ ሳይ ውሎ፥ ያለዕረፍት በመሥራታቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ከድካም የተነሳ ፈረሶቻቸውም እየተዝለፈለፉ ይወድቁ ነበር።*

ሰድሰት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ቀን ማረፍ፣ በጣም ጠቃሚ ነው። ራሳችንንም የሚጠቅም መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በሥራችን ያሉትን ሰዎች ያለአግባብ ጉልበታቸውን እንዳንበዘብዝ ያደርገናል። ዕረፍት ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። የቀድሞ የሃይማኖት መሪዎች ትልቁ ችግራቸው ሥራና ዕረፍት ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ነው ብለው ማሰባቸው ነው።

በመሠረቱ የሰንበት ቀን የደሰታ ቀን መሆን አለበት። በነብዩ ኢሳያስ ዘመን የነበሩት ሰዎች ሰንበትን ይመለከቱት የነበረው አንደ ከባድ ሸክም ስለነበረ፣ የሰንበት ቀን ቶሎ አልፎ ወደ ሥራቸው የሚመለሱበትን ጊዜ ይናፍቁ ነበር። በዚህ ምክንያት ኢሳያስ ሲነቅፋቸው፣ "እሻሮችህ ሰንበትን አንዳይሽሩ ብታሳርፍ በተቀደሰውም ቀን የልብህን ባታደርግ ሰንበትን ደስታ፣ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቀን የተከበረ ብለህ ብትጠራው በገዛ መንገድህ ከመሄድ፣ እንደ ፈቃድህ ከማድረግና ከከንቱ ንግግር ብትቆጠብ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል" ይላል (ኢሳ. 58፥13-14)። ሰንበትን የደሰታ ቀን ከማድረግ ይልቅ የህዘን ቀን አድርገው የሚወስዱት ሰዎች

አሉ። በሰንበት ቀን ሀዘንተኞች፣ ደስታ የሸሸን ሰዎች እንድንሆን የእግዚ አብሔር ፍላጎት አይደለም። ገንዘብ መሰብሰብ ደስታ የሚያገኙበት ሆኖ ሰባቱንም ቀን ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚነግዱት ሰዎች ደሰ አይለ ውም።

የሰንበት ቀን የዕረፍትና የአምልኮት ቀን በአንድ ላይ እንዴት መሆን ይችላል? ከአይሁድ ባህል የመጣ አንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሰ ይናገራል። አሰራኤላውያን በሰንበት ቀን ሰአግዚአብሔር መስዋዕት በማቅረብ ያመል ኩት ነበር። "በሰንበት ዕለት አንድ ዓመት የሆናቸውንና እንከን የማይገኝባ ቸውን ሁለት ተባዕት የበግ ጠቦቶች መስዋዕት ከመጠጥ ቁርጡንና በዘይት ከተለወሰ የሊፍ ሁለት ዐሥረኛ ልም ዱቄት ጋር አቅርቡ። ይህም ከመጠጥ ቁርባን ጋር በመደበኛነት ከሚቀርበው የሚቃጠል መስዋዕት ሌላ በየሰንበቱ የሚቀርብ የሚቃጠል መስዋዕት ነው" ይላል (ዘኁ.28፥9-10)። እንስሳዎ ችን ሰመስዋዕት ወደ መቅደስ ማምጣት፣ ማረድ መስውያው ላይ ማስቀ መጥ ሥራ ቢሆንም እንደ ሥራ አይቆጠርም ነበር። ስለዚህ የሰንበት ቀን ማንኛውንም ጉልበት የሚጠይቀውን ነገር አለማድረግ አይደለም። የመዝ ናናትና የመታደስ ጊዜ እንዲሆንልን ነው። በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ አርሱን ከማምለክ የበለጠ መታደስን የሚሰጥ ምን አለ? ቀጥሎም አይሁ ዳውያን በሰንበት ቀን ቅዳሜ በቤተ መቅደስ ተሰብስበው በጸሎትና ቃሉን በማንበብ አግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር።


ለክርስቲያኖችም የጌታ ቀን፣ ይኸውም የመጀመሪያውን ቀን ማለ ትም ዕሁድ ጌታን የሚያመልኩበት የሰንበት ቀን ሆነ። በሐዋርያት ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች በሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን፣ ይኸውም ዕሁድ ለአምልኮት መሰብሰብ ጀመሩ። የሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን የጌታ ቀን የሆነበት ምክንያት ኢየሱስ ከሞት የተነሳበት ቀን በመሆኑ ነው። የክርስ ቶስ ትንሳኤ ለክርስቲያኖች ዋና (መካከለኛ) በመሆኑ፣ ክርስቶስ ከሞት የተ ነሳበትን ቀን ለማክበር ክርስቲያኖች ለአምልኮት በአንድ ላይ ይሰበሰቡ ነበር። የክርስትና አምነት በሮማውያን ግዛት በተሰይ በባሪያዎች መካከል በፍጥነት ተስፋፍቶ ስለነበረ፣ ባሪያዎች ቅዳሜ አየሠሩ ዕሁድ አንዲያመ ልኩ ከሥራቸው ነጻ ይሆኑ ነበር። ቀስ በቀስ ዕሁድ የዕረፍትና የአምልኮት ቀን እየሆነ መጣ። አይሁዳውያን ያልሆኑ አማኞች ሰንበት "የአይሁዶች ልማድ" ነው ብለው ያሰቡ ስለነበረ በሰንበት ቀን ማረፍን ጠበቅ አድርገው አይዙትም ነበር። አንዲያውም አይሁድነት የሌላቸው አማኞች፣ አይሁ

ዶች በየሳምንቱ ማረፍ በመፈለጋቸው "ሰነፎች ናቸው" ይሏቸው ነበር። ኮንስታንታይን በነገሠበት ዘመን ዕሁድ የክርስቲያኖች የማረፍያና የአም ልኮት ቀን እንዲሆን አዋጅ አወጣ። ከዚህ አዋጅ በኋላ በሰንበት ቀን ማንም ሰው ሥራ አንዲሠራ አይገደድም ነበር።

ሥጋችን ዕረፍት፣ መንፈሳችን መነቃቃትና መታደስ አንደሚያስፈል ገው የሚያውቀው አምላክ ስድስት ቀን ሠርተን አንድ ቀን እንድናርፍ አስፈላጊ የሆነውን ሕግ ሰጠን። ሕጉንም የሰጠን ስለሚወደን እንጂ፣ ሊቀጣን ወይም ደስታችን የተሟላ እንዳይሆን ሰማድረግ፣ ወይም ሸክም አንዲሆንብን አይደለም። ክርስቶስ በምድር በነበረበት ዘመን የነበሩት ፈሪሳውያንና የሃይማኖት መሪዎች አንድ ሺ አምሰት መቶ ሕጎች ነበሯ ቸው። ከዚህ ውስጥ ሰላሳ ዘጠኞቹ ሥራን በሚመለከት ነገር ላይ ያወጧ ቸው ናቸው። እነዚህ ሕግ አጥባቂዎች የሚያወጧቸው ሕጎች ምን ያህል በሞኝነት የተሞሉ መሆናቸውን፣ ለሕዝቡ ሸክም እንደነበሩ ታሪካቸው ይመሰክራል።

ሰምሳሌ፥ ሪበን ወይም ስስ ጨርቅ ከለውየው ልብስ ጋር በእስፒል ቢያያዝ ያንን እንደ "ሸክም" ይቆጥሩታል። ነገር ግን ከልብሱ ጋር አብሮ ከተሰፋ ያ እንደሸክም አይቆጠርም። በዚህ ዓይነት በዘመናችን አርቲፊሻል ጥርስ ያሳቸው ሰዎች ሁሉ ሸክም ስለተሸከሙ የሰንበትን ሕግ ለፍርሰዋል ይባሉ ነበር።

አግዚአብሔር ለእኔና ለእናንተ ሕጎችን የሰጠን አንደ አግዚአብሔር ልጆች ነጻ ሆነን አንድንኖር፣ ከራሳችን ሞኝነት አንድንላቀቅ እንጂ ሸክም ሊያበዛብን አይደለም። አግዚአብሔር አኔና አናንተን የፈጠረን ያለሥራ ቁጭ ብለን እንድንኖር አይደለም። ሥራ ከሌለን ዓላማ ቢስነት ስለሚሰማን ለሳምና ደስታ የሸሸን እንሆናለን። በሌላ በኩል ደግሞ የዕረፍት ጊዜ ከሌ ለን፣ አምላካችንን የምናመልክበት፣ ስለ እርሱ ጸጋና ፍቅር የምናስብበት ጊዜ ካጣን፥ መሠረታዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፋችን ብቻ ሳይሆን፣ ሥጋዊውና መንፈሳዊው ሕይወታችን ጤና ያጣ ይሆናል። አራ ተኛው ሕግ ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት መኖር እንድንችል የሚረዳን ነው።



አምስተኛው ትዕዛዝ

ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ

"አባትህንና እናትህን አክብር፤
እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጠህ ምድር
ዕድሜህ እንዲረዝም።"
(ዘፀአት 20፥12)

በዓለም ውስጥ ወላጆቹን መርጠ የተወለደ እንድም ሰው የለም። ማናችንም ብንሆን ከእንዴት ዓይነት ወላጆች፣ የት አገር፣ መቼ መወለድ ትፈልጋላችሁ?" ተብለን ተጠይቀን በምርጫችን መሠረት አልተወለድንም። ምናልባት ይህን ዓይነት ምርጫ ቢሰጠን ኖሮ አንዳንዶቻችን እሁን ያሉንን ወላጆች እንመርጥም ይሆናል። እኛ ብቻ ሳንሆን፣ የእኛም ልጆች የመረጥ ዕድል ቢሰጣቸው ኖሮ እነርሱም አንዳንዶቻችንን እንደማይመርጡ እርግጠኞች ነን። ወላጆቻችንን አንምረጥ እንጂ ያለእግዚአብሔር

ፈቃድና ዕቅድ እንዲሁ፣ በወላጆቻችን የሥጋ ፈቃድ ብቻ የተወለድን አይደለንም።

- በዓለም ዙሪያ በሴኮንድ 3፥ በደቂቃ 180 ሕጻናት፣ በአንድ ሰዓት 10,900፥ በአንድ ቀን 259,200፥ በዓመት 95 ሚሊዮን ሕጻናት እንደሚወለዱ አኃዞች ይናገራሉ። "ብዙ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሏት" ስላለ፥ በልጆች መወለድ ደስ የሚላቸው ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርም ደስ ይሰኛል።

ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ዕቅድ የተፈጠረ ነው

በየቀኑ የሚወለዱ ሕጻናት ሁሉ በእግዚአብሔር ዕቅድ የተወለዱ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ይወቁትም አይወቁትም፣ ለሁሉም እግዚአብሔር ዓላማ አለው። በልተው፣ ጠጥተው፣ ወልደው ተዋልደው በዚህ ዓለም ውስጥ ለተወሰነ ዘመን ኖረው እንዲሞት ብቻ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለሆነም፣ በየዓመቱ ለሚወለዱት ለ95 ሚሊዮን ሕጻናት ሁሉ በጅምላ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ሕጻናት የት አገር እንደሚወለዱና እንደሚኖሩ፣ ከማን እንደሚወለዱ፣ መቼ እንደሚወለዱ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ሳይኖርበት አንዲሁ እንደ ድንገት ወይም እንደ አጋጣሚ የተፈጠረ አንድም ሰው የለም። ወደዚህ ዓለም መቼ መምጣት እንዳለብን ብቻ ሳይሆን፣ እኔና እናንተ እንወቀው እንጂ፣ ከዚህ ዓለም መቼ መሄድ እንዳለብን አስቀድሞ በእግዚአብሔር የታወቀና የተወሰነ ነው።

ሁላችንም በእግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ ወደዚህ ዓለም እንደመጣነው ሁሉ፣ ወላጆቻችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ እስቀድመው የተወሰኑ ናቸው። እግዚአብሔር የሕይወት ሁሉ ምንጭ ወይም መነሻ ሲሆን፣ ወላጆቻችንም እግዚአብሔር ሊሰጠን ለፈለገው ሕይወት ማስተላለፊያ መሣሪያ ወይም ምክንያት እድርጎ የተጠቀመባቸው ናቸው። በእናታችን ማህጸን ውስጥ ሆነንን፣ እናታችንን በሕይወት ሊያቆማት በሚችለው በራሷ ደም፣ በምትስበው ዓየር፣ ለራሷ በምትወስደው ምግብ ለእኛ በማካፈል አካላችን ዳብሮ እስክንወለድ ድረስ በሕይወት እንድታቆየን ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበለችን ናት። ከተወለድንም በኋላ ራሳችንን እስክንችል

ድረስ ወላጆቻችን ከእግዚአብሔር በተቀበሉት አደራ መሠረት አስፈላጊ ውን እንክብካቤ እንዲያደርጉ በእግዚአብሔር የተሰጠኑ ናቸው። ሕጻናት ሆነን እግዚአብሔር ጉዳት እንዳይደርስብን ስለሚፈልግ፣ ራሳችንን መጠበቅ እስክንችል ድረስ ከአደጋ እንዲጠብቁን ከእግዚአብሔር አደራውን የተቀበሉ ናቸው።

እንዲሁም በሕይወታችን ሙሉ ሥልጣን ያለው፣ የሞራል መመሪያ ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ይሁን እንጂ፣ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን የሞራል መመሪያ እኛ ልጆቻቸው በመልካም ጎዳና እንድንሄድ የሚመራንን መልካም መመሪያ የማስተላለፍም ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆቻችን ከእግዚአብሔር ከራሱ የመነጨውን የሕይወት መመሪያ ተከትለን እንድንሄድ፣ እንዲሁም ሕጉን ስንተላለፈ አስፈላጊውን ቅጣት ስጥተው የማሳደግ ኃላፊነት አለባቸው። ይህን የመሰለ ከፍተኛ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሰጣቸውን ወላጆቻችንን እንድናከብር ነው እግዚአብሔር አምስተኛውን ትዕዛዝ የሰጠን። ወላጆቻችንን እግዚአብሔር በሚያዘው መሠረት ለማክበር ፈቃደኞች ካልሆንን እግዚአብሔር በእነርሱ አማካኝነት ሊያስተላልፍልን የሚፈልገውን የሕይወት መመሪያ መቀበል አይሆንልንም። ጳውሎስ ኤፌሶን 6፥1-2 ላይ *"ልጆች ሆይ! ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ ተገቢ ነውና። አባትህንና እናትህን አክብር በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ፣ መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝምልህ..."* በማለት የሚያሳስበን ለዚህ ነው።

አምስተኛውን ትዕዛዝ ማክበር ብድራት አለው

እግዚአብሔር ራሱን እንደ አባት፣ አንዳንዴም እንደ እናት የሚገልጽበት ጊዜ እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናያለን። *"እናት ልጇን እሹሩሩ እንደምትል፣ እኔም እናንተን እሹሩሩ እላችኋለሁ"* ይላል (ኢሳይያስ 66፥13)። በተፈጥሮ ከወላጆቻችን ጋር ቅርበት ያለን ብቻ ሳንሆን፣ የሥጋቸው ቁራጭ፣ የአጥንታቸው ፍላጭ ነን። በአካላችን ውስጥ አካላቸው አለ፤ በደማችን ውስጥ ደማቸው አለ። እነርሱን አለማክበር፣ ራሳችንን አለማክበር ነው። እነርሱን ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ ራስን ዝቅ አድርጎ መመልከት ነው። ያልተማሩ ቢሆኑም፣ "ተምረናል" ያልነውን ወልደው ያስተማሩ ስለሆነ ሊከበሩ እንጂ ሊናቁ አይገባም። በመማሯ እናቷን ዝቅ

አድርግ በማየቷ ምክንያት የተበሳጨ እናት *"ምንም ብትማሪ፥ አትበልጭኝ..."* አሏት። በዓለም ውስጥ ከወላጆቻችን ጋር በጣም የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖረን እግዚአብሔር ያደረገው ስለሆነ፣ ወላጆቻችንን በሚመለከት አሳብ ላይ ፈጽሞ ችላ ልንለው የማይገባንን እምስተኛውን ትዕዛዝ እግዚአብሔር ሰጥቶናል። ይሄኛው ትዕዛዝ ከሌሎች የሚለይበት ሁለት ነገር የያዘ ሲሆን እንደኛው፣ ትዕዛዙ *"በአምንታ"* መቅረቡ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ትዕዛዙን ብንጠብቅ የምናገኘውን በረከት ጨምሮ የሚገልጽ መሆኑ ነው። *"አባትህንና እናትህን አክብር.."* ይልና፣ ይህን ትዕዛዝ ብትጠብቅ፣ *"...እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጠህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም"* ይላል።

እዚህ ትዕዛዝ ላይ ቁናው አሳብ፣ "አክብር" የሚለው ቃል ነው። ይህም ማለት በሕይወታችን ውስጥ ለወላጆቻችን ከሌሎች ሰዎች የበለጠ፣ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ከፍተኛውን ሥፍራ እንድንሰጣቸው የሚያመለክት ነው። ይህን እምስተኛውን ትዕዛዝ ዘሌዋውያን 19፥3 ላይ ሲደግመው፣ *"ከእናንተ እያንዳንዱ እናቱንና አባቱን ያክብር..."* ይላል። እዚህ ላይ ጸሀፊው የተጠቀመበት ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደሚሉት፣ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚጠቀሰውን ቃል ነው። ከላይ እንደጠቀስነው ከትዕዛዙ ውስጥ፣ ትዕዛዙን ብንጠብቅ የምናገኘውን በረከት የሚገልጽ ይሄ አምስተኛው ትዕዛዝ ብቻ ነው። ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች በላከው መልዕክት ላይ *"ልጆች ሆይ! ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ ተገቢ ነውና። አባትህንና እናትህን አክብር በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ፣ መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝምልህ..."* ይላል (ኤፌ. 6፥1-2)።

አክብር ማለት ምን ማለት ነው?

አምስተኛው ትዕዛዝ "የሥልጣን ተዋረድን" የሚያሳይ ነው። መጀመሪያ ወይም ከሁሉም በላይ ክብር የምንሰጠው ለእግዚአብሔር ሲሆን፣ ቀጥሎ ለወላጆቻችን ነው። "አክብር" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? እማርኛችንና የዕብራይስጥ ቋንቋ፣ ተቀራራቢ የሆኑ ወይም የሚመሳሰሉ ብዙ ቃላት አሏቸው።

- "አክብር" የሚለው ቃል "ካቨድ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የወጣ ሲሆን፥ አማርኛችን ደግሞ "ከባድ" የሚለው ነው። ይህ "ካቨድ" የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም፥ "ክብር" ማለት ነው። መሠረታዊ ትርጉሙ "ከባድ መሆን" ወይም "መከበድ" ማለት ነው። በዕብራይስጥ ባሕል እንዱን ሰው ማክበሩ ለዚያ ሰው ክብደት መስጠት፥ ልዩ አድርጎ መመልከት ማለት ነው።

ስለዚህ ወላጆቻችንን ስናከብር፣ በማቃለል ፈንታ ከማንኛውም ሰው የበለጠ ክብደት እንሰጣቸዋለን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ሲከበሩ እናያለን። ሊቀ ካህኑ ኤሊ ከእግዚአብሔር የበለጠ ልጆቹን አከ በራቸው ወይም ክብደት ሰጣቸው (1 ሳሙ. 2፥29)፥ ሳኦል ሙሴን፣ "...በሕዝቤ አለቆች ፊትና በእስራኤል ፊት አክብረኝ... "ሲለው "በሕዝቡ ዘንድ ቀልዱ እንዳልታይ ክብደት ስጠኝ" ማለቱ ነበር (1 ሳሙ. 15፥30)። በብሉይ ኪዳን ዘመን ወላጆቹን በማክበር፣ ወይም ለወላጆቹ ክብደት በመ ስጠት ፈንታ የሚያቃልል፣ ከፍተኛ ቅጣት ይደርስበት እንደነበረ መጽ ሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል። "አባቱን ወይንም እናቱን የሚሰድብ ይገ ደል" ይላል (ዘፀ. 21፥17)። ይሁን እንጂ፥ ማክበር ማለት "ማምለክ" ማለት አይደለም። እንውደዳቸው እንጂ አናምልካቸው። የምናመልከው አግዚአ ብሔርን ብቻ ነው። እነርሱን የምናመልክ ከሆን የመጀመሪያውን ትዕዛዝ በመጣሳችን፥ ቀኖተኛ የሆነውን አምላክ እናስቆጣዋለን። አንዳንዶች ወላ ጆቻቸውን በማክበር ፈንታ ከማምለክ ደረጃ የሚደርሱ እንዳሉ የታወቀ ነው። "ማክበር" መታዘዝን የሚጨምር ይሁን እንጂ ማክበር ማለት መታ ዘዝ ማለት አይደለም። በባሕሪያቸው፣ በያዙት ደረጃና ሥልጣን መሠረት ለሰዎች ክብርን እንሰጣለን። ለወላጆቻችን ደግሞ ከእግዚአብሔር በተሰጣ ቸው ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣ በሕይወታችን ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው፣ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ አስፈላጊውን ክብር እንድንሰጣ ቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል።

አንዳንድ ሰዎች ወላጆቻቸውን ማክበር የሚከብዳቸው ለምንድነው?

ይህንን አምስተኛውን ትዕዛዝ መቀበል እጅግ በጣም የሚከብዳቸው ሰዎች አሉ። እነርሱም፣ አጥጋቢ ይሁንም አይሁንም የራሳቸው የሆነ የተ ለያየ ምክንያት ያላቸው ናቸው። ስለ ወላጆቻቸው ሲያሰቡ፣ አንዳንዶች

በሁለቱም ወላጆቻቸው፣ አንዳንዶች ደግሞ በአባታቸው ወይም በእናታ ቸው ላይ ቅሬታ ያላቸው ናቸው። በልጅነታቸው ያለፉበት መጥፎ ትዝታ ወደ አዕምሯቸው እየመጣ፣ ዕንባ እየተናነቃቸው፥

- "...እንዲህ ዓይነቱን አባት ወይም እንዲህ ዓይነቷን እናት እንዴት ላክብር?" ይላሉ።
- እጅግ በጣም መራራ የሆኑት ደግሞ "እነርሱን ከማክበር፣ ሲያል መግባትን እመርጣለሁ" የሚሉ አሉ።
- "ወላጆቼ መንግሥተ ሰማይ የሚገቡ ከሆነ፣ ተመልሼ እነርሱን እንዳላያቸው መንግሥተ ሰማይ መሄድ አልፈልግም" ይላሉ።

አግዚአብሔር፣ ሕጻናት ከሁለት ወላጆች እንዲወለዱ ያደረገበት ምክ ንያት አለው። ፈጣሪው አርሱ ስለሆነ፣ ከአንድ ሰው ብቻ እንዲወለዱ ግድረግ ይችል ነበር። ልጆች እናት ብቻ ሳይሆን፣ አባትም ያስፈልጋቸ ዋል። አባት ብቻ ሳይሆን፣ እናትም ታስፈልጋቸዋለች። የሚያሳዝነው ግን ብዙ ያለአባት ወይም ያለ እናት የሚያድጉ ልጆች መኖራቸው ነው። ይህን ስንል እናትና አባት እቤት የሉም ወይም ሞተዋል ማለት ሳይሆን፥ የራሳቸውን ምኞት በመፈለግ ልጆቻቸውን ችላ ያሉ በመሆናቸው፣ እንደ ሌሉ ስለሚቆጠሩ ነው። እሽከር፣ ገረድ ያሳደጋቸው፣ የናታቸውንና የአባ ታቸውን ፍቅር ፈጽሞ ያላዩ ብዙዎች ናቸው።

- "አባቴ አቅፎኝ... እወድሃለሁ/እወድሻለሁ... ብሎ ያለኝን ጊዜ ፈጽሞ አላስታውስም፤ አባቴን የማስታውሰው ስሙ ሲጠራ፣ መጣ ሲባል የከረረኝን ድንጋጤዬን፣ ፍርሃቴንና መንቀጥቀጤን ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱን አባት እንዴት ላክብረው?" ብለው የሚጠይቁ አሉ።
- ራሳቸውን እንዲሁም የግል ምኞታቸውን መሰዋዕት ያደረጉትን፣ እነርሱ ተርበው ልጆቻቸውን ያበሉትን፣ እነርሱ ተራቁተው ልጆ ቻቸውን ያለብሱትን፣ እነርሱ ቆሻሻ ሰብሰው ልጆቻውን ግን ባማረ ልብስ ውበትን እየሰጡ ያሳደጉትን፣ እነርሱ ዕንቅልፍ እጥ ተው ልጆቻቸውን ምኞት ባለው አልጋ ያሰተኙትን፣ ሊሰጧቸው የሚችሉት ብዙ ቁሳቁሳዊ ነገር ባይኖራቸውም፣ ልጆቻቸውን

ፍቅር አጥግበው ያሳደጉትን ወላጆች ማክበር አስቸጋሪ እንዳል ሆነ ግልጽ ነው።

የሚያሳዝነው ግን ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ያሳደጓቸውን ወላጆች የሚረሱ ልጆች በተስይ በአሁኑ ጊዜ ቁጥር ሥፍር የላቸውም።

- *"ይህ ፣ምስተኛው ትዕዛዝ ባሁኑ ጊዜ አስፈላጊ አይደለም። ከረዜው ጋር የማይሄድ ነው። የራሴን ኑሮ ለማሸነፍ መሯሯጥ ሲገባኝ የራሳቸውን ኑሮ ኖረው ላበቁ ወላጆቼ የማሰብበትና የምጨነቅበት ጊዜ የለኝም። የራሳቸውን የሥጋ ፈቃድ ለመፈጸም ሲሉ ወለዱኝ እንጂ፣ ልወለድ ብዬ ለልጠየቅኋቸውም። እኔን ሲያሳድጉኝ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸው ነው። እኔም አድጌ ልጆች ሲኖሩኝ፣ ግዴታዬን መፈጸም ያለብኝ ለልጆቼ እንጂ፣ ለወላጆቼ ለይደለም፣ ለእነርሱ ኃላፊነት የለብኝም" ብለው በማሰብ የወላጆቻቸው መራብ፣ መቆሸሽ ፈጽሞ የማይሰማቸው" አሉ።*

እውነት ይሁን ተረት አላውቅም በልጅነቱ አንድ የለማሁት ታሪክ አለ። ልጁ ውጪ ወጥቶ ከልጆች ጋር ኳስ በመምታት፣ ብይ በመጫወት ፈንታ ሁልጊዜ ከቤቱ በራፍ ላይ ቆርቆሮ ሰብስቦ ሁልጊዜ ይቀጠቅጣል። በልጁ ሁኔታ በጣም የተደነቀው አባቱ አንድ ቀን፥ "ሁልጊዜ ስትቀጠቅጥ አይሃለሁ። ለመሆኑ ምን ዓይነት ዕቃ ልትሠራ ነው?" ብሎ ጠየቀው። ልጁም ጥቂት ካሰበ በኋላ "ልሠራ የምፈልገው ዕቃ የምግብ ሳህን ነው" አለው። አባትየው ጥያቄውን እዚህ ላይ ቢያበቃ ይሻለው ነበር። ይሁን እንጂ ቀጥሎ "የምግቡን ሳህን ምን ልታደርግበት ነው?" ብሎ ጠየቀው። ልጁም አሁንም ጥቂት ካሰበ በኋላ፥ "አባቴን ከውሾች ጋር ምግብ እንዳበላበት ነው" አለ። አባትየው በጣም ደነገጠ። የደነገጠው አንዲሁ አልነበረም። ያ ለው አባቱን ከውሾች ጋር የሚመግብ ለው በመሆኑ ነበር። ታሪኩ እውነትም ይሁን ተረት፥ ትልቅ ትምህርት የያዘ ነው።

ወላጆቹን ማክበር ያቃተው ሲራቡና ሲታረዙ ችላ የሚለው ልጅ፣ አንድ ቀን የዘራውን በራሱ ልጆች በኩል እንደሚያገኘው ግልጽ ነው።

ወላጆችን በሚመለከት ነጥብ ላይ ሁሉም የራሱ የሆነ የተለያየ ታሪክ አለው። አንድ ክርስቲያን ጸሀፊ "እናትና አባትህን አክብር..." ስለሚለው ስለ አምስተኛው ሕግ ሲገልጽ፣ ስለ አባቱ ያለውን የራሱን ልምምድ ይተ

ርካል። ይህ ሰው፣ በሥጋ የወለደውን አባቱን ስለማያውቅ፣ ማንነም "አባባ" ብሎ አላደገም። በስሙ ቢጠራም፣ ወይም "የእከሌ ልጅ" ቢባልም አባቱ በሕይወት መኖሩን እንጂ በዓይኑ ግን አይቶት አያውቅም። ሁልጊዜ አዕምሮው ውስጥ የሚመላለስ፣ መልስ ያላገኘለት ጥያቄ ነበረው። "የሥጋ አባቴ ማን ነው? ምን ይመስላል? የት ነው የሚኖረው? ለምን እኔና እናቴን ትቶ ሄደ? በሕይወት ካለ፣ ከእናቴ ጋር ተለያይተው ቢሆን እንኳን፣ እኔን ለማየት፣ እኔን ለመፈለግ ለምን ለልመጣም? አስከዚህ ድረስ የጠላኝ ለምንድነው? የእናቴና የአባቴ መለያየት ምክንያት እኔ አሆን?" የሚል ጥያቄና አሳብ ያስጨንቀው ነበር። ከብዙ ዓመት በኋላ፣ በሚስቱ እርዳታ አባቱን በመፈለግ ብዙ ከደከመና ከለፋ በኋላ አንድ ቀን በሥጋ የወለደውን አባቱን በዓይኑ የሚያይበት ቀን መጣ። እስቲ ታሪኩን ከራሱ ከታሪክኛው አፍ እንስማ።

"ከብዙ ድካምና ልፋት በኋላ፣ እርሱን ለመፈለግ ብዙ ገንዘብ ካወጣሁ በኋላ አንድ ቀን አባቴ ካለበት ሥፍራ ደረስኩ። ልቤ በኃይል እየመታ እኔና ሚስቴ በሩን አንኳኩተን ሲከፈትልን፣ ዓይኔ ከዚህ በፊት አይቶት የማያውቀውን ለው አየ። ለረጅም ጊዜ ለማየት የምመኘው፣ ከቤቱ በራፍ ላይ ፊት ለፊቴ የቆመው፣ ለውነቱ በጣም የጠወለገውና የተጨማደደው ሰው፣ በሥጋ የወለደኝ አባቴ መሆኑን አውቄ ለመጀመሪያ ጊዜ ትከ ብዬ አየሁት። ከዚህ በፊት ሌላው ቀርቶ ፎተግራፉን እንኳን አይቼ የማላውቀው ለው ነው። ከአርባ አምስት ዓመት በላይ በሀሳቤ ያ አባቴ የሚባለው ለው ማን ይሆን? አያልኩ የምጠይቀውን ለው ለመጀመሪያ ጊዜ በዓይኔ ዓየሁት።

በራፍ ላይ የቆምነውን እኔና ባለቤቴን፣ "ግቡ!" ብሎ ወደዚያች ጥበብ ቤቱ አስገባን። ማንነቴን አውቆ አቀፈኝና ዕንባውን አፈሰሰ። ፈጽሞ ስለ ማላውቀው ምን ብዬ እንደማጋግረው ግራ ተጋባሁ። ትንሽ ሰላምታ ከተ ለዋወጥን በኋላ፣ ስላለፈው ሕይወቱ ለመናገር ሞከረ። ግን የቤተሰቡ መፍረስና መለያየት ምክንያት በመሆኑ ጸጸቱን ለመደበቅ አልሞከረም። ዕንባ እየተናነቀው በጎረና ድምጹ፣ "ጊዜው የጦርነት ጊዜ ስለነበረ፣ የጦርነት ተልእኮዬ እንዳለቀ ወደ ሚስቴና ወደ ሕጻን ልጄ ተመለስኩ። ከተመለስኩ በኋላ ግን ሁኔታዎቹ እንደ ቀድሞው አልሆኑልኝም" አለ። ምን ማለቱ እንደሆነ ግን በሰፊው አልገለጸም። ዓይን ዓይኔን እያየም "እኔን ምንጊዜም

ይቅር ማለት እንደማትችል አውቃለሁ' አለኝ። እኔም "እርግጥ ነው ምንም አታውቀኝም" አልኩት።

"የሥጋ አባቴን ፈልጎ ማግኘት በሕይወቴ አንድ ያልተፈጸመ፣ ሁል ጊዜ የጎደሎነት ስሜት እንዲሰማኝ የሚያደርገኝ መሆኑን የተረዳችው ባለቤቴ በጣም ስለገፋፋችኝ ነበር አባቴን ፍለጋ ብዙ የደከምኩት። ይሄ የሲጋ አባቴ የተባለውን ሰው ፈልጌ በሕይወት ካለ፣ ሌላው ቢቀር ዓይኑን ትክ ብዬ ብቻ ማየት እመኝ ነበር። ሀሳቡ ከባለቤቴ የመጣ በመሆኑ፣ እር ሷም የጌታ ልጅ በመሆኗ፣ አባቴን ፈልጌ ማየት አለብኝ ብዬ ተነሳሳሁ። ከአርባ አምስት ዓመት በላይ ያሳየሁት 'አባት አለህ' ስባል እንጂ፣ የማላ ውቀው፣ ራሱን ከቤተሰቡ ያሸሸ፣ ጥሎኝ የጠፋ ሰው ቢሆንም፣ የሚያስደ ንቀው በውስጤ ምንም ዓይነት መራራነትና ቅሬታ በእርሱ ላይ ስላልነበ ረኝ፣ ይቅር ማለት ይሆን ያህል አላሰቸገረኝም። ይሁን እንጂ፣ ይሄ አባቴ ጥሩ ምክንያት ይኑረውም አይኑረው፣ ፈጽሞ ከሕይወቴ ያስወጣኝን፣ ፈጽሞ ያልፈለገኝን ሰው፣ "አባቴ" ብዬ እንዴት ላከብረውና ልቀበለው እች ላለሁ?" የሚል ጥያቄ በውስጡ አልፎ አልፎ ይመላለስ ነበር። ጌታ ግን ድል ሰጠኝና ወደድኩት፣ አከበርኩት" አለ።

እኛ ከወላጆቻችን ያላገኘነውን፥ ለትምሕርታችን እናውለው

አንዳንዶቻችሁ በተለይ ከወላጆቻችሁ ጋር ጥሩ ትዝታ፣ ጥሩ ልምምድ የሌላቸሁ፣ ወይም መጥፎ ትዝታ ያላችሁ አምሱትኛው ትዕዛዝ፣ *"አባትህ ንና እናትህን አክብር..."* በማለት በግልጽ ቢናገርም፣ በአግባቡ ያላሳደጉ ኝን ወላጆቼን እንዴት ወይም ስምን አከብራለሁ?" ብላችሁ የምትጠይቁ ትኖራላችሁ። ችግራችሁ 'እንዴት ላክብር' ሳይሆን፣ 'ለምን ላክብራቸው?' የሚል ይሆናል። ከላይ በአጭሩ ታሪኩን የገለጽነው ሰው፣ አባቱ ገና በሀ ጻንነት ዕድሜው እያለ ጥሎት በመሄዱ ሌሎች ልጆች ከአባታቸው ጋር ያላቸውን ቅርበት ባየ ቁጥር፣ እርሱ ግን ያለአባት ማደጉ ሲቆረቁረው፣ ልቡ በሃዘንና በባዶነት ስሜት ሲሞላ፣ በሚያስፈልገው ጊዜ ያልተገኘ ለት፣ ተስፋ ሲቆርጥ "አይዞህ!" ሲያዝንና መጽናናት ሲያስፈልገው፣ ያላ ጽናናውን አባት እንዴት ማክበር ቻለ" ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። ይሄ ሰው ገና በልጅነት ዕድሜው አባቱ ጥሎት በመጥፋቱ በውስጡ የሚ መላለሱ ብዙ ሀሳቦችና ጭንቀቶች እንደነበሩት አንጠራጠርም። ትልቅ

ልጅ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ፣ 'የማልወደድ፣ የተጠላሁ፣ ፈላጊ የሌለኝ ልጅ ነኝ' የሚል ስሜት ከውስጡ እንደነበረም አውንም አንጠራጠርም። ሌላው ቀርቶ፣ እናቱ ልጇ ጉዳቱ እንዳይሰማው፣ ያላየው አባቱ እንዳይና ፍቀው ብላ ይሆን ወይም ጥሏቸው በመጥፋቱ ምክንያት ራሷ አዝና፣ ልቧ መራራ ሆኖባት ይሆን አይታወቅም፣ ሌላው ቀርቶ የአባቱን ስም እንኳን አትጠራም ነበር። አባቱ ቤቱን ጥሎ የጠፋበት ምክንያት 'እኔ መጥፎ ልጅ ሆኜ ይሆን?" በማለት ራሱን እንዲጠላ የሆነበት ጊዜም ነበር።

እኔም አባቴ በልጅነቴ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ፣ ልጆች ከአባታ ቸው ሊያገኙት የሚገባቸውን መልካም ነገር አላገኘሁም። ድሌንም ሆነ ሽንፈቴን አላካፈልኩትም። የአባት ፍቅር ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም ፍቅሩ በተግባር ሲተረጎም፣ በእኔ ሕይወት ሲፈጸም አላየሁም። ጳውሎስ ለተሰሎ ንቄ አማኞች፣ *"አባት ለልጆቹ እንደሚያደርገው ወይነት እኛም ለእናንተ ለእያንዳንዳችሁ እንዳደረግንላችሁ ታውቃላችሁ፤ ዘወትር እየመከርናች ሁና እያበረታታናችሁ፣ መንግሥቱንና ክብሩን እንድትካፈሉ የጠራችሁ አምላክ ደስ በሚያሰኝበት ሁኔታ እንድትኖሩ አደራ እንዳልናችሁ ታውቃ ላችሁ"* ይላል (1 ተሰሎ. 2፥11-12)። አንዳንዶቻችን ጳውሎስ ከላይ የገለ ጸው ዓይነት አባት፣ ተሰፋ ሰንቆርጥ የሚያበረታታን፣ ስናዝን የሚያጽና ናን፣ ልንደርስበት ከምንችለው ከፍተኛ ደረጃ እንድንደርስ "አይዞህ! በርታ!" የሚለን አባት ቢኖረን እንዴት ደስ ባለን ነበር! ይሆን የመሰለ አባት አጠገባችን አለመኖሩ በሕይወታችን ትልቅ እጠት፣ ትልቅ ባዶነት እንደ ሚሰማን ግልጽ ነው።

ይሁን እንጂ፣ እኔ በበኩሌ ለራሴ ቁጭ ብዬ በማልቀስ ፈንታ፣ ጥሩ ትምህርት እንዲሆነኝ ተጠቅሜበታለሁ። ለልጆቼ ከላይ የገለጽነውን ዓይነት አባት ለመሆን ራሴን እንዳዘጋጅ ምክንያት ሆኖኛል። እኔ ያጣሁ ትን ልጆቼ እንዳያጡ፣ ራሴን ለልጆቼ ቅርብ ማድረግ እንዳለብኝ ተምሬ በታለሁ። አባቴ አጠገቤ መሆን ባይችልም፣ እኔ ግን ለልጆቼ አጠገባቸው ለመሆን እንድችል ትምህርት ሆኖኛል። ከአባት የሚመጣውን የማበረታ ቻና የማጽናኛ ቃል እየሰማሁ አላደግሁም። እኔ ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ለልጆቼ ብቻ ሳይሆን ዕርዳታዬን ለሚፈልጉ ሁሉ ማነቃቂያና ማጽናኛ እንድሆን መመሪያ ሆኖኛል።

ከላይ ታሪኩን የሰማነው ሰው፣ አባቱ በልጅነቱ ጥሎት በመጥፋቱ ምክ ንያት በችግር ውስጥ አልፋ ለብቻዋ ወይም ያለአባት ያሳደገችው እናቱ

ነች። እናቱን ሲያዩበት፣ *"አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጠህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም"* ስለሚለው ትዕዛዝ በልቡ ውስጥ የተሰማው ምን ዓይነት ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። *"ያሳደገችህን እናትህን አክብር፣ ያሳሳደገህን፣ ጥሎህ የጠፋውን አባትህን ግን አታክብር"* የሚል ትዕዛዝ ስላልሆነ፣ እናቱን ብቻ ሳይሆን፣ አባቱንም ጭምር ማክበር እንዳለበት የተረዳ ሰው ነበር። እናቱ በምድር የተመደቡላትን ዘመን ጨርሳ ስትሞት፣ በቀብሯ ሥነ ሥርዓት ላይ መልዕክቱን ያቀረበው እርሱ ስለነበረ፣ ስሜቱን ሲገልጽ እንዲህ አለ።

"የዛሬው ቀን በሕይወቴ ለእኔ ልዩ ቀን ነው፤ የእናቴን ውለታ፣ ለእኔ ያላትን ፍቅርና ስለ እኔ ስትል የከፈለችውን ከፍተኛ ዋጋ እያሰታወስኩ እርሷን የማከብር በት ቀን ስለሆነ፣ የዛሬው ቀን ለእኔ ልዩ ቀን ነው። ስለ እናቴ ብዙ ትዝታዎች አሉኝ። ለዕድገቴ የሚጠቅመኝን እትክልት፣ ሰላጣ አልበላም እያልኩ ስለማስቸግራት፣ እኔን ለማብላት የምትጠቀምባቸውን ዘዴዎች ምንጊዜም አልረሳም" አለ። እንደኛ ውን ሲጠቅስ እንዲህ አለ፥ "አልበላም እያልኩ አፌን ጥርቅም አድርጌ ስለምዘጋ አይሮፕላኑ እየበረ መጣ፤ ማረፊያ እየፈለገ ነው። እፍህን ከፈትና የሚያርፍበት ሰፍራ ስጠው ትለኛለች። እኔም እውነት መስሎኝ አፌን ስከፍት፣ በሹካ የያዘችውን ቅጠላ ቅጠል አፌ ውስጥ ትከተዋለች። እስከ ዛሬ ድረስ፣ የአይሮፕላን ድምጽ በሰ ማሁ ቁጥር እናቴ እኔን ለማብላት ታደርግ የነበረውን ጥረት አስታውሳለሁ" አለ።

ያ ሰው በቀብሯ ሥነ ሥርዓት ላይ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት ቆሞ ለእ ናቱ ያለውን አክብሮትና ፍቅር በመቀጠል እንዳንድ ትዝታዎቹን ሲጠ ቅስ እንዲህ አለ። "እግዚአብሔርን መከተል ምን እንደሆነ በሕይወቷ እየኖረች ያሳየችኝ እናቴ ናት። እናቴ በሕይወት በነበረችበት ወቅት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም የምትወደው አንድ ጥቅስ አላት። ለእኔም የምወደው ጥቅስ ሆነልኝ። በቀብሯ ሥርዓት ላይ ይህንን ጥቅስ ተጠቅሜበታለሁ። ጥቅሱም ኤርምያስ 6፥16 ላይ ያለው "እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ ይላል፤ 'በየጎዳናው ቆማችሁ ተመልከቱ፤ ጥንታዊና መልካም የሆነችው መንገድ የትኛው እንደ ሆነች ጠይቃችሁ ተረዱ፤ ባገኛችኋትም ጊዜ በእርሷ ሂዱ፤ በነፍሳችሁም ትኖራላችሁ" የሚለው ነው።

"እናቴ ከሞተች ከጥቂት ቀናት በኋላ፥ እንድ ቀን የተዘጋውን ቤቷን ከፍቼ ገባ ሁና ቁጭ ብዬ ዕቃዎቿን ማየት ጀመርኩ። የ5ና የ6 ዓመት ልጅ በነበርኩበት ጊዜ የሰበራትን መጥበሻ፣ የሚብ ማቅረቢያ ላሆኖቿ ጀበናዎቿ እንዳሉ ናቸው። የጥንቱን ዓይነት አምልኮቷን እወደው ነበር። 'በመዳኔ ጌታን አመሰግናለሁ፤ በደሙ ሰላነጸኝ ደስ ይለኛል" እያለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየተነሳች ሁልጊዜ የምትሰጠው ምስ

ክርነት ትዝ አለኝ። ከእናቴ ከተማርኳቸው ነገሮች ውስጥ ሕይወታችንን በእግዚአ ብሔር እጅ ላይ እደራ ብለን ከጣልን፣ ከጠበቅነው በላይ የተሻለ ሰው ሆነን እገ ኛለን የሚለውን የእምነት አቋሟን ነው። ጌታን በጣም የምትወድ እኔንም በጣም የምትወደኝ እናት ስለነበረኝ ዕድለኛ ነኝ። ለእኔ "አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግ ዚአብሔር አምላክህ በሚሰጠህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም" የሚለው አምስተኛ ውን ትዕዛዝ ለመቀበል አይከብደኝም አለ።

ስለ እናታቸው ብዙ መልካም ትዝታ የነበራቸው ብዙ ታላላቅ መንፈሳዊ አባት መጥተው አልፈዋል። ከእነርሱ መካከል እንደኛው ከዚህ በፊት ታሪ ኩን በሌላ ትምህርት ውስጥ እቅርቤ ታሪኩን የሰማችሁት ዲ. ኤል. ሙዲ ነው። የዲ. ኤል. ሙዲ እናት የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ታላላቅ ሰዎች ከአሜሪካ ዙሪያ የመጡ ተገኝተው ነበር። አንዳንዶቹ እየተነሱ ስለ ሙዲ እናት የሚሰማቸውን ከተናገሩ በኋላ፣ ሙዲ ጥቂት ቃል መናገር እፈልጋ ለሁ ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳ። እሬሳ ሳጥን ውስጥ የነበረችውን እናቱን እያየ፣

> "ውዷ እናቴ! በዓለም ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ የበለጠ ነገር ያደረግሽልኝ አንቺ ነሽ። ቀዥቃዣና የማልረባ ልጅ በነበርኩበት ዘመኔ ማንም በእኔ እምነት ባልነበረው ጊዜ አንቺ ግን ከፍተኛ እምነት ነበረሽ። በሄድኩበት ሁሉ ተከ ተልሽኝ፣ ጸለይሽልኝ፣ ፍቅርሽን አሳየሽኝ። ውዷ እናቴ! ከአንቺ ዕዳ በቀር የማንም ዕዳ የለብኝም" አለት።

እንዲህ ዓይነት እናቶች፣ ወይም አባቶች ያሏቸው "እናትህና አባትህን አክብር" የሚለው አምስተኛው ትዕዛዝ አይከብዳቸውም። ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ልጆች ሕግ፣ ወይም አስታዋሽ ያስፈልጋቸው ይሆን? የሚያስደ ንቀው ግን፣ ከፍተኛ ዋጋ ከፍለው፣ ፍቅር አጥግበው ወልደው ያሳደጓቸ ውን ወላጆች እንኳን ክብር ሊሰጧቸው ቀርቶ፣ መፈጠራቸውን እንኳን የሚረሱ አሉ። እጅግ በጣም ያሳዝናል። ተራርቀው የሚኖሩ፣ የልጆቻቸው ድምጽ የሚናፍቃቸው፣ በልጆቻቸው ፈጽሞ የተረሱትን ወላጆች ቤታ ቸው ይቁጠራቸው። ሌላው ቀርቶ በሠጻንነታቸው ጡጦ ወይም ጡት ሲያ ጠቧቸው ትን ብሏቸው ወላጆች የሚደነግጡት ድንጋጤ በገንዘብ ቢተ

መን ምን ያህል ዋጋ አንደሚያወጣ አስበን ይሆን? ያንን ሁሉ የሚረሱ ልጆች መኖራቸው ያሳዝናል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይሄ አምስተኛው ትዕዛዝ በጣም የሚከብድባ ቸው፣ ከወላጆቻቸው ጋር ጥሩ ልምምድ፣ ጥሩ ትዝታ የሌላቸው፣ "አንተ የማትረባ! ደደብ! የወንድ አልጫ!" አየተባሉ፣ ጥቂት ጥፋት በማጥፋታ ቸው ተዘቅዝቀው የተሰቀሉ፣ በርበሬ የታጠኑ፣ እንደ ወንበዴ፣ እንደ ወን ጀሰኛ በእግር ብረት የታሠሩ፣ ዛሬ ራሳቸውን የቻሉ ትልቅ ሰዎች ቢሆ ኑም፣ የአባታቸው ወይም የእናታቸው ስም ሲጠራ የሚደነግጡ፣ 'ዓይናች ውን ማየት አልፈልግም' ብለው ከወላጆቻቸው ሸሽተው የሚኖሩ እንዳሉ የታወቀ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ፣ "ይህ ትዕዛዝ ለእንደ እኔ ዓይነቱ ሰው አስቸጋሪ ነው። እኔን ወልደው ያሳደጉኝን ወላጆች ማክበር አልችልም። በልጅነቴ ወላጆቼ ያደረሱብኝ ጉዳት፣ የፈጸሙብኝ በደል ከልቤ ውስጥ ፈጽሞ ሊጠፋልኝ አይችልም። ይህን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ በጣም ከባድ ነው" ማለታቸው አይቀርም።

ይሁን እንጂ፣ ይህ ትዕዛዝ የተሰጠው ጥሩ ወላጆች ላሏቸው ብቻ ሳይ ሆን፣ በወላጆቻቸው እየተጎዱ ላደጉትም ጭምር ነው። እግዚአብሔር ክፉ ወላጆች ላሏቸው ልጆች፣ ልዩ አስተያየት አያደርግም። ይሄ ትዕዛዝ በእግ ዚአብሔር ዘንድ ከፍተኛ ሥፍራ እንዳለው የበለጠ እንድንረዳ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደገና እንዲጻፍ አደረገ። ጳውሎስ "*"ልጆች ሆይ! ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ ተገቢ ነውና። አባትህንና እናትህን አክብር በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝምልህ...*" ይላል (ኤፌ. 6፥1-2)። ይሄ ቃል ሁላችንንም ይመለከታል። ባለፈው ሕይወታችን ምንም ነገር ይድረስብን፣ እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጠው፣ ስላለፈው ሳይሆን በአሁኑ ወቅት ስላለው ሕይወታችን ነው። ሊለውጥ የሚፈልገው፣ ነገ የሚሆነውን ሳይሆን በአሁኑ ወቅት ያለንን ሕይወት ነው። ከልቡ ወላጆቹን ይቅር ማለት የሚችል ሰው፣ ለራሱ ልጆች የተመቸ፣ ከመራራነት ነጻ የሆነ ልብ ያለው፣ በራሱ ልጆች ዘንድ የተከበረ ወላጅ መሆን ይችላል።

ወላጆቹን የማያከብር ሰው የሚደርስበት ቅጣት

ወላጆቻቸውን ስለማያከብሩ ልጆች ምን ዓይነት ቅጣት መቀጣት እንዳ ለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ውስጥ ሁለቱን እንመለከ ታለን።

- 1ኛው/ ዘሌዋውያን 20፥9 ላይ *"አባቱን ወይም እናቱን የሚረግም ማንኛውም ሰው ይገደልI አባቱን ወይም እናቱን ረግሞአልና ደሙ በራሱ ላይ ነው"* የሚል ሲሆን፥
- 2ኛው/ ዘዳግም 21፥18-21 ላይ የተጠቀሰው ነው። *"አንድ ሰው የአ ባቱን ወይም የእናቱን ትእዛዝ የማይሰማ፣ ቢቀጡትም የማይታረም አልከኛና ዐመፀኛ ልጅ ቢኖረው፣ አባትና እናቱ ይዘው በሚኖሩበት ከተማ በር ወዳሉት አለቆች ያምጡትI ይህ ልጃችን አልከኛና ዐመ ጸኛ ነውI አይታዘዝንም፣ አባካኝና ሰካራም ነው ብለው ለአለቆች ይንገሯቸው። ከዚያም በኋላ የከተማዪቱ ሰዎች ሁሉ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩትI ክፉውንም ከመካከልህ አስወግድI እስራኤ ልም ሁሉ ይሆን ሰምቶ ይፈራል"* ይላል።

በዚህ ዓይነት እናትና አባትን ማዋረድ ወይም አለማክበር በእግዚ አብሔር ዓይን ከፍተኛ በደል መሆኑን እናያለን። በአዲስ ኪዳን ዘመን በወ ላጆቻቸው ላይ የሚያምጹ ልጆች በድንጋይ ተወግረው የሚሞቱ ቢሆኑ ኖሮ ምን ያህል ልጆች ያልቁ አንደነበረ መገመት አያስቸግረንም።

ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር ያለባቸው ለምን ይሆን? ብዙ ምክንያ ቶች አሉ። ወላጆች ስለልጆቻቸው ሲሉ ከፍተኛ ዋጋ ስለሚከፍሉ መከበር አለባቸው። ወላጆች በሕይወት ልምምዳቸው ያከበቱት ብዙ ጥበብና ማስ ተዋል ስላላቸው፣ ልጆች ወላጆቻቸው የሚሰጧቸውን ምክርና ሃሳብ ማክ በር አለባቸው። ሌላው እግዚአብሔር የሰጠውን አምስተኛውን ትዕዛዝ ማክበራቸው፣ እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኙት ነው። ይሄ ብቻ በቂ ምክንያት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"ልጆች ሆይ! ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር ታዘዙ"* ይላል (ቆሰ. 3፥2)። እንዲ ሁም ኤፌ 6፥1 ላይ *"ልጆች ሆይ! ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙI ይህ ተገቢ ናውና I 'አባትህንና እናትህን አክብር' በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም የሚል ነው"* (ኤፌ. 6፥1-3)።

አምስተኛውን ትዕዛዝ ተግባራዊ የምናደርገው እንዴት ነው?

ይሆን ስንል በልጆቻቸው ላይ ጉዳት ያደረሱትን ወላጆች እግዚአብሔር ችላ ይላቸዋል ማለት አይደለም። ወይም ምንም ያድርጉ ምንም፣ ግድ የለም ማለቱ አይደለም። ወላጆች ልጆቻቸውን በማሳደግ ላይ በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለባቸው። ማቴዎስ 16፥6 ላይ ጌታ ኢየሱስ *"...ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሰው፣ ክብድ የወ ፍጮ ድንጋይ በወንጩቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል"* ይላል። ልጆች በወላጆቻቸው ምክንያት የሚደርስባቸው ሥቃይና ጉዳት ይረዳል። እኛ ከሚገባን የበለጠ ቢረዳም፣ "አባትህንና እናትህን አክብር" ይለናል። ከዚህ ትዕዛዝ ራሳችንን ነጻ ማድረግ የማንችል ከሆነ፣ ትዕዛዙን ተግባራዊ የምናደርገው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

አምስተኛውን ትዕዛዝ ልጆች መጠበቅ ያለባቸው በወላጆቻቸው ቁጥጥር ውስጥ ባሉበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ራሳቸውን ችለው ከወጡም በኋላ ወላጆቻቸውን ማክበር አለባቸው። "እናትና አባትህን አክብር" ማለት "በሕይወታችሁ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራን ስጧቸው፣ እየወደዳችኋቸው የሚገባቸውን የክብር ስፍራ አትንፈጓቸው፣ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ፣ ራሳቸውን መርዳትና መደገፍ በማይችሉበት ጊዜም አስፈላጊውን ድጋፍ ስጧቸው" ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ *"የወለደህን አባትህን አድምጥ፣ እናትህንም ባረጀች ጊዜ አትናቃት"* ይላል (ምሳሌ 23፥22)። አንድ የጥንት ፀሀፊ ይህን ጥቅስ ሲያብራራ፥

> *"ልጄ ሆይ! በእርጅናው ዘመን አባትህን እርዳው፣ በመጨረሻ ዕድሜው ላይ ሳለ አታሳዝነው፣ ከእርጅና የተነሳ ራሱን መምራት በማይችልበት ጊዜም እንኳን፣ አንተ ብርቱና ጤነኛ በሆንክበት ጊዜ እዘንለት እንጂ አትናቀው"* ማለት ነው አለ።

በዚህ ትዕዛዝ መሠረት የሚኖሩ አማኞች ለወላጆቻቸው የሚያደርጉትን፣ የሚያሳዩት ክብር ከላይ ጸሀፊው እንደገለጸው ነው። በሰለጠነው ዓለም አብዛኛዎቹ ልጆች ለወላጆቻቸው የሚያሳዩዋቸው ፍቅር፣ የሚሰ

ጧቸው ክብር እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው። ወላጆች በእርጅና ምክንያት ራሳቸውን መርዳት ሲያቅታቸው፣ ሽማግሌዎች የመጨረሻ ዘመናቸውን ከሚያሳልፉበት ከጡረታ ቤት ተጥለው፣ በልጆቻቸው ሳይጎበኙ፣ ጠያቂ እጥተው፣ በብቸኝነት ማቀው፣ ልባቸው ተሰብሮና በሀዘን ተሞልተው የሚሞቱ ጥቂቶች አይደሉም። ይሄም የእግዚአብሔርን ልብ በጣም የሚያሳዝንና የሚሰብር ነው።

ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን ፈሪሳውያን በዕድሜ የገፉትን ወላጆቻቸውን ችላ ሲሉ አይቶ እንዲህ አላቸው። "እናንተስ ለወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለምን ትሽራላችሁ? እግዚአብሔር አባትህንና እናትህን አክብር በአባቱ ወይም በእናቱ ላይ ክፉ ቃል የሚናገር ይገደል ብሎ ሲያዝ፣ እናንተ ግን ማንም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ላደርግላችሁ የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ለእግዚአብሔር መባ አድርጌ አቅርቤአለሁ ቢላቸው፣ አንድ ሰው ይህን ካደረገ ዘንድ አባቱን ወይም እናቱን አክብሮ አል ትላላችሁ። ስለዚህ ለወጋችሁ ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ" አላቸው (የማቴ. 15፥3-6)። ፈሪሳውያን ወላጆቻቸውን በመርዳት ፈንታ በገንዘቡ ተጠቅመው፣ ለእግዚአብሔር ሰጥተናል ይላሉ።

ዛሬም እንዳንድ ክርስቲያኖች አሥራታቸውን ለቤተ ክርስቲያን በመስጠት ፈንታ፣ ሀሊናቸውን ለማጽዳት ሲሉ፣ እንዳንድ ሰዎች እንዳይታዘቧቸው ሲሉ ወላጆቻቸውን በአሥራት ገንዘብ የሚረዱ አሉ። በዚህ ዓይነት በሰዎች ዘንድ እንምስል እንጂ፣ እግዚአብሔርን ግን ልናታልለው አንችልምና የዘመኑ ፈሪሳውያን እንዳንሆን እንጠንቀቅ። ወላጆቻችንን የመርዳት ግዳጃችንን የምንፈጽመው የጌታን ገንዘብ በመስረቅ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እናድርግ። ይህንን የምናደርግ ከሆነ፣ በሁለቱም በኩል የሚገባንን በረከት የምናጣ መሆናችንን እንወቅ። እንደኛው፣ እሥራታችንን በታማኝነት በመስጠታችን የምናገኘው በረከት፣ ሁለተኛ፥ ወላጆቻችንን ተግባራዊ በሆነ መንገድ ማክበራችንን በመግለጽ የምናገኘውን ረጅም ዕድሜ እናጣለን።

አምስተኛውን ትዕዛዝ፣ ይኸውም "እናትህንና አባትህን አክብር" የሚለውን ትዕዛዝ መጠበቅ፥ አለመጠበቃችንን ራሳችንን መመርመር አለብን። ከእናትና ከአባታችን ጋር ያለን ግንኙነት፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር የሚያስጥ ነው? በአሁኑ ጊዜ በተለይ ልጆች ወላጆቻቸውን ለማክበር በጣም ከባድ ይሆንባቸዋል። የራሳቸው ፍልጎት ብዙ ስለሆነ፣

ከራሳቸው ምቾት ቀንሰው ደካማ ለሆኑ ወላጆቻቸው ማካፈል አይሆንላቸ ውም። የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላት ቀንና ሌሊት ስለሚሮጡ፣ እንኳን ሄደው ሊጠይቿቸው ቀርቶ ስልክ ደውለው እንኳን ማነጋገር አይሆንላቸ ውም። ስልክ በጮኸ ቁጥር፣ "...ልጄ ይሆን!... ልጄ ትሆን..." በማለት ልባቸው የሚጨነቅባቸው ወላጆች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። በእኩ ዘመን በባህላችን የተለመደውን ከብር ለወላጆች መስጠት ችላ እየተባለ የመጣ ይመስላል።

ለመሆኑ ወላጆቻችንን የምናከብረው እንዴት ነው? አንደኛው ከልባ ችን በጣም በመውደድ ነው። መውደዳችንም የሚታወቀው "እወዳችኋ ለሁ" በማለት በቃላት በመገለጽ ብቻ አይደለም። ፍቅራችንን የምንገልጽ በት መንገድ፣ በቂ ጊዜ ለንሰጣቸው ነው። አሜሪካን አገር አርጅተው ራሳ ቸውን መርዳት ሲያቅታቸው፣ ከሽማግሌዎች መጠሪያ ድርጅት ውስጥ ይገባሉ። የሚያሳዝነው አብዛኛዎቹ በልጆቻቸው ጊዜ ማጣት ምክንያት ጠያቂ አጥተው፣ በብቸኝነት ተሰቃይተው ይሞታሉ።

ቀደም ሲል ታሪኩን የሰማነው ሰው፣ ለእባቱ ያሳየው ፍቅር፣ እንዲ ሁም ያለአባት ላሳደገችው እናቱ ያሳየው ፍቅር ምን ዓይነት ይሆን? በማ ለት፣ እውነቱን ለማወቅ እንደምትጓጉ እገምታለሁ። ያላባት ላሳደገችው እናቱ በመጨረሻ ዕድሜዋ ላይ ያሳያት ፍቅርና እንክብካቤ ምን ዓይነት ይሆን? እስቲ ታሪኩን ከራሱ እንስማ።

"ስሙን ከመስማት በስተቀር አይቼው የማላውቀውን አባቴን ፍለጋ ብዙ ደክሞኩ፣ ብዙ ዋጋ ከፈልኩ። አንዳንድ ጊዜ ሥጋዬ ሲያይል፣ 'ፈጽሞ ያልፈለገኝ፣ ለረጅም ዘመን ጥሎኝ የሄደውን፣ ያላሳደገኝን አባት ብዬ ለምን እፈልጋለሁ? ያልኩበት ጊዜ ብዙ ነበር። እኔ የሚሰማኝን ከማድረግ ይልቅ እግዚአብሔር ከእኔ የሚጠብቀውን ማድረግ አለብኝ የምልበት ጊዜም ነበር። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር የሰጠኝን ትዕዛዝ መጠበቅ እንዳለብኝ ከውስጤ ይሰማኝ ነበር። ጌታን መታዘዝ የፈለግሁት በዮሐ. 14፥15 ላይ "ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ..." እንዲሁም በዮሐ. 15፥10 ላይ "እኔ የአባቴን ትእዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣ እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ..." ስለሚል ነው። አሥርቱ ትዕዛዛትን መጠበቅ ያለብን አንደኛውና ትልቁ ምክንያት ይሄ ነው። በፍ ቅሩ መኖር ከመረጠን ትእዛዙን መጠበቅ አለብን።

ንግግሩን በመቀጠል፣ "እናቴ ልትሞት ሁለት ዓመት ሲቀራት፣" ይላል፣ አንድ ቀን በሽተኞች ከሚያገግሙበት ጣቢያ ልጠይቃት ሄድኩ። የደረስኩት በምሳ ሰዓት ስለነበረ፣ ምሳዋን የማብላት ዕድል አጋጠመኝ። ምሳዋን እያጎረስኳት፣ በልጅነቴ እኔን ታጎርሰኝ የነበረው ትዝታ መጣብኝ። እናቴ የስኳር በሽታ ስለነበረባት ጣፋጭ ነገር እንድትበላ አይፈቀድላትም ነበር። ይሁን እንጂ፣ በዚያን ወቅት መብላት የምትፈልገው ጣፋጭ የሆነ ውን ነገር እንደ ኬክ ዓይነቱን ነበር። የቀረበላት ምግብ ልዩ ልዩ አትክ ልት፣ በተለይ እኔ የምጠላው ጎመን ወይም ስፒናች ነበር። 'እይሮፕላኑ ሊያርፍ ነው፣ አ! ብለሀ አፍህን ከፍተህ እስገባው' ትለኝ የነበረው ትዝ ብሎኝ፣ እኔም በተራዬ ምሳዋን ሳጎርሳት፣ ወደ ጎን ገፋ ያደረገችውን ስፒ ናች (ጎመን) በማንኪያ እንስቼ እየሳቅሁ፣ 'እማዬ! እይሮፕላኑ የሚያርፍ በትን ቦታ እየፈለገ ነውና አ! ብለሽ እስገቢው' እያልኩ የማትፈልገው ጎመን እበላት ነበር" አለ። በዚህ ዓይነት ለእናቱ አክብሮቱን በሚያሳያት ፍቅሩን ይገልጽ ነበር።

ወላጆቻችንን ማክበር፣ መውደድ ያለብን እንዳንዶቹ የሚገባቸው ሆነው ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመጠበቅና ለማክበር ነው። እኛንም እግዚአብሔር የወደደን እንዲሁ ነው እንጂ የሚወደድ ነገር ስላ ለን እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። ለው የዘራውን ያጭዳል የሚለው ሕግ የማያጠራጥር እውነት እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጸን ነበር። አልፎ አልፎ በዘነም ሆነ በደግ የምንዘራውን የምናጭድበት ጊዜ አለ። እዚህ ላይ እንድ ነገር መርሳት የሌለብን እውነት ቢኖር፣ ለወላጆቻችን በጎ አድርገን፣ ልጆ ቻችን ተመልሰው ለእኛ ሁልጊዜ በጎ ይሆኑልና ማለት እይደለም። ተቃራ ኒውን የምናገኝበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ በትክክል ጠብቀንበትና ኖረንበት ከሆነ፣ ብድራታችንን ከሰው ዘንድ ወይም ከልጆቻችን ባናገኝም፣ ካልጠበቅነው አቅጣጫ ልናገኘው እንደም ንችል ምን ጊዜም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። ከላይ ለትምህርታችን ምሳሌ እንዲሆነን ታሪኩን ያቀረብነው ለው፣ ያልፈለገውን አባቱን ፈልጎ ያገኘው፣ ያለአባት ያሳደገችውን እናቱን በአክብሮትና በፍቅር ተሞልቶ አሲታሞ የቀበራት ለው፣ እርሱ ራሱ ከልጆቹ ያገኘው አክብሮት ምን ዓይ ነት ይሆን? አሁንም ለማወቅ እንደምትጓጉ እምናለሁ።

እስቲ አሁንም ታሪኩን ከራሱ እንስማ። "ሃያኛውን የአገልግሎት ዘመ ኔን ለማክበር፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ልዩ ፕሮግራም እየተዘጋጀ


ነው። ጠቅላላውን ፕሮግራም የሚያቅደው የእኔ ተባባሪ (ረዳት) ፓስተር ነበር። ፕሮግራሙ ምን ዓይነት እንደሚሆን፣ እንግዳ ተናጋሪው ማን እን ደሚሆን አንድም ፍንጭ አልሰጠኝም። እከሌ ቢጋበዝ፣ እከሌ ተናጋሪ ቢሆን፣ የሴሚናሪ ፕሮፌሰሬን ዶክተር እከሌን ይጋብዝ ይሆን? ፓስተር እከሌን ይጠራ ይሆን? እያልኩ አንዳንድ በወቅቱ ታዋቂ የነበሩትን ሰባኪ ዎችንና አስተማሪዎችን በአዕምሮዬ አወጣና አወርድ ነበር። ተናጋሪውን ሳላውቅ በዓሉ የሚከበርበት ቀን ደረሰ። እኔና ባለቤቴ ታጅበን ከፊት ወን በር ላይ አስቀመጡን። የምሽቱን ፕሮግራም ተባባሪው ፓስተር በጸሎት ከፈተ። የአምልኮት ዝማሪ አንዳሰቀ፣ ተናጋሪው ማን ይሆን እያልኩ ሳስ ብና ስጨነቅ፣ ረዳቴ 'የዛሬውን መልዕክት የሚያቀርብልን፣ እከሌ ነው...' ብሎ የመጀመሪያውን ልጄን ስም ጠርቶ ተቀመጠ። ይህን ስሰማ መሬት ተስንጥቆ ቢውጠኝ ይቀለኝ ነበር። ምን ማድረጉ ነው ይሄ ሰውዬ ብዬ ጠየቅሁ። የእኔ ልጅ ተናጋሪ አይደለም። እንኳን በሁለት ሺ አምስት መቶ ሕዝብ መካከል መናገር ቀርቶ በአስር ሰውም ፊት መናገር ይችላል ብዬ አላምንም ነበር። አርግጥ ነው በዚህ ጊዜ የኮሌጅ ትምህርቱን ጨርሶ ተመርቋል። በሕዝብ ፊት ቆሞ ሲናገር ግን አይቼው አላውቅም። ይህን ዓይነት ሁኔታ ያጋጥመኛል ብዬ ፈጽሞ አልጠበቅሁም ነበር።

የምሽቱ ተናጋሪው የእኔ ልጅ መሆኑን የተሰበሰበው ሕዝብ ሲሰማ የሰው ሁሉ ዓይን በእኔና በባለቤቴ ላይ አረፈ። ደነገጥኩ፤ ሥሮቼ ተግተረ ተሩ። ላብ አጠለቀኝ። ወደ አዕምሮዬ መጀመሪያ የመጣው አሳብ፣ ይሄ ምክትሌ ምን ማድረጉ ነው? እኔ ደግሞ ስመናገር ምንም ተዘጋጅቼ አል መጣሁም አልኩ። ልጄም ስሙ ሲጠራ ፈገግ ብሎ ወደ መድረኩ ወጣ። የዕለቱ ታናጋሪ ሆኖ የቀረበውን ልጄን ሳይ፣ አጅቼን ፊቴ ላይ አድርጌ ግልቀስ ጀመርኩ። በዚያ ሕዝብ መካከል ቆሞ መናገር ይችላል ብዬ ፈጽሞ አልገመትኩም ነበር። ንግግሩን ሲጀምር እንዲህ አለ። 'ከብዙ ዓመት በፊት አባቴ አንድ ጥያቄ ጠይቆኝ ነበር። ጥያቄውም 'የእኔ ልጅ በመሆንህ ትኮራለህ? ፓስተር በመሆኔ ታፍርብኛለህ?' የሚል ጥያቄ ነበር። ለዚህ ጥያቄ ምን ዓይነት መልስ እንደምሰጥ ግራ ስለተጋባሁ፣ በወቅቱ "አዎን!" ወይም "አይደለም" የሚል መልስ ሳልሰጠው አለፍኩት። የመጋ ቢው ልጅ በመሆኑ፣ አባቴ ሲያስተምር (ሲሰብክ) ብዙ ጊዜ አንደ ምላሌ ስለሚጠቅሰው፣ ከሰንበት ትምህርት ክፍል ሲወጣ ጓደኞቹ 'ዛሬም አባትህ ስለ አንተ ተናገረ" በማለት ይስቁበት አንደነበረ ገለጸ። ልጄም፣ ያኔ አባቴ

የእኔን ስም አየጠራ የሚናገረው ታሪክ እንደ ነበረው ሁሉ፣ ዛሬም እኔ ስለ አባቴ የምናገረው የራሴ ታሪክ አለኝ" በማለት ብዙ ታሪኮች ስለ እኔና ስለ አናቱ እየጠቀሰ አወራ።

የሃያ አምስት ደቂቃ መልዕክቱን ሲያጠቃልል፣ ሞጨረሻ ላይ "እኔ በወላጆቼ የምኮራውን ያህል፣ ሌሎች ልጆች በወላጆቻቸው ይኮራሉ ብዬ አላምንም። ይህን የምሰው እኔ ብቻ ሳልሆን ታናሽ ወንድሜም ነው። የዚህ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ከመሆን የበለጠ ትልቅ ነገር ስለሌለ፣ ወላ ጆቼ ሌላ ነገር ሲሠሩ ማየት አልፈልግም" አለ። ወደ እኔና ወደ እናቱ ዞር ብሎ "አማዬና አባዬ! ስለ ወደዳችሁን፣ እኔና ወንድሜ የምንኮራባችሁ ወላ ጆች ስለሆናችሁልን እናመሰግናችኋለን። አማማና አባባ! በጣም በጣም አንወዳችኋለሁ" በማለት በሁለት ሺ አምስት መቶ ሕዝብ ፊት ቆሞ ፍቅ ሩን በመግለጽ አከበረን። ይሄን የልጄን ንግግር የሰማሁበት ቀን፣ በሕይ ወቴ ከፍተኛውን ሥፍራ የምሰጠው ቀን ነው። ለእኔ ከዚህ የበለጠ ወይም የተሻለ አናትና አባት የማክበር ሌላ መንገድ የለም። ይህን ዓይነቱን ቃል መስማት ነው ለወላጆች እስክ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ ጉልበት የሚ ሆናቸው" አለ። እንዴት የሚያስደንቅ ታሪክ ነው?

"አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር እምላክህ በሚሰጠህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም" የሚለው አምስተኛው ትዕዛዝ በብሉይ ኪዳን ዘመን ላሉት ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዘመን ላለነው ክርስቲያኖችም የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ በትዕዛዙ መሠረት እንኑር።



ስድስተኛው ትዕዛዝ

ነፍሰ ገዳይ አትሁኑ

"አትግደል" (ዘፀአት 20፥13)

"ከአስርቱ ትዕዛዛት ውስጥ አወዛጋቢ ወይም አከራካሪ ነው የሚባለው ትዕዛዝ የትኛው ይሆን?" ብለን ብንጠይቅ የተለያየ መልስ ማግኘታችን አይቀርም። የአከራካሪነቱ መጠኑ እንደየሰዉ ይልያይ እንጂ፥ አሥሩም ትዕዛዛት አካራካሪዎች ናቸው። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ይኸ ውም "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑርሆ" የሚለው ትዕዛዝ ለምን አስፈለገ? በማለት ትእዛዙን መቀበልና መታዘዝ የሚያቅታቸው ይኖራሉ። ለአንዳንዶቹ ደግሞ አራተኛውን ትዕዛዝ ይኸውም፣ "የሰንበትን ቀን ትቀ ድሰው ዘንድ አስብI ስድስት ቀን ሥራI ተሣርሆንም ሁሉ አድርግI ሰባ ተኛው ቀን ግን ለአምላክህ ለእዝአብሔር ሰንበት ነው.." የሚለው ትዕዛዝ ሰው ሰንፍናን እንዲለማመድ፣ ሥራ እንዲሸሽ ያደርገዋል ብለው ሰለሚያ

ምኑ አስፈላጊነቱን መቀበል፣ እንደ ትእዛዙ መኖር የሚያቅታቸው ይኖ ራሉ። ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ደስ የሚላቸው ሰዎች ደግሞ፣ "በሁለቱም ወገን በስምምነት እስክ ተደረገ ድረስ፣ ደስታን የምናገኝበት ከሆነ፣ ማንንም ሰው ካልጎዳን ለምን እንከለከላለን?" በማለት "አታመንዝር" የሚለውን ሰባተኛውን ትዕዛዝ መቀበልና እንደ ትእዛዙ መኖር የሚያቅታቸው፣ እግዚአብሔር ደስ እንዳይለን ብሎ ያወጣው ሕግ ነው ብለው የሚያምኑ ይኖራሉ። "አትግደል" የሚለውን ሰድስተኛውን ትዕዛዝ ግን በየትኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ፣ የሰው ነፍስ ማጥፋት ትክ ክል እይደለም ብለው ስለሚያምኑ፣ ትእዛዙ ብዙዎችን ቅር ላያሰኝ ይች ላል። ይሁን እንጂ ይህንንም ትዕዛዝ ጠለቅ ብለን ስንመረምር፣ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ "መግደል" ምን እንደሆነና እንዲሁም ምንን እንደሚ ያጠቃልል የሰጠውን ገለጻ ስንረዳ፣ ይሔም ትዕዛዝ ብዙዎችን የሚያከራ ከር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በብዙዎች ዘንድ ትዕዛዙ ሲጣስ እናያለን።

የመግደል ዓይነቶች

"አትግደል" የሚለው ትዕዛዝ በእማርኛችን እንድ ቃል ብቻ ነው። "አትግደል" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ግን "ሎ ራትዛክ" ሲሆን፣ ሁለት ቃላት የያዘ እንደሆነ እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ "አትግደል" ሲል የትኛ ውን ዓይነት መግደል ማለቱ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። "መግ ደል" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ከላይ ያየነው "ሎ ራትዛክ" ብቻ አይደ ለም። "መግደል" በስምንት የተለያዩ ቃላት እንደሚገለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይጠቁማሉ። ከላይ የለማነው፣ "ሎ ራትዛክ" የሚለው ቃል፣ እን ዲሁ የተጠቀሰ ሳይሆን፣ የትኛውን ዓይነት መግደል እንደሆነ በደንብ ታስ በት የተጻፈ ነው።

በጦርነት ውስጥ ጠላትን ተኩሶ መግደልን ለመግለጽ ሌላ የዕብራይስጥ ቃል ይጠቀማሉ እንጂ "ሎ ራትዛክ" የሚለውን ቃል እይጠቀሙበትም።

- እንሰላትን አድኖ መገደልን ሲገልጹ ደግሞ ሌላ ቃል እንጂ "ሎ ራትዛክ" የሚለውን ቃል አይጠቀሙም። በዚህ ዓይነት ገለጻ "አትግደል" የሚልው ትዕዛዝ ማንኛውንም ዓይነት መግደል ሳይ ሆን፣ ሰውን ያለአግባብ ወይም ትክክል ባልሆነው ዓይነት መግ ደል ነው የሚሉና የሚከራከሩ አሉ። ሆን ብሎ አስቦ፣ "ጠላቴ

ነው" ብሎ መግደል ሕጋዊ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ አገዳደል ስለሆነ፣ "ሎ ራትዛክ" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ይጠቀማሉ።

- የሰው ነፍስ አጥፍቶ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት ቢወሰንበትና ቢገ ደል፣ ሕጋዊ የሆነ የሞት ቅጣት ስለሆነ፣ "ሎ ራትዛክ" የሚለውን ቃል አይጠቀመባትም።
- አንድ ሰው ሆን ብሎ፣ ወይም አስቦ ሳይሆን በስህተት ሌላውን ቢገድል፣ "አትግደል" (ሎ ራትዛክ) የሚሰው ትዕዛዝን መጣሱ እንደሆነ አይቆጠርበትም። ስለዚህ "አትግደል" የሚለው ሰድስተኛው ሕግ፣ በቁጣ ወይም በደም ፍላት ተነሳስቶ ንጹህ ደም ማፍሰስ ብቻ ነው ይላሉ።

ለመሆኑ "መግደል" የሚለው አሳብ ከላይ የገለጽነው ዓይነት ብቻ ነው ወይ? በእናታቸው ማህጸን ያሉትን፣ ገና ያልተወለዱትን ሕጻናት በውርጃ ማስወጣት ያ ነፍስ መግደል አይደለም ወይ? "ነው... አይደለም..." የሚሉ አሉ። አንድ ጊዜ የህክምና ትምህርት ተማሪዎች፣ ስለ "ጽንስ ማስወረድ" (አቦርሽን) የሚሰጠውን ሴሚናር ይከታተሉ ነበር። ሴሚናሩን የሚመራው ፕሮፌሰር፣ ስለ አንድ ቤተሰብ አውነት ላይ የተመሠረተ ታሪክ እንዲህ ሲል አቀረበላቸው። "የቤተሰቡ መሪ (አባትየው) የአባለ ዘር በሽታ (ቂጥኝ) ያሰበት ሰው ነበር። እናትየው ደግሞ የሳንባ ነቀርሳ ሕመምተኛ ነበረች። የመጀመሪያው ልጃቸው ሲወለድ ዓይነ ስውር ሆኖ ተወለደ። ሁለተኛው ልጃቸው እንደተወለደ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሞተ። ሦስተኛው ልጃቸው ደንቆሮና ዲዳ ሆኖ ተወለደ። አራተኛ ልጃቸው ደግሞ ልክ እንደ እናቱ የሳንባ ነቀርሳ ሕመምተኛ ሆነ። እናትየው 5ኛውን ልጃቸውን አርግዛ ሰመውለድ ተቃርባለች። ለዚህች ሴት የምትሰጪት ምክር፣ ለምትወስነው ውሳኔ፣ ሰምታደርገው ምርጫ ከፍተኛ ወሳኝነት ያለው ነው። ያረዝች ውን ጽንስ እንድታስወርድ የምትመክሯት ከሆነ ጽንሱን ለማስወረድ ዝግጁ ነች። ለመሆኑ ለዚህች ምስኪን ሴት ምን ዓይነት ምክር ትሰጪታ ላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። ተማሪዎቹ ሁሉም በአንድ ድምጽ፣ "ጽንሱን እንድታስወርድ እንመክራታለን" አሉ። አስተማሪው መልሳቸውን ከነምክ ንያታቸው በጥሞና ካዳመጠ በኋላ፣ "እንኳን ደስ አላችሁ፣ እናንተ ከእናቱ ማህጸን አውጥታችሁ እንዲጠፋ ወይም እንዲሞት የፈረዳችሁበት ያ ህጻን ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በመዘቃ ችሎታው ዓለም ያደነቀው የታወ

ቀው <u>ቤት ሆቨን</u> ነው" አላቸው። ያ ህጻን በእናቱ ማህጸን እንዳለ ቢገደል ኖሮ ዓለም ቤትሆቨንን የመሰለ ታላቅ የኪነ ጥበብ ሰው ታጣ ነበር አላቸው።"

በዚህ ዓይነት ቤት ሆቨንን የመሰሉ ታላላቅ ሰዎች ስንቶቹ በእናታ ቸው ማህጸን እያሉ ተገድለው ይሆን? በ1944 ዓ.ም (ኢ.አ.አ.) አንዲት የአርባ አንድ ዓመት ሴት ያረገዘችውን ጽንስ በውርጃ አንዲያስወጣላት ህኪሟን ለመነችው። ሐኪሟ ግን ጽንስን ማስወረድ ሕጋዊነት የለውም፤ በሞራል ወይም በሥነ ምግባር አቋምም ትክክል አይደለም" በማለት "አምቢ!" አላት። ምርጫ ስላልነበራት ዘጠኝ ወር አርግዛ ጊዜውን ጠብቃ ያ ሕጻን ተወለደ። ያ በእናቱ ያልተፈለገው ሕጻን ማን እንደሆነ ታውቃ ላችሁ? በዘመኑ ዓለም ያደነቀው ወንጌላዊው ጀምስ ሮብንስ ነው። ያ እናቱ እንዲወለድ ያልፈለገችው ሕጻን ልጅ አድጎ ብዙዎችን ወደ አግዚአ ብሔር መንግሥት የጠራ ታዋቂ ወንጌላዊ ሆነ። ለያንዳንዱ ሰው፣ ሌላው ቀርቶ በወላጆቻቸው ለማይፈለጉት ሕጻናትም እንኳን ቢሆን እግዚአብ ሔር ዓላማ ወይም ዕቅድ አለው። በዚህ ዓይነት በአሜሪካ ውስጥ ብቻ በዓመት አንድ ሚሊዮን ሕጻናት በእናታቸው ማህጸን አያሉ የሚገደሉ መሆናቸውን እናውቅ ይሆን?

አንድ የማህጸን ህኪም፣ ሕይወት ኖሮት በማደግ ላይ ያለውን ጽንስ ቢያስወርድ፣ ድርጊቱ እንደ ነፍስ መግደል ወይም ሕይወት እንደ ማጥ ፋት ሆኖ ይቆጠርበታል? ህኪም "በፍጹም አይተርፍም የተባለውን በሽ ተኛ፣ እየተሰቃየ ከመኖር ይልቅ ሞት ይሻለዋል" ብሎ እንዲሞት ቢረ ዳው እንደ ነፍስ ገዳይ ያስቆጥረዋል?" ሕይወት የሚጀምረውና የሚያበ ቃው መቼ ነው? በማለት ምሁራን ለረጅም ጊዜ ቢከራከሩበትም፣ በአንድ አሳብ ላይ መስማማት እንዳልቻሉ የታወቀ ነው። "አትግደል" የሚለው ስድስተኛው ሕግ ቀላል፣ ግልጽና ቀጥተኛ ቢሆንም፣ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ግን የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደሚፈጥር የታወቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን ዓይነት ነፍስ መግደል ፈቅዶ፣ ሌላውን ዓይነት ነፍስ ማጥ ፋት ግን ይከለክል ይሆን? የተፈቀደውና የተከለከለው የትኛው ነው? የሰው ነፍስ ያጠፋውን ወንጀለኛ በሞት ፍርድ መቅጣት "አትግደል" የሚ ለውን ስድስተኛውን ትዕዛዝ መጣስ ይሆን? ራስን ከወራሪ ለመጠበቅና ለመከላከል ጦርነት ውስጥ ገብቶ ጠላትን መግደል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ? በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ አከራካሪ አስተያየቶች እንዳሉ የታወቀ ነው። የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ ለነዚህና አነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎች መልስ

ለመስጣት እንዳልሆነ በቅድሚያ መግለጽ እንወዳለን። ትምህርታችን በጅምላ ያለንን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ለመጨመር ሳይሆን፣ የግል መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚመለከተውን ለመረዳት ነው። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በግል ሕይወታችን "እትግደል" የሚለውን ስድስተኛውን ትዕዛዝ እየጣስን ይሆን? የምንጥሰውስ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? የትምህርታችን ዋና ዓላማ ላለን የሥነ መለኮት ጥያቄ መልስ ለመፈለግ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያበላሽብን መንፈሳዊ ድካማችንን ማየት እንድንችል ነው።

"ሕይወትን" የሚሰጥም ሆነ የሚወስድ እግዚአብሔር ብቻ ነው

ለጥቂት ደቂቃ "ሞት... መግደል..." የሚለውን አባብ ወደ ጎን እናድርገውና "ሕይወት" በሚለው አባብ ላይ ትኩረት እናድርግ። መጽሐፍ ቅዱስ "ሕይወት" የሚለው አባብ በሁለት መሠረታዊ እውነት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይገልጻል። ይኸውም፣ እንደኛው ሕይወት ለጪ፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜና ሰዓት የሰጠውን ሕይወት መልሶ የመውሰድ ሙሉ ሥልጣንም ሆነ ኃይል ያለው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ኢዮብ በመከራው መካከል የሰውን የሕይወት ዘመን ምን ያህል መሆን እንዳለበት ወሳኙ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ሲገልጽ፣ *"የሰው ዕድሜ አስቀድሞ የተወሰነ ነው፤ የወራቱንም ብዛት ወስነህ አስቀምጠሃል፤ ሊያልፈው የማይችለውንም ገደብ አኖርህለት"* ይላል (ኢዮብ 14፥5)። እንዲሁም ዘማሪው *"...እስትንፋሳቸውንም ስትወስድባቸው ይሞታሉ፤ ወደ ዐፈራቸውም ይመለሳሉ፤ መንፈስህን ስትልክ ይፈጠራሉ፤ የምድርንም ገጽ ታድሳለህ"* ይላል (መዝ. 104፥29)። *"ሕይወት"* ለሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠው ታላቅ ስጦታ በመሆኑ፣ ሰው እንዲጠብቀው በአደራ ተሰጠው እንጂ ከራሱ የተገኘ አይደለም። አቤል፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሕይወት፣ ወንድሙ ቃየል ያለአግባብ ሲያጠፋበት፣ ደሙ ወደ ፈጣሪው፣ ወደ እግዚአብሔር እንደ ጮኸ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ሁለተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት፣ እግዚአብሔር ለውን በራሱ አምሳል የፈጠረ መሆኑን ይገልጻል። ይሄም ሰውን ከሌሎች እንስሳት የተለየ የሚያደርገው አንደኛውና ዋናው ነው። ጀምስ ዋትሰን የተባለው

ታዋቂ ሰባኪ፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የሰውን ሕይወት ማጥፋት ጥልቀቱን ሲገልጽ፥

> "የሰውን ሕይወት ማጥፋት፣ የእግዚአብሔርን ምስል (ፎቶ ግራፍ) ቀዶ እንደመጣል ነው" አለ።

ለሰው ልጅ "ሕይወት" ከእግዚአብሔር የተሰጠው፣ እንደ መልካም ባለአደራ ሆኖ እንዲጠብቀው ነው። ከላይ የገለጽናቸው እነዚህ ሁለት እውነቶች፣ የሰው ሁሉ ሕይወት ምን ያህል ጥንቃቄ ሊደረግለት እንደሚገባ የሚያመለክቱ ናቸው። "ጠላታችን ነው" የምንለው ለው ሕይወት፣ እኛ ካለን ሕይወት የተለየ ሳይሆን ከእኛ ጋር እኩል ወይም አንድ ዓይነት ስለሆነ፣ ልንገድለው (ልናጠፋው) መብት ወይም ሥልጣን የለንም። በጠላት ወገን ሆኖ የሚዋጋው ወታደርም ያለው ሕይወት፣ የእኛኑ ዓይነት ሕይወት ስለሆነ፣ ሕይወቱን ዋጋ ቢስ ወይም የማይረባ አድርገን እንድናየው አይገባም። በማይድን በሽታ ተይዞ ቀስ በቀስ እንጎሉ እየደከመ ሊሄድ የሚታየው ለው ያለው ሕይወት፣ የላቀ አዕምሮ ኖሮት የአንጎል ቀዶ ጥገና ህኪም ከሆነው ለው ሕይወት ጋር ማወዳደር ወይም ማበላለጥ እንችልም። <u>በእግዚአብሔር ዘንድ የሁለቱም ሕይወት እኩል ነው።</u> "ይሄኛው ይሙት፣ ያኛው ይዳን" ማለት እንችልም። ስለዚህ "አትግደል" የሚለው ሰድስተኛው ትዕዛዝ፣ ማንኛውንም ዓይነት ለው "መግደል" እንደሌለ ብን ያሳየናል።

የሰው ልጅ በኃጢአቱ ምን ያህል እንደ ወደቀ፣ እንዲሁም ሕይወቱ ምን ያህል የተበላሸ እንደሆነ፣ ሁሉን ማወቅ ከሚችለው አምላክ ፊት የተደበቀ ወይም የተሰወረ እይደለም። ደሙን አፍሰን የምንገድለውን ብቻ ሳይሆን፣ ደሙ ሳይታይ ቀስ በቀስ የምንገድለውንም ለው ያያል። ዓለም፣ አሁንም ሆነ ጥንት በእመጽ ምክንያት ከምን ዓይነት አስከፊ ወይም አሳዛኝ አቋም ላይ እንዳለች ያውቃል። በጥላቻ ምክንያት በየቀኑ በዓለም የሚፈጸመውን ደም መፋሰስ ወይም ግድያ፣ የእርስ በርስ መተላለቅን በዜና ማሰራጫዎች ስንሰማ ብዙዎቻችን የሚሰቀጥጠን መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ ለእኔና ለእናንተ አዲስ ዜና ይሁንብን እንጂ፣ ሁሉን ለሚያውቀው እግዚአብሔር ግን ይህን ያህል አዲስ ነገር አይደለም። የዛሬውን ብቻ ሳይሆን፣ በነገው ቀን ምን ዓይነት ዜና እንደሚቀርብም አስቀድሞ ያውቃል። ለእርሱ አዲስ የሚሆን ምንም ዓይነት ዜና አይኖርም። ከአስር ሺ ዓመት በኋላ የሚሆነውን አስቀድሞ ያውቃል።

በምድረ ገነት እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው፣ አዳምን "...ያደረግኸው ምንድነው?" ብሎ ሲጠይቀው፣ በወቅቱ አዳም ያደረገውን ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ፊት ዓለም በሰው ኃጢአት ምክንያት ምን ያህል የከፋች እንደምትሆን ያውቃል። ኃጢአቷንና ክፋቷን ብቻ ሳይሆን፣ ከመጠን በላይ የተበላሸችውን ዓለም ከበደሏ ለማንጻት ምን ያህል ዋጋ እርሱን እን ደሚያስከፍለው ወይም እንደሚጠይቀው አስቀድሞ አውቋል።

በአንድ ወቅት፣ በዓለም ውስጥ የሰዎች ልጆች ክፋት እየበዛ በመም ጣቱ፣ የእርስ በርስ ግድያው፣ ጭካኔውና እንዲሁም የደም መፋሰሱ ከመጠን በላይ እየከፋ በመምጣቱ እግዚአብሔር ትዕግስቱ ያለቀበት ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ጻድቁን ከኃጢአተኛው ጋር በአንድ ላይ ለማጥፋት ያልፈለገው እግዚአብሔር፣ በዚያን ወቅት ክፉ በሆነው ሕዝብ መካከል በቅድስና ይኖር የነበረውን ኖህና ቤተሰቡ የሚድንበትን መንገድ እዘጋጀ ላቸው። ዓለምን ለማጥፋት ከሰማይ የሚለቀቀው ዝናብ ከመምጣቱ በፊት ኖኅ መርከብ እንዲሰራ አስቀድሞ መመሪያ ሰጠው። ኖኅም ዝናብ መም ጣቱን የሚያሳይ ዳመናም ሆነ ሌላ ዓይነት ምልክት ባያይም፣ እግዚአብ ሔር የተናገረውን ቃል በማመን ብቻ እርሱ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የመዳኛ መርከቡን ሠራ። ጊዜው ሲደርስ፣ እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት በምድሪቱ ላይ የነበሩትን ነፍስ ያላቸውን ፍጥረታት ሁሉ በውሃ እንዳጠፋ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ይመሰክራል። "የሰዎችን ክፋት፣ እንዲ ሁም በክፋታቸው ምክንያት የሚደርሰውን አሳዛኝ ነገር እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚያውቅ ከሆነ፣ አስከፊ የሆነ እልቂት በዓለም ላይ እንዳይደ ርስ የሰውን ልጅ የማይገታው ለምንድነው?" ብለው የሚጠይቁ አንዳንድ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን እውነት፣ እግ ዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር የራሱ ፈቃድና ምርጫ እንዲኖረው እድርጎ ሰሰ ሆነ የሚደርስበት ክፉም ሆነ ደግ ነገር የምርጫው ውጤት እንደሆነ ነው።

ያለንበት ዘመን የከፋ ነው

የነጻነትና የሰላም እገር የሆነችው አሜሪካ በአሁኑ ጊዜ የመጋደያ ክልል መስላ ትታያለች። በጠር ሜዳ ላይ ብቻ ይታያሉ ብለን ያሰብናቸው ነገ ሮች ሁሉ፣ በሰላሙ ጊዜ በአሜሪካ ምድር በየመንደሩ፣ በየከተማውና በየእ ውራ መንገዱ መታየታቸው ያሳዝናል። በትላልቆቹም ሆነ በትናንሽ ከተ

ማዎች ሁሉ የእርስ በእርስ ግድያ የደም መፋሰስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨ መረ እንደ መጣ ይታወቃል። በአሜሪካ ምድር የምንኖር፣ የሚያስደነግ ጠውን አሳዛኝ ዜና በየቀኑ መስማቱን እየለመድነው መጥተናል። በዓለም ዙሪያ እሸባሪዎች የሚያፈነዱት ፍንዳታ፣ በፍንደታው የሚያልቀው ሰው ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በወጣቶች መካከል "ግደል! እለበለዚያ ትገደላለህ" የሚለው ማሰጠንቀቂይ እየተጠናከረና እየባሰ፣ የሰው ሕይወት እንደ ርካሽ ዕቃ እየተቆጠረ መምጣቱ ግልጽ ነው።

የሰው ሕይወት፣ ገና በእናቱ ማህጸን ጀምሮ ከማህጸን እስከሚወጣ ድረስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ቅዱስ ነገር መሆኑ ቀርቶ፣ በዘመናች እንደ ርካሽ ዕቃ የሚታይበት ጊዜ ሆኗል። ያለንበት ዓለም ከምንጊዜውም የበ ለጠ መተማመን የጠፋበት፣ ጥርጣሬ፣ ክህደትና ተስፋ መቁረጥ በፈታ ቸው ገጽታ በግልጽ የሚነበብባቸው ሰዎች ቁጥር የበዛበት ዓለም ሆኗል። የሕይወት መጥፋት፣ የሰውን ቁስ አካሉን (ሥጋውን) ብቻ ሳይሆን፣ መን ፈሳዊ ሕይወትንም የሚያጠፋ ነው። "አትግደሉ" የሚለው ትዕዛዝ፣ እንዳ ይሞት የሚከላከለው የሰውን ሥጋዊ አካሉን ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ሕይወቱንም ጭምር ነው። ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የሰውን ሕይወት ማጥ ፋት፣ ተስፋ ቢስነትንና ተስፋ መቁረጥን ያደርሳል።

የሰው ልጅ ልብ ክፋቱ፣ ከቁጥጥር ውጪ ሲሆን፣ እርስ በርሱ እንደ ሚተላለቅ፣ እንዱ ሌላውን እንደሚገድልና እንደሚያጠፋ የታወቀ ነው። ጥላቻና ግድያ መሠረታዊ ምንጩ ከሌላ ሰፍራ የሚመጣ ሳይሆን፣ ከሰው ልብ ውስጥ የሚፈልቅ እንደሆነ የታወቀ ነው። በጸጋ የተሞላው እግዚአብ ሔር ካልገታው፣ ወይም ካላቆመው ሰው ራሱንም ሆነ ታሪኩን እንዳልነ በረ እድርጎ ሊያጠፋ እንደሚችል ታሪክ ይመሰክራል። ፍቅር የሆነው እግ ዚአብሔር፣ ሰው እርስ በርሱ እንዳይጨራረስ ወይም እንዳይገዳደል በማሰብ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ በእሁኑ ዘመን ላለነውም ሰዎች መመሪያ እንዲሆነን አሥርቱ ትዕዛዛትን በሙሴ እማካኝ ነት፣ "አትግደል..." የሚለውን ትዕዛዝ እክሎ ስጥቶናል። በእሁኑ ዘመን፣ በኖኅ ዘመን የነበረውን ዓይነት እልቂትና ጥፋት ለማየት ተቃርበን ይሆን? እርግጥ ነው የምንኖረው የሰዎች ልጆች በቁጣ የተሞሉብት፣ ትርጉም የለሽ ግድያ ከምንጊዜውም የበለጠ እይሎ የሚታይበት ጊዜ ነው። ሌላው ቀርቶ ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሳይወለዱ፣ ገና በእናታቸው ማህጸን ውስጥ እየ ተገደሉ የሚያልቁት ሕጻናት ቁጥር እንኳን እየጨመረ የመጣበት ዘመን

ነው። በዓለም የሚደርሰው መከራ የሰዎችን ዐመጸኛ የሆነውን ልባቸውን መለወጥ እንዳልቻለ ዮሐንስ ባየው ራዕይ ሲገልጽ፣ "...ከሥራ ግድያቸው፣ ከጥንቆላ ሥራቸው፣ ከዝሙት ርኩሰታቸው ወይም ከስርቆታቸው ንስሓ አልገቡም" ይላል (ራዕ. 9፥21)።

"አትግደል" የሚለው ትዕዛዝ፣ በአሁኑ ወቅት በሰዎች ልብ ውስጥ ምን ዓይነት ሥፍራ ይዞ ይሆን? የስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ ሳይካትሪስት የነበሩት ዶናልድ ቲ. ሉንድ፣ በአሜሪካ ውስጥ የሚፈጸመው ግድያ ቁጥር በታሪክ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት መሆኑን ባደረጉት ጥናት ገልጸዋል።

- ከ1965 እስከ 1975 (እ.አ.አ.) ይኸውም በአሥር ዓመት ውስጥ የግድያ ቁጥር አጥፍ መጨመሩን ጠቁመዋል።
- በጥይትና በጠመንጃ ተመትተው ሕይወታቸውን የሚያጡ፣ እንዲሁም የሌላውን ሰው ሕይወት የሚያጠፉ፣ በ15ና በ24 ዓመት ዕድሜ መካከል ውስጥ ያሉ አሜሪካውያን ወጣቶች ቁጥር 19 ከመቶ (19%) ከፍ እንዳለ ገልጸዋል።
- በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ውስጥ ከ200 ሚሊዮን የሚበልጥ ጠመንጃና ሽጉጥ በሕዝቡ እጅ እንዳለ ጨምረው ገልጸዋል። በዚህ ምክንያት አሜሪካ ውስጥ በጥይት ተመተው ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎች ቁጥር በዓመት ከ10 ሺ ሰዎች በላይ እንደሚ በልጥ ታውቋል።
- በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጦርነቶች ምክንያት ሕይወታ ቸውን ያጡ 530,000 ሰዎች ሲሆኑ፣ ከ1900 ዓ.ም. ጀምሮ በጥ ይት ተመትተው ሕይወታቸውን ያጡት ግን ከ800,000 በላይ እንደሆነ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተደረገው ጥናት ይገልጻል።

የክርስቶስ ወንጌል "ሕይወት" ከሙተንፈስ ወይም ከእስትንፋስ በላይ እንደሆነ፣ እንዲሁም ለመኖር ያህል ብቻ ከምንኖረው ኑሮ በላይ እንደሆነ ያሳየናል። እግዚአብሔር ሚስጢራዊ በሆነው በመፍጠር ሥራው ሰውን በራሱ አምሳል ስለ ፈጠረው፣ ሰው የራሱንም ሆነ የሌላውን ሰው ሕይወት ማጥፋት እንደሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ያዛል። ሰው እግዚአብሔርን መስሎ በመፈጠሩ መገደል፣ እንዲሁም የሌላውን ሰው ሕይወት ማጥፋት

እንደሌለበት፣ ይህን ትዕዛዝ ቢተላለፍ ግን በፈጣሪው ላይ ማመጹ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። "የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ በሰው እጅ ይፈሳልI በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔር ሰውን ሠርቶታልና" ይላል (ዘፍ. 9፥6)። የሰውን ሕይወት ማጥፋትም ሆነ መንፈሱን መጉዳት በእግዚአብ ሔር ላይ አመጽን ማካሄድ ነው።

ይሄም እውነት ትዕዛዙ ምን ያህል ጥልቅና አሳሳቢ እንደሆነ ያሳያል። በብሉይ ኪዳን "ግድያ" ወይም መገደል በሁለት ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈ ጸም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይኸውም አንደኛው፣ ሆን ብሎ ወይም እውቆ መገደል ሲሆን፣ ሁለተኛው ሆን ብሎ ሳይሆን፣ ሳያውቅ መገደል ነው። "ሰውን ደብድቦ የገደለ ሞት ይገባዋል። ሆኖም እግዚአብሔር ፈቅዶ ሰውየው ሳያውቅ በድንገት አደጋት ከሆነ አኔው ወደምወሰነው ስፍራ ይሸሽ። አንድ ሰው በተንኮል ሆን ብሎ ሌላውን ቢገድልI ከመሠዊያዬ ተወሰዶ ይገደል" ይላል (ዘጸ. 21፥12-14)። ሆን ብሎ ሳይሆን፣ ድንገት ሰው ቢገድል ሸሽቶ የመሰውያውን ቀንድ ከያዘ ከሞት ያመልጣልI ሆን ብሎ ገድሎ ሸሽቶ የመሰውያውን ቀንድ ቢይዝ ግን፣ ከመሰውያው ተወ ሰዶ እንዲገደል ሕጉ ያዛል።

የሰውን ሕይወት ከሞት ለመጠበቅ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ የበለጠ አጠ ንክሮ ይናገራል። "በሬ አንድን ወንድ ወይም ሴት ቢገድልI በሬው በድን ጋይ ተወግሮ ይሙትI ሥጋውም አይበላI ነገር ግን የበሬው ባለቤት በኃላ ፊነት አይጠየቅም። ሆኖም በሬው የመውጋት ዐመል ያለበት ሆኖ ሰባ ቤቱም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሳለ በበረት ሲያስቀረው ቀርቶ አንድን ወንድ ወይም ሴት ቢገድልI በሬው በድንጋይ ይወገርI ባለቤቱም እንዲሁ ተወ ግሮ ይሙትI ሆኖም ካሣ እንዲከፍል ከተጠየቀI የተጠየቀውን ሁሉ በመክ ፈል ሕይወቱን ይዋጅ" ይላል (ዘፀ. 21፥28-30)። በትክክል ካልተመለከት ነውI ይሄ የብሉይ ኪዳን ትዕዛዝ እርስ በርሱ የሚቃረን ይመስላል። የሌላ ውን ሰው ሕይወት ማጥፋት ወይም መገደል "ሕጉን መጣስ ነው" ይልናI ቀጥሎ ግን ሌላውን የገደለውን "ግደሉት" ይላል። ማንም የሌላውን ሰው ሕይወት ሆን ብሎ እንዳያጠፋ የሚገታውን ብርቱ ትዕዛዝ መጣሱ አይሆ ንም ወይ? ይህንን ምክንያት በመስጠት ገዳይን በሞት መቅጣት ትክክል አይደለም የሚሉ አሉ።

በብሉይ ኪዳን የአንዱ ሰው በሬ ሌላውን ወግቶ ቢገድልI የበሬው ባለቤት ቅጣት እንደማይደርስበትI በሬው ግን ሌላውን የመግደል ባህሪ

እንዳለው እያወቀ በፊውን አሥሮ ባይዘውና ሰው ቢገድል፣ በፊውን ብቻ ሳይሆን የራሱንም ሕይወት እንደሚያጣ ከላይ ሰምተናል። በዘመናችን ሌላውን ወግቶ የሚገድል በሬ ባይኖርም፣ በሚያሽከረክረው መኪና ምክንያት የብዙዎች ሕይወት እንደሚጠፋ የታወቀ ነው። በእሁኑ ጊዜ በመጠጥ ኃይል ተይዘው በመንዳት የብዙዎች ሕይወት እንደሚጠፋ እናውቃለን። እነዚህ ሁሉ ነፍስ በማጥፋታቸው ምክንያት መገደል አለባቸው እንል ይሆን? ቀደም ብለን እንደገለጽነው የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ በዚህ ህሳብ ላይ የሰዎችን የተለያየ እቋም ለማሳየት ስላልሆነ፣ እሳቡን እዚሁ ላይ ቋጭተን ማለፋን እመርጣለሁ።

"አትግደል" የሚለው ትዕዛዝ ሁላችንንም ይመለከታል

"ማንንም አልገደልኩም! ...ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜዬን ስምን አጠፋለሁ? በዚህ ነጥብ ላይ ትምህርት ማዘጋጀቱ ምን ይጠቅማል?" ማለታችን እይቀርም። "አትግደል የሚለው ትዕዛዝ እኔን ፊጽሞ አይመለከተኝም" ብለን ከመደምደማችን በፊት ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ የተናገረውን ልብ ብለን እንመርምር። *"ሽቀደሙት ሰዎች አትግደል! የገደለ ይፈረደበታል እንደተባለ ሰምታችኋል! እኔ ግን እላችኋለሁ! ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል! ማንም ወንድሙን ጅል የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል! ደደብ የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል"* ይላል (ማቴ. 5፥21-22)። ሌላውን 'ደደብ' ወይም ሞኝ ብሎ መጥራት፣ ከመኖር ውጪ ማድረጋችን፣ በሕይወት መኖር አይገባውም ማለታችን ይሆናል። ይሄም በዓይን የማይታይ ግድያ በሌላው ላይ መፈጸማችን ነው። ለመሆኑ "አትግደል" የሚለው ስድስተኛው ሕግ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያሳየው ወይም የሚገልጸው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? እግዚአብሔር 'አትግደል' የሚለውን ሕግ የሰጠን ለምንድ ነው? እርሱን በሕይወታችን ከሁሉም ነገር በላይ ወይም እንደኛ እድርገን የምንወደው ከሆነ፣ ማንንም እንደማንጎዳ ያውቃል። የሚጠሉንና የሚያሳድዱንስ የምናያቸው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? እርሱ እኛን በጣም ስለወደደን፣ ክፉዎችና የእግዚአብሔር ጠላቶችም ብንሆንም በእኛ ምትክ በመስቀል ላይ እንደሞተልን፣ እኛም እርሱን የምንወደው ከሆነ፣ እርሱ እንደወደደን ክፉ የሚያደርጉብን ሰዎችንም እንወዳቸዋለን። ጳውሎስ

ለሮም ቤተክርስቲያን ለነበሩት አማኞች "ይህም ተነሱ ለፅፍረት አይዳርግ ንም! እግዚአብሔር በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና ይላል (ሮሜ 5፥5)። የፊሰሰልን ፍቅር ጠላቶቻችንን በበቀል ጥይት እንድንገድላቸው ሳይሆን እንድንወዳቸው ኃይልን ይሰጠናል።

ሰው ሌላውን የሚገድልበት ምክንያት ምን ይሆን?

ሰው "አትግደል" የሚለውን ሰድስተኛውን ሕግ የሚጥስበት ዋና ምክንያት ምን ይሆን? ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው በጭካኔ ተሞልተው የሚገድሉበት ምክንያት ምን ይሆን? ለሚለው ጥያቄያችን መልስ እንፈልጋለን። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ሰው ሌላውን የመግደል ፍላጎት በልቡ ውስጥ የሚፈጠረው ወይም የመነሻው ምክንያት "ቁጣ" መሆኑን ይገልጻል። ሰዎች በጣም ሲቆጡ ወይም ሲናደዱ ሌላውን ለመግደል ይቀሰቀሳሉ። ሰው በልቡ ውስጥ ጥላቻና እንዲሁም ቁጣን በልቡ ውስጥ ማጠራቀም ሲጀምር፣ ወይም ቁጣውን በአግባቡ መጠቀም (መያዝ) ሲያቅተው፣ ሌላውን ለመግደል ልቡ ይነሳሳል። ቁጣና ጥላቻ ሌላውን ለመግደል ቀስቃሽ ወይም አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው። አመለካከታችንን የሚያጨልሙ፣ በትክክል እንዳናስብ የሚያደርጉ ናቸው። ባልና ሚስት ሲጣሉ፣ ከሁለት አንዳቸው ሌላውን *"አልወድህም/አልወድሽምI ለምን እንዳገባሁህ/እንዳገኩሽ አላውቅም"* ይባባላሉ። በዚህ ዓይነት በመካከላቸው ጠብ ሲፈጠር መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጣቸው ምክር አለ። *"ተቆጡI ነገር ግን ኃጢአት አትሥሩI በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ። ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት"* ይላል (ኤፌ. 4፥26-27)። "ተቆጡI ግን ቁጣችሁን መስመር ሳታስይዙ፣ በልባችሁ ውስጥ እንደያዛችሁት ወደ መኝታችሁ አትሂዱ" ማለቱ ነው። መስመር ያልያዘው ቁጣ፣ አጥፊያችን የሆነውን ሰይጣንን የመሰብ ኃይል እንዳለው ማወቅ አለብን። ይሄ ጠላታችን ወደ ሕይወታችን ሲሳብ የሚያጠፋው ትዳራችንን፣ ልጆቻችንን ብቻ ላይሆን፣ ሕይወታችንንም ጭምር ነው።

ታላቁ እስክንድር (አሌክሳንደር ዘ ግሬት) በታሪክ ውስጥ "ታላቅ" የሚል የቅጽል ስም ከተሰጣቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል እንደኛው ነው። "ታላቅ" በሚል ስም መጠራቱ በእርግጥም ተገቢው ነበር። ታላቁ እስክንድር በኃይል የተሞላ፣ ሁለገብ፣ ብልህ ሰው ነበረ። በአጠቃላይ በማንም

ላይ ጥላቻ ያልነበረው ሰው ቢሆንም፣ የሚያሳዝነው ለቁጣ ወይም ለንዴት ተሸናፊ የሆነ ሰው ነበር። እንድ ቀን አሌክሳንደር በጣም የሚወደው፣ አብሮ አደግ ጓደኛው፣ በጦር ሠራዊቱ ውስጥ የጄኔራልነት ማዕረግ የነበረው ሰው፣ ብዙ የሚያስከር መጠጥ ጠጥቶ በሰካር ላይ እያለ በወታደሮቹ ፊት እየሳቀ በመቀለድ አሌክሳንደርን ስላዋረደው፣ አሌክሳንደር በንዴትና በቁጣ ገንፍሎ አጠገቡ ከቆመው ወታደር እጅ ጦሩን ነጥቆ ያን በጣም የሚወደውን አብሮ አደግ ጓደኛውን ወርውሮ ልቡን ወግቶ ገደለው። የሰከረውን ጄኔራል ጓደኛውን ለማስደንገጥ እንጂ፣ ሕይወቱን ሆን ብሎ ለማጥፋት እልነበረም፤ ይሁን እንጂ፣ የሚወደውን ጓደኛውን በሞት አጣ። ወዲያው በሀዘንና በጸጸት ልቡ ተሞላ። ጓደኛውን ወርውሮ በገደለበት ጦር ራሱን ለመግደል ሲሞክር፣ አጠገቡ የቆሙት ወታደሮች ራሱን እንዳይገድል አሰቆሙት። ሰብዙ ቀናት ታመመ፤ የጓደኛውን ስም መጥራት፣ ራሱን ነፍሰ ገዳይ እያለ መክሰስ አላቆመም። ታላቁ እስክንድር ብዙ አገሮችን፣ ብዙ ታላላቅ ከተሞችን በጦርነት ድል አድርጓል፤ ነገር ግን የራሱን ቁጣ ወይም ንዴት ማሸነፍ ግን አልቻለም።

እግዚአብሔር፣ ቁጣ ከምን ዓይነት እደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል መጀመሪያ ገልጾ ያስጠነቀቀው ቃየልን እንደ ነበር እናስታውሳለን። "እግዚአብሔር አምላክም ቃየንን እንዲህ አለው፤ ለምን ተናደደህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ተቀባይነትን አታገኝምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅህ እያደባች ናት፤ ልታሸንፍህ ትፈልጋለች፤ አንተ ግን ተቆጣጠራት" አለው (ዘፍ. 4፥6-7)። እግዚአብሔር የእጁ ሥራ የሆነውን ሰው በጣም ሰለሚወደው፣ ቃየል በልቡ ውስጥ እንደ እሳት ነዶ የነበረው ቁጣው ሊያደርስበት የሚችለውን ጉዳት ወይም እደጋ ምን ያህል ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል በሚገባው ቋንቋ ሊያስረዳውና እንዲሁም ሊያስጠንቅቀው ሞክሮ ነበር። ቃየል ግን ልቡ ሰረጅም ጊዜ በመራራነትና በንዴት ተሞልቶ ስለነበረ፣ እግዚአብሔር በመንገዱ ላይ ቆሞ ሊፈጽመው ያሰበውን ድርጊት እንዳይፈጽም ሊከለክለው፣ ወይም ሊያስቆመው ቢሞክርም፣ ቃየል በጅ አላለም። እግዚአብሔር የሰጠውን ማስጠንቀቂያም ሆነ ምክር ችላ ብሎ፣ ምንም ዓይነት በደል ያላደረሰበትን እንዱን ወንድሙን በድንጋይ ቀጥቅጦ ገደለው።

እግዚአብሔር ሕይወታችንን በሚመለከት ማንኛቸውም ጉዳይ ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ እዚህም ላይ የሰውን ልጅ ችግር ውስጥ ሊከተው

የሚችለውን ዋና ምክንያት ሲነካ እናየዋለን። የችግሩ ዋና ምክንያት የሆነውን ላይ ላዩን በመቁረጥ ፈንታ፣ ወደ ውስጥ ዘለቅ ብሎ በመግባት ሥሩን ሊነካው እናያለን። መርዛም የሆነውን አረም ወደ ውስጣችን ዘልቆ በመግባት ከሥሩ ቆርጦ ሊያስወግደው ይፈልጋል። የነፍስ ግጥፋት (ግድያ) ዋናውና መሠረታዊ ምክንያት ሌላ ነገር ሳይሆን ንዴት (ቁጣ) እንደሆነ ኢየሱስ ይናገራል። በክርስቶስ ዘመን እንደ ነበሩት ፈሪሳውያን "ማንንም እልገደልኩም" በማለት ይህንን ስድስተኛውን ትዕዛዝ ችላ ብለን እንዳናልፍ መጠንቀቅ አለብን። ኢየሱስ ሊያሳስበን የሚፈልገው፣ ውጪያዊውን ላይ ሆን ከልባችን ውስጥ ያለውን ነገር ነው። መሣሪያ አንስተን ሌላውን ተኩሰን ከመግደላችን በፊት፣ በእዕምሯችን ውስጥ የሚካሄደውን አሳብ አስቀድመን እንድናይ ሊያደርገን ይሞክራል።

ከአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ "እኔን እይመለከተኝም... ይህንን ትዕዛዝ እልተላለፍኩም" የምንለው "አትግደል" የሚለውን ስድስተኛውን ትዕዛዝ ይሆናል። እርግጥ ነው በሽጉጥ መትተን፣ በድንጋይም ሆነ በዱላ ቀጥቅጠን አንድም የገደልነው ሰው ላይኖር ይችላል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንዶቻችን ከዚህ በደል ሙሉ በሙሉ ነጻ አይደለንም። ኢየሱስ "ሰቀደሙት ሰዎች አትግደል፤ የገደለ ይፈረድበታል እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን ጅል የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ ደደብ የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል" (ማቴ. 5፥21-22) ሲል፣ በዓይን የሚታየውን ዓይነት መግደል ማለቱ እንዳልሆነ ይገባናል። በቁጣ ተሞልተን አጥንት ሰብሮ የሚገባ ስድብ የሰደብናቸው፣ ክፉ ቃል የተናገርናቸው ሰንቶች ይሆኑ? እርግጥ ነው ተኩሰን የገደልናቸው፣ በዱላና በድንጋይ ቀጥቅጠን የገደልናቸው የሉም። ይሁን እንጂ በጥላቻ መንፈስ ተሞልተን የገደልናቸው፣ ስማቸውን በማጥፋት እንዳይሞቱ እንዳይሽሩ እድርገን ያጠፋናቸው፣ ስማቸውን ያለአግባብ ያቆሸሽንባቸው፣ እኛ በዳዮቹን ባይሰማንም ደማቸው ግን ወደ አግዚአብሔር የሚጮኽ ሰንቶች ይሆኑ? በሠሜትና በአሉባልታ ጎጂ በሆነው ምላሳችን ወግተን የገደልናቸው፣ እከባቢው ሕብረተሰቡ እንዳይቀበላቸው፣ ፊቱን እንዲያዞርባቸው፣ ያደረግናቸው፣ ጠልተን ያስጠላናቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደማቸው በእግዚአብሔር ፊት እየጮኸ ነው።

እግዚአብሔር ለአንዳንዶቻችን እንዲሁ በጸጋው ከሌሎች የበለጠ ወይም የተሻለ አዕምሮ፣ ቀልጣፋ ምላስ፣ ብርቱ ክንድና ጉልበት ሰጥቶን ይሆናል። ታዲያ ይህን ታላቅ ስጦታ የተጠቀምንበት እንዴት ይሆን? ወን ድማችንን ገፍተን ለመጣል፣ በረከቱን ለመውሰድ፣ ክቤተ ክርስቲያን ሕብረት ለማስወጣት ተጠቅመንበት ይሆን? ጳውሎስ *"በእምነት የደከመ ውን ተቀበሉት፣ በአሳቡም ላይ አትፍረዱ"* (ሮሜ 14፥1) ሲለን፣ ስጦታች ንን የደከመውን ወንድማችንን ደግፈን ለማንሳት የምንጠቀምበት እንዲሆን ሲመክረን ነው። አማኞች በእግዚአብሔር ቤት አብረን የምንኖረው፣ እርስ በርሳችን ለመጠላለፍ፣ አንዱ ከሌላው ለመቅደም ሳይሆን ተደጋግፈን ጌታ እስኪመጣ ድረስ አብረን ለመቆም ነው። ዛሬ ደጋፌ አጥተው፣ ወይም በወንድሞቻቸው ተገፍተው እግራቸው የሚንቀጠቀጥባቸው፣ "የውሰጤን ለማን ልንገረው? የማምነው ክርስቲያን ወዳጅ አጣሁ" የሚሉ ክርስቲያኖች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ኢየሱስ ነፍስ መግደል ያለውን ጥልቅ አሳብ ሲገልጽ፣ *"...ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድሙን ጅል የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበታል፤ ደደብ የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል"* ይላል (ማቴ. 5፥21-22)። የሚያስፈርድብን ማንኛውም ዓይነት ቁጣ ሳይሆን፣ ያለአግባብ የሆነ ቁጣ እንደሆነ ኢየሱስ ይናገራል። ጳውሎስም *"እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። ለቤዛ ቀን የታተምችሁበ ትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ። መራራነትን ሁሉ፣ ቁጣና ንዴትን፣ ጭቅጭቅና ስድብን ከመንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ"* በማለት ይመክረናል (ኤፌ. 4፥29-31)። መጽሐፍ ቅዱስ መቆ ጣትን አይከለክልም። እንዲያው ኤፌ. 4፥26 ላይ *"ተቆጡ! ኃጢአትን ግን አታድርጉ..."* ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ *"መራራነት፣ ንዴት፣ ቁጣ... ከእናንተ ይራቅ"* ሲል፤ (ኤፌ. 4፥31) ያለአግባብ የሚገለጸውን ቁጣ ማለት ነው።

በሰው ተፈጥሯዊ አካል ውስጥ በጣም እነስተኛ (ትንሽ) የሚመስሉ የሰውነት ክፍሎቻችን፣ ለምን እንደተፈጠሩ፣ ምን ጥቅም እንዳላቸው እኔና እናንተ አንወቅ እንጂ የማያስፈልጉ ወይም እንዲሁ ያለምክንያት የተፈጠሩ አይደሉም። ልክ እንደዚሁ፣ አስፈላጊነታቸው አይግባን እንጂ ሰሚቶቻችንንም የፈጠራቸው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ "እያስፈልጉም" የም

ንሳቸው ስሜቶች የሉንም። ከስሜቶቻችን መካከል ለምሳሌ <u>ፍርሃት፣ ድን ጋጤ፣ ሲጋት፣ ቁጣን</u> የመሳሰሉ መጥፎ ይምሰሉ እንጂ፣ በአግባቡ ከተጠ ቀምንባቸው ሁሉም ጠቃሚነት ያላቸው ናቸው። ፊጽሞ አለመቆጣት መልካም ይምሰለን እንጂ፣ አለመቆጣት እግዚአብሔር በሰጠን መልካም ስጦታ አለመጠቀም ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሲቆጣ የም ናየው ለው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደገለጹት ብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር 455 ጊዜ፣ እንዲሁም በአ ዲስ ኪዳን ውስጥ 375 ጊዜ ቁጣውን እንደገለጸ ይናገራል። በቅድስናቸው የታወቁት መንፈሳዊ አባቶችም በተደጋጋሚ ሲቆጡ እናያለን። ሙሴ እግ ዚአብሔር ያደነቀው ሰው ቢሆንም፣ ብዙ ጊዜ ሲቆጣ እናየዋለን። *"ሙሴም ወደ ሲና ሰፈር ተጠግቶ ጥጃውንና ጭፈራውን ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣ፤ ይዟ ቸው የመጣውንም ጽላቶ በተራራው ሥር ወርውሮ ሰባበራቸው"* ይላል (ዘፀ. 32፥19)።

እግዚአብሔር በአግባቡ እንድንጠቀምበት የሰጠንን *"የመቆጣት"* ስሜ ታችንን ያለአግባ ከተጠቀምንበት፣ ሌላውን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም እን ጎዳለን። ቁጣና ንዴት የብዙ ሰዎች ትዳር መፍረስ ምክንያት ሆኗል። በቁጣ ተናግረው ብዙ ወዳጆቻቸውን ያስቀየሙ፣ የነበራቸውን የተቀራረበ ግንኙነት ያበላሹ አሉ። በቁጣና በንዴት ተሞልተው ልጆቻቸውን ክፉ ቃል ተናግረው የማይጠፋ ጠባሳ በሕይወታቸው ላይ ትተዋል። አንዳን ዶች ደግሞ ቁጣቸውን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላቸው፣ የብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆነዋል። ሌሎች ደግሞ ዘመናቸውን በወህኒ ቤት እንዲያሳልፉ ሆነዋል። አንድ ቀን ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አንዳንድ ልክ ያልሆነ ነገር ሲፈጸም አየ። ምስኪን ድሆች በገንዘብ ለዋ ጮች ሲበዘበዙ፣ ያባቱ ቤት የሚገባውን ክብር አሳጥተው መነገጃና መለ ወጫ አድርገውት ሲያይ ኢየሱስን በጣም እንዳስቆጣው እናውቃለን። ቁጣው አግባብነት ያለው እንጂ ከመስመር የወጣ ቁጣ አልነበረም።

አንድ ጊዜ አንድ ትንሽ ልጅ አባቱን "አባባ ጦርነት የሚጀመረው? እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀው። አባትየውም ሲመልስለት፣ "ለምሳሌ አን ደኛው ዓለም ጥርነት የጀመረው፣ ጀርመን ቤልጀምን በመውረሩ ምክን ያት ነው" አለው። ልጁ የጠየቀውን ጥያቄ እንዲሁም አባትየው የሰጠውን መልስ የልጁ እናት ስትሰማ፣ ተቆጥታ "ትክክለኛውን ነገር ለልጁ ንገረው እንጂ! ጦርነቱ የጀመረው እንዱ ሌላውን በመግደሉ አይደለም እንዴ?"

አለችው። አባትየውም ከሚሰቱ የተሻለ መሆኑን ለማሳየት ተቆጥቶ "ጥያቄውን ያቀረበው ለአንቺ ነው ወይስ ለእኔ? ለምን ጣልቃ ትገቢያለሽ?" በማለት ተቆጥቶ ተናገራት። በዚህ ጊዜ ፊቷን አዙራ ቁና ቁና እየተነፈሰች፣ በንዴት ተሞልታ በሩን በኃይል ጓ እድርጋ ዘግታ ቤቱን ጥላ ወጣች። በሩን በኃይል ጥርቅም እድርጋ ስትመታው ተደርድረው የነበሩት ብርጭቆዎችና ሳህኖች መሬት እየወደቁ ሰብርብራቸው ወጣ። ያልጅ ይሀን ሁኔታ ከተመለከተ በኋላ አባቱን፣ "አባባ! ግዴለም ለጥያቄዬ መልሰ እግኝቻለሁ፤ ከዚህ የበለጠ መልሰ አልፈልግም፤ ጦርነት እንዴት እንደሚነሳ አሁን ገብቶኛል" አለው።

ኢየሱስ "...ወንድሙን ያለ አግባብ የሚቆጣ ...፣ ወንድሙን ጅል የሚል... ደደብ የሚል..." በልቡ ነፍሰ ገዳይ ነው ይላል (ማቴ. 5፥21-22)። ቁጣ ከውስጣችን የሚፈልቅ ስሜት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ልባችንን መጠበቅ ያለብን እንዴት ነው? የቁጣችን ወይም የንዴታችን ዋና ምክንያት ምን ይሆን? ለምንድነው የምንቆጣው? መብታችን የተነካ፣ ያበጀነው ድንበር የተጣሰ መስሎ ሲሰማን፣ ተደረገብን የምንለው ነገር ጉዳት ያደረሰብንም ባይሆን የምንቆጣበት ጊዜ አለ። እንዱ እውቆም ሆነ ሳያውቅ እግራችን ላይ ቆሞ ቢያሳምመን፣ ህመሙ ተሰምቶን "ዋይ!" ብለን መጮኻችን እይቀርም። ሕመሙ ሲሰማን ታግሰን፣ መጨረሻ ላይ በረገጠን ሰው መቆጣታችን እይቀርም። የሚያሳምመን ነገር ደርሶብን እንደሚያመን ሁሉ፣ የሚያሰቆጣ ነገር ሲያጋጥመን ደግሞ መቆጣት ተፈጥሯዊ ባህሪያችን ስለሆነ፣ ቁጣ እንዳይሰማን ለማድረግ አንችልም። ቁጣችንን የምንገልጽባቸውን መንገዶቻችንን ግን መወሰን እንችላለን። በቅርቡ በአሜሪካ ውስጥ ከእርሱ ሕይወት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸውን፣ ወይም በእርሱ ሕይወት ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ያላደረሰብትን 31 የቨርጂኒያ ቴክ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንና መምህራንን፣ በጥይት እየመታ ከገደለ በኋላ ራሱን መትቶ የገደለው ወጣት ምክንያቱ ምን ይሆን? ይህን ዓይነቱን ወንጀል እንዲፈጽም ያነሳሳው ምንድነው? "በሕይወቴ ደረሰብኝ" የሚለው ጉዳት ይሆናል። ያንን የመሰለ ወንጀል የፈጸመው ሰው ችግሩ የተሰማው የመጎዳት ስሜት ሳይሆን፣ ቁጣውን ወይም ንዴቱን በአግባቡ መግለጽ ካለመቻሉ የተነሳ ነው። በውስጡ ይሰማው የነበረውን ቁጣና ንዴት በጊዜውና በአግባቡ በመግለጽ ፈንታ፣ ከውስጡ በማጠራቀሙ፣ ከውስጡ ያጠራቀመው ስሜት ሲይዘው ከሚችለው በላይ

ሲሆን፣ ፈንድቶ የራሱንም ሆነ የሌላውን ሰው ሕይወት ከማጥፋት ደረጃ ሊደርስ ቻለ።

በእግባቡ ያልተያዘ ቁጣ የሚያደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት እግዚአብሔር ያውቃል። ምንም ያህል በሰው ልብ ውስጥ ተደብቆ ቢቆይ አንድ ቀን ፈንድቶ በግልጽ መታየቱ አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ የሚያሰቆጣን ጥቃቅን ምክንያቶች ሊያጋጥመን ይችላል። ለምሳሌ መኪናችንን ስናሽከረክር በትራፊኩ ብዛት ምክንያት ከፈለግንበት ቦታ በሰዓት መድረስ ሲያቅተን፣ በቀላሉ የምንቆጣበት ወይም የምንናደድበት ጊዜ እስ። እንዲሁም መብታችን የተነካብን ሲመስለን እንቆጣለን (እንናደዳለን)። የምንፈልገውን በምንፈገው ጊዜና ሰዓት ማግኘት ሲያቅተን እንናደዳለን። "ይሀን ወይም ያንን ማግኘት መብቴ ነው" በማለት የፈለግነውን በፈለግነው ጊዜና ሰዓት ማግኘት ሲያቅተን፣ ያቁነጠንጠናል፤ ለላማችን ይገፈፋል። ታዲያ ይሀን ዓይነቱ ስሜት ከቁጥጥር ውጪ እንዳይወጣ መያዝ የምንችለው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

አንደኛው፣ የሚሰማንን ስሜት ወዲያው በተግባር ከመግለጽ፣ ጥቂት ጊዜ መውሰድ ጠቃሚ ነው። ስሜትን ቶሎ አለመግለጽ ምን ያህል ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ይሀን ያህል የአንጎል ቀዶ ጥገና ህክምና መሆንን አይጠይቅም። ቃየል ወንድሙን አቤልን "ና ወደ ሜዳ እንውጣ" በማለት ይዞት በመሄድ ፈንታ ለብቻ ተገልሎ ቢቀመጥና ጥቂት የማሰቢያ ጊዜ ቢያገኝ ኖር፣ ያን የመሰለ የነስፍ መግደል (ማጥፋት) ወንጀል ባልፈጸመም ነበር። ያዕቆብ "...ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገር የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን..." (ያዕ. 1፥19) በማለት ይመክራል። ከዚህ የተሻለ ምክር የትም አናገኝም። ቶማስ ጄፈርሰን ሲቆጣ፣ ከአንድ እስከ አሥር ድረስ ይቆጥር ነበር። በጣም የተናደደ እንደሆነ ደግሞ ከአንድ እስከ መቶ ይቆጥር ነበር። እንዳንድ ጊዜ በጣም ከመናደዱ የተነሳ፣ መቁጠር እስከ ሚያቅተው ድረስ ጊዜ ወስዶ ይቆጥር ነበር። ቁጣዬን ለማብረድ "አንድ–ሁለት" እያልኩ መቁጠሬን ካቆምኩ፣ የሚጸጽተኝን ነገር አደርጋለሁ ብዙ እፈራለሁ" አለ። ጠቢቡ ሰሎሞን "አስተዋይ ሰዎች ለሚሠሩት ሥራ አስቀድመው ዕቅድ ያወጣሉ፤ ማስተዋል የጎደላቸው ሰዎች ግን አላዋቂነታቸውን ይገልጣሉ" ይላል (ምሳሌ 13፥16)። ከመጠን በላይ ስንቆጣ ወይም ስንናደድ፣ ወዳጅነታችንን፣ ግንኙነታችንን ፈጽሞ ሊያጠፋ የሚችለውን ቃል እንደምንናገር የታወቀ ነው።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሰባተኛው ትዕዛዝ

"አታመንዝሩ..."

"አታመንዝር"
(ዘፀአት 20፥14)

"ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበርI መኝታውም
ንጹሕ ይሁንI ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና
በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል" ይላል (ዕብ. 13፥4)።

"የምንዝር ተግባር የሚፈጽም ሰው ግን ማሰተዋል
የጎደለው ነውI ሕይወቱን በክንቱ ያጠፋል" (ምሳሌ 6፥32)።

ከተሃድሶ ዘመን በፊት የጣሪ ሥጋ ግንኙነት በጋብቻ ክልል ውስጥ ቢሆንም እንኳን በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ክፉ ነገር ወይም እንደ ኃጢአት ይታይ ነበር። ከጥንት መንፈሳዊ አባቶች መካከል ለምሳሌ፥

- አምብሮስ የተባለው መምህር "ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸማቸው ሊያፍሩበት ይገባል" ሲል አገሰቲን ደግሞ "በጋብቻ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ትክክል ቢሆንም የግብረ ሥጋ ስሜት ግን ኃጢአት ነው። አዳምና ሄዋን በኃጢአት ከመውደቃቸው በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አልፈጸሙም፤ ቢፈጽሙ ቀዝቃዛና ስሜት ያልተቀላቀለበት መሆን አለበት" ብሎ ያስተምር ነበር።
- ተርቱልያን ደግሞ "በጋብቻ ውስጥና ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያለው ልዩነት ሕጋዊ የሚያደርገው ትንሽ የሕግ ወረቀት ነው፤ ሁለቱም የሀፍረት ወይም የውርደት ተግባር ነው" ይላል።

የቀድሞ መንፈሳዊ አባቶች በጋብቻ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው" ባይሉም፣ አማኞች ሳያገቡ እንዲኖሩ ያደፋፍሩ ነበር። ብዙ የካቶሊክ ካህናት ወይም ቄሶች ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚጠራቹ እንዳይፈጽሙ ይመክሩ ነበር። በተለይ "ቅዱስ ናቸው" በሚባሉበት ቀናት ውስጥ ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የለባቸውም በማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕግ ማውጣት ጀምራ ነበር።

- ማርቲን ሉተር ተሃድሶን ሲያውጅ፣ በዓመት ውስጥ ባልና ሚስት "በእነዚህ ቀናት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የለባቸውም" በማለት የለዩዋቸው ቅዱስ ቀናት 183 ደርሰው እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሀፊዎች ይገልጻሉ።

በጋብቻ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈቀደ ነው

ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ከላይ የሰማነውን ዓይነት የራሳቸው የሆነ አቋም ይኑራቸው እንጂ ያላቸው እምነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር አብሮ የማይሄድ ወይም የሚቃረን ነበር። ጊዜውን ጠበቆ የመጣው፣ በማርቲን ሉተር የሚመራው የቤተ ክርስቲያን ተሃድሶ፣ እግዚአብሔር በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ለተሳሰሩ ወንድና ሴት መደሰቻ እንዲሆን የፈጠረው የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ገና የሚገባውን ትክክ

ለኛ ሥፍራ እንዲይዝ ሆነ። የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ሰው በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸመው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ንጹሀና ትክክል መሆኑን ሲገልጽ፣ *"ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይክበርI መኝታውም ንጹሕ ይሁንI ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል"* ይላል (ዕብ. 13፥4)።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ሥፍራ ተጠቅሶ እናነባለን። በባልና በሚስት መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲኖር፣ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ የደነገገው ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ የፈጠራቸውን የመጀመሪያ ሰዎች *"ብዙ ተባዙ! ዘራችሁ ምድርን ይሙላI ምድርም በቁጥጥራችሁ ሥር ትሁን..."* አላቸው (ዘፍ. 1፥28)። በእግዚአብሔር መንፈስና አነሳሽነት የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ በወንድና በሴት መካከል ያለውን መሳሳብና መፈላለግ በግልጽ ይናገራል። ይህንን አባብ የሚገልጽ ብዙ በፍራ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል።

- *"ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ፣ ከንፈሮችህ ይሳሙኝ"* ይላል (መኃልየ መኃልይ 1፥2)።
- በዚሁ ምዕራፍ፣ ቁጥር አራት ላይ ደግሞ *"እጇን ይዘህ ሳበኝI አብረን እንሩጥI ንጉሥ ሆይ! ወደ እልፍኝህ አስገባኝI በዚያም አብረን ደስ ይለናልI ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ ያስደስታል..."* ይላል።
- እንዲሁም ሙሽራው ሚሽራቱን *"ውድ እኅቴ የሆንሽ ሙሽራዬ ሆይ! ፍቅርሽ እንዴት ያስደስታል! ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ ደስ ያሰኛልI መዓዛሽም ከማንኛውም ሽቶ ይበልጣል። ውዴ ሆይ! ከከንፈሮችሽ የማር መለላ ይፈሰላልI ከአንደበትሽም ማርና ወተት ይፈልቃልI የልብሽም መዓዛ የሊባኖስን ሽቶ ይመስላል"* ይላታል (መኃልየ 4፥10-11)።
- እንዲሁም 5፥2-5 ላይ *"...ውድ እኅቴ የሆንሽ ሙሽራዬ ሆይ! እባክሽ በሩን ክፈችልኝI ራሴ በጠል ርሷልI ጠጉሬም በሌሊት ካፊያ ረስርሶአል። ልብሴን አውልቄአለሁI ታዲያ እንደኛ ልልበሰን? እግሬንም ታጥቤአለሁI ታዲያ እንዴት እን*

ደኛና ላሳድፈውI ውዴ በበሩ ቀዳዳ በኩል እጁን ወደ ውስጥ ዘረጋI ልቤም ስለ እርሱ ተንሰፈሰፈ" ይላል።

እነዚህ ሁሉ የጠለቀ መንፈሳዊ ትርጉም ያላቸው ይሁኑ እንጂ፣ በወንድና በሴት መካከል ያለውን መፈላለግና መሳሳብን ያሳያል። ከላይ የሰማነውን ገለጻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምን ዓይነት የተቀራረበ ወይም የተያያዘ ሕይወት እንደሆነ መረዳት ያስችለናል። በባህላችን ተጽእኖ ምክንያት ይህንን እውነት ገላልጾ መናገር እኔና እናንተን ያሳፍረን እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሀፍረት የሚሰማው አይመስልም። በጋብቻ ውስጥ ያለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት የእግዚአብሔር ሥጦታ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ሥፍራ እንደተጠቀሰ ከላይ ገልጸናል። ምሳሌ 5፥18-19 ላይ የተጠቀሰው፣ *"ከመጣትንትህ ያገባሃት ሚስትህ እንደ ጥሩ የምንጭ ውሃ ስለሆነች ትባረክልህI ከአርስቦም ጋር ደስ ይበልህI እንደ አጋዘን ውብና እንደ ዋልያ ሞገስ የሞላባት ትሁንልህI ቁንጅናዋም ደስ ያሰኝህ ፍቅርዋም የሚያረካይ ይሁን"* የሚለው እንደኛው ነው።

ጥንት የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሰውን ዘር ለማባዛት እንጂ፣ ሰው ደስ እንዲሰኝበት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ወይም የተፈቀደ እንደሆነ አድርገው መቀበል ያቅታቸው ነበር። ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሰውን ዘር ለማባዛት ብቻ ሳይሆን፣ ሰው ደስ እንዲሰኝበት የተሰጠ መሆኑን በተደጋጋሚ ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር ራሱ የፈቀደለትን በጋብቻ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ እንዳያበላሽበት በማሰብ ነው እግዚአብሔር "አታመንዝር" የሚለውን ሰባተኛውን ትዕዛዝ ለሰው የሰጠው።

ብዙዎች *"ሕይወቴ የራሴ እንጂ የማንም አይደለም። ደስ ያለኝን ማድረግ፣ ደስ ባለኝና በፈለግሁት ዓይነት መኖር፣ የፈለግሁበት ቦታ መሄድ እችላለሁ። 'ይሆን አድርግ፣ ይሆን አታድርግ' የሚል ትዕዛዝ መስማት አልፈልግም። እኔን ራሴን ችግር ውስጥ እስካልከተተኝ ድረስ ማድረጌ አይቀርም።* እግዚአብሔር "አታመንዝር" ቢልም፣ የፈለግሁትን ነገር ባደርግ እርሱን አያገባውም" የሚል እቁም ያላቸው ሰዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። ከላይ እንደገለጽነው በንግግር ባይገልጹትም፣ በተግባራቸው ይገልጹታል። እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ ሰዎች ቢከተሉም ባይከተሉም፣ ዓለሙ ሁሉ የእርሱ ስለሆነ "እርሱን እያገባውም" ማለት አይችሉም።

እግዚአብሔር ስለ ዝሙት ወይም ስለ ማመንዘር ይህን ያህል ምን አስ ጨነቀው ወይም አሳሰበው?' ብለን መጠየቃችን አይቀርም። እኔና እና ንተ የራሱ ሕዝቦች ስለሆንና በጣም በሰሚወደን፣ እንድንጎዳም ስለማይፈ ልግ ከችግርና ከጉዳት የሚጠብቀንን ገደብ ወይም ወሰን አበጅቶልናል። በሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ ያሰውን ደስታ እልከለከለንም፤ የከለከለን ሊጎዱን ከሚችሉ ነገሮች መካከል እንደኛው የሆነውን ዝሙት ነው። ደስታችን የተሟላ እንዲሆን፣ በጋብቻ ውስጥ መኖር ስላለበት ንጽህናና ታማኝነት አስፈላጊ መሆኑን ያሳስበናል። ቤተሰብና እንዲሁም ቤተ ክርስ ቲያን፣ የእግዚአብሔር የፍቅሩና የቅድስናው ሞዴል እንዲሆኑ የመሠረ ተውና የወሰነው እርሱ በመሆኑ፣ ሰይጣን ሊያበላሸውና ሊያጠፋው ከፍ ተኛ ትግል እንደሚያካሂድ የታወቀ ነው። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ሰይጣን በጋብቻ ውስጥ ያለውን ፍቅርና እንዲሁም ቤተሰብን ለማጥፋት ያልተኛ መሆኑን እናውቃለን። በየቀኑ በቴሌቪዥናችን ላይ የምናያቸው ግብረ ገብ የጎደላቸው ድርጊቶች ሰዎችን ወደ ዝሙት የሚገፋፉ ወይም የሚያባ ብሉ መጥፎ ሀሳብ በሰው አዕምሮ ውስጥ እንዲፈጠሩ የሚያደርጉ ናቸው።

ከሆሊ ዉድ የሚፈልቁት የሲኒማ ትዕይንቶች ከላይ ሊታዩ ደስታ የሞ ላባቸው፣ የፍቅር ስሜት ቀስቃሾች፣ ሰለው ልጅ እርካታን የሚሰጡ እን ዲሁም አፍን በሳቅ የሚሞሉ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ ሰውን ሀፍረት ውስጥ የሚከቱ፣ "አፈቅረዋለሁ" የሚሉትን ሰው መዋሸትና ማታለል፣ እንዲሁም ከዳተኛነትን የሚያስተምሩ ናቸው። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት መልካም ያልሆነ ውጤት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ግን ሰዎች እንዲያውቁ አይፈ ልጉም። እውነቱን በትክክል ማየት የማይሆንላቸው አንዳንድ ሰዎች በሚ ያዩት ውጪያዊ ነገር ተስበውና "የእኔ ኑሮ የጨለማነው፣ የሚሰለች፣ ፍቅር የጎደለው ነው። እነዚህ ደምቀው የሚታዩት ነገሮች ምናልባት ባዶ የሆነውን ሕይወቴን የተሟላ እንዲሆን ሊያደርጉልኝ ይችላሉ" ብለው ያበባሉ።

ይሁን እንጂ ሆሊ ዉድም ሆነ ሌሎች ብልጭልጩን ነገር ቀባብተ ውና አሳምረው የሰውን ልብ ለመሳብ የሚሞክሩት ከፍሎች፣ ደስታ አለ በት ይበሉ እንጂ መጨረሻው ምን ያህል የከፋ እንደሚሆን ግን እውነቱን አያሰዩም። ከጋብቻ ከልል ውጪ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚሰ ጠውን ደስታ ይናገሩ እንጂ፣ መጨረሻ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ይኸ ውም፥ የሚያፈርሰውን ትዳር፣ የሚያስፈሰሰውን ዕንባ፣ የሚያስከትለውን የአባለ ዘር በሽታ ምን ዓይነት የከፋ እንደሆነ ገልጸ አያሰዩዋቸውም።

ዳዊት በውበቷ ተወዳዳሪ ካልነበራት ከቤርሳቤ ጋር ቢያመነዝር የሚያገኘ ውን ደስታ፣ የሚቀምሰውን ፍቅር እንጂ እግዚአብሔር ያበጀለትን ድን በር ጥሶ በመውጣቱ ምን ያህል ከበግ እረኛነት አንስቶ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ያበቃውን እግዚአብሔር እንደሚያሳዝን፣ በበደለኛነት ስሜት ምክንያት የሚደርስበትን ከፍተኛ የአዕምሮ ጭንቀት፣ ኃጢአቱን ለመሸ ፈን ሲል የሚያፈሰውን ንጹህ ደም፣ በተቀረው ዘመኑ ሊደርስበት የሚችለ ውን መከራና ችግር ሰይጣን ገልጾ አላሳየውም።

ሰይጣን የኃጢአትን መጨረሻ እንዳናይ የማድረግ ጥበብ አለው

አንድ ጸሀፊ "ሰይጣን፣ የሰው ልጅ በኃጢአት እንዲወድቅ ሲያግባ ልከ እንደ መኪና ሻጭ ወይም ኒጋዴ ነው" አለ። መኪና ነጋዴ ዋና ዓላማው መኪናውን ሸጠ በርከት ያለ ትርፍ ማግኘት እንጂ፣ መኪናውን ከሚሸጥ ለት ሰው ጋር ረጅም ጊዜ የሚቆይ ወዳጅነት ለመፍጠር አይደለም። ሊሸ ጥለት ስላሰበው መኪና፣ ከሆነው በላይ አድንቆና አሳምሮ ከነገረው በኋላ ለእርሱ የሚያበብ ወዳጁ ይመስል "ይህን መኪና የራስህ ማድረግ እንድት ችል ምን ላድርግልህ?" ይለዋል። ገዢውም፣ "መኪናው ጥሩ ነው፤ ወድ ጀዋለሁ። ነገር ግን ቤቴ ሄጀ በጀታችን ይፈቅድ እንደሆነ ከሚስቴ ጋር መነጋገር አለብኝ" ይለዋል። ነጋዴውም፣ "ይሄን መኪና ሳትገዛ ከዚህ ብት ሄድ፣ ተመልሰህ ስትመጣ ልታገኘው እትችልም ይሆናል። የተሰያዩ ሰዎች መጥተው አይተውት ብዙዎቹ በጣም ወደውታልና በኋላ ተመል ሰህ ብትመጣ ላታገኘው ትችላለህ። ገና መጀመሪያ ላይ ሳይህ በጣም ጥሩ ሰው ሆነህ አግኝቼሃለሁና ይህቺ መኪና የእንተ እንድትሆን ማድረግ የምችለውን ሁሉ አደርግልሃለሁ" ይለዋል።

ሰይጣንም ሲያባብለን፣ ልክ እንደዚሁ የአሁኑን እንጂ፣ የወደፊቱን እንድናይ አይፈልግም። ውሳኔ ከመወሰናችን በፊት ረጋ ብለን እንድናስ ብና ሁኔታዎችን እንድናጠና አይፈልግም። በምናደርገው ነገር ሊደርስ ብን ስለሚችለው ጉዳት እንድናስብ አይፈልግም። አንድ ጌታን በጣም የሚወድ ሰው፣ ለሥጋዊ ፍላጎት "እሺ!" ብል ምን ይደርስብኛል? ምን አሆናለሁ? ብሎ ጠየቀ። ለጠየቀው ጥያቄ ራሱ መልስ ሲሰጥ፣ "የቤዛኛንን ጌታ አሳዝናለሁ፤ የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ስም በጭታ አስውሳለሁ። አንድ ቀን በሊየሱስ ፊት ስቀርብ ላደረግሁት ነገር መልስ አሰጣለሁ፤

ተጠያቂ እሆናለሁ። በጣም ጥሩ የሆነችውን የኑሮ ጓደኛዬን፣ ለእኔ ታማኝ የሆነችውን ሚስቴን እጎዳለሁ። በዚህ ምክንያት ከሚስቴ አገኘው የነበረውን ፍቅርና ከብርና መተማመንን አጣለሁ። ልጆቼን እጎዳለሁ። ምሳሌነቴን አጣለሁ፤ ሰዎች በእኔ ላይ እምነት አይኖራቸውም። ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሚስቴንና ልጆቼን ላጣ እችላለሁ። ቤተሰቤን አሳፍራለሁ። እግዚአብሔር ይቅር ቢለኝም ራሴን ይቅር ማለት ያቅተኛና ራሴን መቀበል እቸገራለሁ። የአባለዘር በሽታ ላተርፍ እችላለሁ። ሚስቴ ያልሆነችውን አሰረግዝና ለረጅም ዘመን የማዝንበትና የማለቅስበትን ጸጸት በሕይወቴ አተርፋለሁ። ዕድሜ ልኬን በሀፍረትና በውርደት እኖራለሁ" አለ።

"እመንዝራ እላውቅምI ወደ ፊትም በዚህ ዓይነት ኃጢአት አልወድቅምI በዚህ ትምህርት ላይ ጊዜዬን ለምን አጠፋለሁ? ይሄ ነገር እኔን የሚመለከተኝ ነገር አይደለም" የሚሉ እንዳንድ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በቀጥታም ሆነ በሌላ መልክ እማኝ ይሆን ትዕዛዝ የመጣስ ዝንባሌ ያለው መሆኑን የምንረዳው፣ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ስንሰማ ነው። ኢየሱስ "ኢታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁI ሴትን ተመልክቶ የተመኛት ሁሉ ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር እንዳመነዘረ ይቆጠራል" አለ (የማቴ. 5፥28)።

ለመሆኑ እማኝ "ኢታመንዝር" የሚለውን ሰባተኛውን ትዕዛዝ መጣስ የሚጀምረው እንዴት ይሆን? ጠላታችን ሰይጣን ሰውን በኃጢአት ለመጣል እውነተኛ የሆነው ጦርነት የሚጀምረው ሌላ ሥፍራ ሳይሆን በሰው አዕምሮ ውስጥ ነው። ሰይጣን የመጀመሪያዋን ሴት፣ ሄዋንን ከመሰመር ለማስወጣት ማባበሉን የጀመረው አዕምሯ ውስጥ ነው። እንዳትበላ የተከለከለችው ፍሬ በጣም ውብ ሆኖ እንዲታያት አደረገ። ሰይጣን ይሄ ብልሃቱ የሚፈልገውን ዓይነት ውጤት ሰላስገኘለት፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውን በኃጢአት ለመጣል ፈተናውን የሚያፋፍመው በሰው አዕምሮ ውስጥ ነው። ለሰው የሚያሰብና የሚቆረቁር መስሎ፣ "ይሆንን የመሰለ መልካም ነገር፣ ደስታ የሞላበትን ነገር እጥተህ የምትኖረው እስከ መቼ ነው? ደስተኛ ሆነህ ለመኖር መብትህ ነው" በማለት በጆሮው እውነት መሳይ ውሸት ሹክ ይልበታል። እግዚአብሔርም "ተጠንቀቅ! ቃሌን ጠብቅ! ልት ወሰደው ያበጠከው እርምጃ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍልሃልና ተው! አትንካ!" በማለት፣ ቀደም ሲል እኖ ልንሄድበት ባሰብኸው መንገድ ሄደው የጠፉ፣ ሕይወታቸው የተበላሸባቸው፣ ብዙ የቆሰሉና የደሙ ሰዎች መኖራቸውን

በመጥቀስ ሊያሳስበን ይሞክራል። በፍቅር የተሞላው እግዚአብሔር "አታመንዝር" የሚለውን ሰባተኛውን ትዕዛዝ እንድንጠብቅ እደራ ያለን ራሱን ለመጥቀም ሳይሆን፣ እኛን ከአደጋ ለመጠበቅ እንደሆነ የተረዳነው አንመስልም። በዝሙት ተጠላልፈው የወደቁ፣ በሕይወታቸው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው እማኞች፣ ልባቸውን እንደሚገባው በጥንቃቄ መጠበቅ ያቃታቸው ሰዎች እንደሆኑ ግልጽ ነው።

እማኝ ራሱን ከዝሙት እንዲጠብቅ፣ ለሚቀርብለት ለሰይጣን ፈተና የተጋለጠ እንዳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በቂ የሆነ መመሪያ ተሰጥቶታል። ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ ራሱ ያላገባ ቢሆንም እማኝ በሥጋው ሊፈተንና ሊወድቅ እንደሚችል በመረዳት ሊያደርግ የሚገባውን ምክር ሲሰጥ እናየዋለን። "ስለ ጻፋችሁልኝ ጉዳይ፣ ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው። ነገር ግን ከዝሙት ለመጠበቅ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረውI እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት። ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያድርግላትI ሚስትም እንዲሁ ለባሏ የሚገባውን ሁሉ ታድርግለት። ሚስት አካሏ የራሰሞ ብቻ አይደለምI የባሏም ነውI እንዲሁም ባል አካሉ የራሱ ብቻ አይደለምI የሚስቱም ነው። በጸሎት ለትጋት ተሰማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉI ራሳችሁን ባለ መግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ። ይሆን የምለው ግን እንደ ትእዛዝ ሳይሆን እንደ ምክር ነው" ይላል (1 ቆሮ. 7፥1-6)። እግዚአብሔር የቀደሰውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ረከስ (እንዳልተቀደስ) አድርጎ በመመልከት፣ ወይም አንዱ ሌላውን ለመቅጣትም ሆነ ለመበቀል ሲል የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠውን ምክርና ትእዛዝ ችላ በማለት በሕግ ጋብቻ የተሳሰሩ ቢሆኑም፣ አንዱ የሌላውን መብት ባለመጠበቅ ለዝሙት ፈተና እንዲጋለጥና እጁን እንዲሰጥ ምክንያት የሚሆኑ እሱ። በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ የሚያልፉ ክርስቲያን ባልና ሚስት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም።

እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ

ከሃያ ዓመት በፊት ከአንድ አገር ስሙንና ማንነቱን የማላውቀው አንድ ሰው ደብዳቤ ጽፎልኝ፣ ደብዳቤውንና ለደብዳቤው መልስ፣ እንዲሁም ለሌሎች ትምህርት እንዲሆን በማለት "አትከላከሉ" በሚል እርዕስት

በወቅቱ "አድማስ" በሚለው መጽሔታችን ላይ ያወጣነውን ጽሁፍ ከዚህ ቀጥሎ አቀርብላችኋለሁ። ደብዳቤው ያዘለው ሀሳብ እንዲህ የሚል ነው።

"ይህችን ደብዳቤ ስጽፍላችሁ ማንነቴን ባታውቁትም የትዳር ጎዳናች ቤቴን እየቦረቦረው ከምወደው ጌታ ይለየኛል ብዬ ባላስብም፣ በሕይወቴም ሆነ በባለቤቴ ሕይወት ምሬት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ እንዲሁም ለእገ ልግሎት ያለኝ ፍላጎት እያደር እየቀዘቀዘ እየሄደ የትዝታ ሰዎች ሆንን፣ ጌታን ምን ተአምር ሠርቶ ይጠሽን ይሆን እያልን በተስፋ ደስ በማይል ሁኔታ ተቀምጠናል። "እኔም ሆንኩ ባለቤቴ፣ ጌታንና የጌታን ሕዝቦች እንወዳለን። እርስ በርስ ግን መጣጣም ስለአልቻልን፣ በውይይት ልንፈ ታው ባለመቻላችን ችግሬን ላካፍላችሁ ቆርጬ ጽፌላችኋለሁ። ሌላው ቢቀር በጸሎታችሁ አስቡን።

ይህንን ሳደርግ ባለቤቴን ለመክሰስ አይደለም። ጌታ ችግሬን፣ ልቤን ያውቃል። ግን ያውቃል ለብዙዎቻችን ከእናንተ ከእግዚአብሔር ሰዎች ምክር እናገኝ ይሆናል። በኦርአችን ጌታ ሁሉን አድርጎልናል። በቂ ቤት፣ በቂ ገንዘብ የሚያስፈልገንን አግኝተን እንኖራለን። ትዳር ከመሠረ ትን 6 ዓመት ሆኖናል። ከሁለት ዓመት ወዲህ ግን አንዳንድ ሁኔታዎች በቤታችን መታየት ጀመረ። ባለቤቴ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ፈቃደኛ አይደለችም። እያማትምI በጣም ጤነኛ ነች። የእርሷ ፈቃደኛ አለመሆን እያደር ብለጭት፣ ምሬትና ፈተናን በሕይወቴ እያመጣ ሄደ። ሳትፈልግ በግድ በወር አንድ ጊዜ ብናደርግም፣ ደስ ስለማይላትና ስለ ሚያበሳጫት፣ በውስጤ አንዳንድ ጥያቄዎች መፈጠር ጀመሩ።

"እርሷ ካልፈለገችኝ ምን ዋጋ አለው በማለት አልጋ ለይተን የተለ ያየ ክፍል መተኛት ከጀመርን ይኸው ዓመት አለፈን። ሆኖም እርሷ ደስ ተኛ ነችI በጸሎቷም ትበረታለችI ታገለግላለች። በወገኖቿም የተወደደች ነች። እኔም የጌታ ለም በእኔ ምክንያት እንዳይሰደብ በሞተ ትዳር ውስጥ እመላለሳለሁ። መንፈሳዊ ብሆንም፣ ሥጋና ደም የለበስኩ በመሆኔ እፈ ተናለሁ። በመሆኑም ሥጋዬን ለማድከም ጥዋት ተነስቼ እሮጣለሁ። በዚህ ምክንያት ቤታችን የጸጥታ፣ ወሬና ሳቅ የሌለበት የጸሎት ቤት ሆኗል። ባለቤቴ ጌታን እንደምትወድ ሳረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። በጸሎ ትም ሆነ በምስክርነት የምትሰጠው አገልግሎት ቀላል አይደለም። በዚ

ህም ደስተኛ እንጂ ቅሬታ የለኝም። ለው ኑሮው ሲኦል ከሆነ ክርስትና ውም ትርጉም የለውም ብዬ እምናለሁ። ባለቤቴ በጣም መንፈሳዊ ስለሆነች ምናልባት ይሄ የማይረባ የሥጋ ሀሳብ ብላ ተቀብላው ይሆን? ምክር ካላችሁ በአድማስም ሆነ በሄዋን መጽሔት ለመስማት እጠብቃ ለሁI ስም የለኝም" ይላል።

ይህ ደብዳቤ ከተጻፈልኝ ሃያ ዓመት ያለፈው ሲሆን፣ በወቅቱ እውነተ ኛውን ማንነታቸውን ገልጸው ስላልጻፉልኝ፣ ዛሬ ከ26 ዓመት በኋላ ያሉ በት የጋብቻ ሕይወት ከምን ዓይነት ደረጃ ላይ እንዳለ ልነግራችሁ አልች ልም። ከዚህ በላይ የለማችሁት ደብዳቤ የጋብቻ ሕይወቱ የጨለመበት፣ ወደ ፊትም ከዚህ የከፋ ነገር ይደርስብኝ ይሆናል የሚል ፍርሃት ካደረበት ክርስቲያን ወንድም የተጻፈ ነው። ብዙዎች እንደዚህ ሰው "በትዳሬ ውስጥ ችግር አለብኝ" ብለው በድፍረት አይጻፉ እንጂ፣ ይህን የመሰለ ተመሳሳይ ችግር ብዙዎች እንዳለባቸው አንጠራጠርም። የሥነ ምክር አገልግሎት ምሁራን በትዳር ዓለም ላይ ከሚያጋጥሙት ችግሮች መካከል 70%፣ 80% በግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም ምክንያት እንደሆነ ይናገ ራሉ። ይሄን ዓይነቱ ችግር በዓለማውያን ዘንድ ብቻ ሳይሆን በክርስቲያ ኖችም ላይ የሚታይ በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ አሳብ መስጠቱ ጠቃሚ ይመስለናል። የግብረ ሥጋ ግንኙነት እምቢ መባል ወይም መከል ከል የለለቸው አንድ ሰው አንድ ጊዜ በቀልድ መልክ ከዚህ በታች ያለውን ደብዳቤ ለሚሉቱ ጻፈላት።

"የተወደድሽው ውዴ ባለቤቴ፣ ባለፈው ዓመት ከአንቺ ከውድ ባለቤቴ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ፈልጌ 365 ጊዜ ጥያቄ አቅርቤልሽ ነበር። ይግረምሽና "እሺ!" ብለሽ የፈቀድሽልኝ 36 ጊዜ ብቻ ነው። "እምቢ!" ያልሽባቸውን ምክንያቶችሽን ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ዘር ዝሬያቸዋለሁ።

23 ጊዜ በጣም መሽቷል አልሽኝ።

27 ጊዜ ልጆቼ ይነሳሉ አልሽኝ።

15 ጊዜ ጉና አልመሽም አልሽኝ። 16 ጊዜ በጣም ሞቆኛል አልሽኝ።

5 ጊዜ በጣም በርዶኛል አልሽኝ።

47 ጊዜ እንቅልፍ እንደያዘሽ አስመስለሽ እምቢ አልሽኝ።

10 ጊዜ ጎረቤት ይሰማል አልሽኝ።

27 ጊዜ ወሬን አሞኛል አልሽኝ።

14 ጊዜ ጥርሴን አሞኛል ብለሽ አምቢ አልሽኝ።

18 ጊዜ ራሴን አሞኛል አልሽኝ።

6 ጊዜ አየሳቅሽ፥ ሳቂ አስቸግሮኛል ብለሽ እምቢ አልሽኝ።

36 ጊዜ ጥሩ ስሜት ላይ አይደለሁም አልሽኝ።

10 ጊዜ ሆዴ ሙሉ ነው (በጣም ጠግቤአለሁ) በማለት እምቢ አልሽኝ።

17 ጊዜ ልጁ ያለቅሳል አልሽኝ።

17 ጊዜ ቴሌቪዥን ስለማይ አልችልም አልሽኝ።

11 ጊዜ እኔን በመንቀፍ አምቢ አልሽኝ፥ አሁንም

11 ጊዜ አንግዳ አለ በማለት አምቢ አልሽኝ።

19 ጊዜ መጸዳጃ ቤት መሄድ አለብኝ አልሽኝ። በጠቅላላው 329 ጊዜ አምቢ አልሽኝ።

"የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንድንፈጽም በፈቀድሽልኝ ጊዜም ይህን ያህል ሙሉ ደስታን (እርካታን) አላገኘሁም። ምክንያቱም፥

6 ጊዜ ማስቲካ ታኝኪ ነበር።

7 ጊዜ ቴሌቪዥን አያየሽ ነበር።

16 ጊዜ 'ቶሎ ጨርሰና አባክህን ተነሳ' አልሽኝ።

6 ጊዜ አንቅልፍ ወሰደሽ።

1 ጊዜ ስሜት ኖሮሽ በመንቀሳቀሽ የጎዳሁሽ ስለ መሰለኝ ደነገጥኩ። ውይ ባለቤቴ፣ ታዲያ ብዙ ጊዜ አምሽቼ መምጣቴ፣ ስከሬ ወደ ቤቴ መግባቴ ይህን ያህል ሊደንቅሽ አይገባም" አላት።

ከዚህ በላይ የሰማነው አንዲት ሚስት ከባሏ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆኗ የሰጠቻቸው ምክንያቶች ናቸው። ምክንያቶቹ በቀልድ መልክ የቀረቡ ይሁኑ እንጂ፣ ብዙዎቹ እውነተኛነት ያላቸውና በብዙዎች ዘንድ የሚስሙ ምክንያቶች ናቸው። በተቀደሰ ጋብቻ በተሳሰሩ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈቀደው ልጆች ለመውለድ ብቻ ሳይሆን፣ ባልና ሚስት ልዩ የሆነ ደስታና እርካታ እንዲያገኙበት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ታላቅ ስጦታ እንደሆነ የታወቀ ነው።

የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሁለት ሰዎች የመንፈስ አንድነት፣ የአንድ አካል (ሥጋ) የመሆን መግለጫና ማረጋገጫ ነው። በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ይሄን ዓይነቱ ግንኙነት ከጎደለው፣ የባልና የሚስት ጎብረትና አንድነት ይቀጭጫል። መጽሐፍ ቅዱስ "አዳም ሄዋንን አወቃትI አርሷም ጸነሰች" ሲል፣ በሁለቱ መካከል ፍጹም የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ነበረ መረዳት አያዳግትም። ይህን ዓይነቱ ግንኙነት በጋብቻ በኩል የሚገኘውን አንድነት ይገልጻል። በዚህም አንዱ የራሱን ሥጋ (አካል) ለሌላው ገልጠ ይሰጣል ማለት ነው። ጳውሎስ ራሱ ያላገባ ቢሆንም ይህን ስለ መሰለው ችግር ላገቡ ሰዎች ጠቃሚ የሆነ ምክር ይሰጣል። *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላትI እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ። ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም። ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፥ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውምI ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ባልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉI ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ"* ይላል (1 ቆሮ. 7፥3-5)።

ጳውሎስ ባልና ሚስት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚርቁበት ጊዜ ቢኖር ሁለቱ ተስማምተው በጸሎት ለመትጋት በሚፈልጉበት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል። ያም ቢሆን፣ ለረጅም ጊዜ ሳይሆን ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። በሥጋቸው ላይ ሥልጣኑ የሌላው እንጂ የራሳቸው እንዳልሆነ ጨምሮ ይጠቅሳል። ስለሆነም፣ "ሥጋዬን ለኑሮ ጓደኛዬ አልሰጥም" ለማለት ማንኛቸውም መብት ወይም ሥልጣን የላቸውም። ስለሆነም፣ አንዱ ሌላውን የሚቀጣበት መሣሪያ ሊያደርገው አይገባም። በጋብቻ ውስጥ ያሉ ሁለት ሰዎች አንድነታቸውን የሚገልጹበት የግብረ ሥጋ ግንኙነት አንዲሆን አግዚአብሔር ከፈቀደ፣ ለምን ብዙ ሰዎች የዚህ ችግር ያጋጥማቸዋል? "እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ቢያውቁም፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች በግብረ ሥጋ ግንኙነት አንደሚገባው የማይቀራረቡበት ምክንያት ምን ይሆን? ከተነሳንበት ዓላማ ውጪ ያደርገናል እንጂ፣ ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶችን መስጠት እንችል ነበር።

ማመንዘር ምንድነው?

ማመንዘር በጋብቻ ውስጥ እምነት ማጉደል ወይም ታማኝ አለመሆን ነው። ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት የጋብቻን ቃል ኪዳን ያፈርሳል። ስለዚህ እግዚአብሔር "አታመንዝር" የሚለውን ትዕዛዝ የሰጠበት ዋና ምክንያት ጋብቻን ለመጠበቅ ወይም ከችግር ለመከላከል ሲል ነው። ዝሙት፣ በባልና በሚስት መካከል ያለውን እምነት የሚተላለፍ በመሆኑ፣ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት ነው። ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ ባልና ሚስት በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት የገቡትን ቃል ኪዳን መስበራቸው ነው። ለዚህ ነው በብሉይ ኪዳን ዘመን ከጋብቻ ውጪ ዝሙት የሚፈጽሙ ሰዎች ከፍ ተኛ ቅጣት እንዲደርስባቸው ይደረግ የነበረው። *"አንድ ሰው አስራኤላዊ ከሆነ ወንኑ ሚስት ጋር ቢያመነዝር አመንዝራውና አመንዝራይቱ ሁለቱም በሞት ይቀጡI አንድ ሰው የአባቱ ሚስት ከሆነችው ከማንኛዋም ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም፣ አርሱና ሴትየዋ ሁለቱም በሞት ይቀጡI በሞት የሚቀጡትም በራሳቸው በደል ነው"* ይላል (ዘሌዋ. 20፥10-11)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ዝሙት የሚፈጽሙ ሰዎች በሞት እንዲቀጡ የተወሰነበት ምክንያት ምን ይሆን? ለሚስቱ ወይም ለባሏ ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች፣ ለሌላውም ታማኝ ስለማይሆኑ ነውI ዝሙት ቤተሰብና እግዚአ ብሔርን መክዳት ስለሆነ ነው የሚሉ አሉ።

ዝሙት፣ ሥጋዊ ግንኙነት መፈጸም ብቻ አይደለም። "አታመንዝር" የሚለው ሰባተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለው ወደ ዝሙት የሚመራውን ነገር ሁሉ ነው። ማንኛውም ዝሙት የሚጀምረው በግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይ ሆን፣ ተገቢ ባልሆነ የተቀራረበ ግንኙነት ነው። ሰባተኛው ትዕዛዝ አንድ ያገባ ሰው ሚስቱ ያልሆነችዋን ሴት ማሽኮርመም እንደሌለበት ያዛል። እንዲሁም አንድ ያላገባ ወንድ፣ ሚስቱ ካልሆነችው ሴት ጋር በጣም የተ ቀራረበ ግንኙነት እንዲኖረው አይፈቅድም። ራሱንም ሆነ ሌላውን ከፈ ተና ለመጠበቅ በመከለላቸው የተወሰነ ርቀት ሊኖር ይገባል። እንዲሁም እንድ ባል ያላት ሴት፣ መሥሪያ ቤትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌላ ውን ወንድ የሰሚታ ድጋፍ ከመፈለግ የተቆጠበች መሆን እንዳለባት ሰባተ ኛው ትዕዛዝ ከመጣስ ይጠብቃል። ሰባተኛውን ትዕዛዝ በአምንታዊ መልክ ለማቅረብ፣ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ያለውን ፍቅር፣ ውስጣዊ ስሜታ

ቸውን፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውንና እንዲሁም፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ያላቸውን ፍላጎት ማጎልበት አለባቸው። ሰው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ብቻ እይደለም ሰባተኛውን ትዕዛዝ የሚያፈርስው። "እታመን ዝር" ማለት "ዝሙት እትፈጽም" ከሚለው አባብ ጋር እንድ ዓይነት ይሆን? በእግርኛ ቋንቋችን አንድ ዓይነት ይምስል እንጂ ዝሙት መፈጸም የሚ ለው ቃል በእንግሊዝኛ "ፎርኒኬሽን" ሲሆን፣ ይሄም እንድ ያገባ ሰው ካላገ ባት ሴት ጋር ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽም ነው።

ለመጋባት ተፈቃቅደው የተጫጩ ወንድና ሴት፥ ከጋብቻቸው በፊት እርስ በርሳቸው ያላቸው መቀራረብ ወሰኑ እስከምን ድረስ ይሆን? መጽ ሐፍ ቅዱስ ግልጽ የሆነ መስመር አስምሮ "እስከዚህ ድረስ ነው" ብሎ እይነ ግረንም። ሁለት ወጣቶች ከመጋባታቸው በፊት በየትኛውም መልክ በሥጋ የተቀራረበ ግንኙነት ማድረግ ሰባተኛውን ትዕዛዝ እንዲጥሱ ይገፋፋል። "እስከ ምን ድረስ መቀራረብ እንችላለን?" ብለው ከመጠየቅ ይልቅ፣ በእግ ዚአብሔርና በእግዚአብሔር ፊት በቃል ኪዳን እስከንተሳሰር ድረስ በንጽ ህና ለመቆየት ራሳችንን ከፈተና መጠበቅ እንዴት እንችላለን? ብለው መጠየቅ የተሻለ ነው። ክርስቲያኖች የተጠራነው ቅዱሳን እንድንሆን ነው። በየትኛውም መልክ ይሁን ሰባተኛው ትዕዛዝ፣ ዝሙትን ይከለከ ላል። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተከለከለው፣ ከጋብቻ ክልል ውጪ እንጂ፣ በጋብቻ ውስጥ ላሉት ወንድና ሴት እይደለም። የተከለከለ የሆነበት ከላይ በሰጠነው ምክንያት እንጂ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጥፎ በመሆኑ እንዳ ልሆነ የታወቀ ነው።

በእንድ ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳንድ ወጣት ክርስቲያኖችን ከትላለቅ ኩተሞች፣ ይኸውም ከቆሮንቶስና ከኤፌሶን ከተማ ሲመጡ አገ ኛቸው። እነዚህ ኩተሞች ውስጥ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚገፋፉ ፈታኝ የሆኑ መጥፎ ሁኔታዎች ስለነበሩ፣ እንዳንዶቹ በእጠቃላይ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ሲያወግዙና በጋብቻ ውስጥ የሚሆነውንም ግንኙነት ትክክል እንዳልሆነ አድርገው በማመን ጋብቻን እየተቃወሙ ይሰብኩ ነበር። ጳው ሎስ ይህን ሁኔታ ዓይቶ ዝም ብሎ ማለፍ ስላልፈለገ በዚህ ነጥብ ላይ ለማስ ተማር ተነሳ።

"እንዳንዶች ጋብቻን ይከለክላሉ..." በማለት፣ ጋብቻ መልካም እንደ ሆነና በእርሱ የተመሠረተ መሆኑን፣ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ በእግባቡ ከተደረገ ምንም የሚጣል ነገር እንደሌለበት በመግለጽ ያስተ

ምር ነበር። ቀደም ሲል እንደገለጽነው የሰባተኛው ትዕዛዝ ዋና ዓላማ በጋብቻ ውስጥ ያለውን የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ለመጠበቅ (ለመከላከል) ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዓላማ በትክክለኛው ጋብቻ ውስጥ ሰዎችን የበለጠ ለማቀራረብ ነው። ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን መፈጸም ጥሩ ውን ወይም መልካም የሆነውን ነገር በተሳሳተ መንገድ መጠቀም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻንም ሆነ፣ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸመውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት አይቃወምም። *"ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይክበር፤ መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል"* ይላል (ዕብ. 13፥4)።

ጋብቻን ልዩ የሚያደርገው በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። ኮማንኛውም ነገር የበለጠ ጋብቻ ቃል ኪዳን ነው። ቃል ኪዳንም ሁለቱንም ወገን በተስማሙበት ነገር ተጠያቂ የሚያደርግ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከማንኛውም ነገር የሚበልጠው፣ እግዚአብሔር ሰራሱ ሕዝብ የሰጠው በፍቅር የተሞላ ስምምነት ወይም ቃል ኪዳን ነው። በእዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን በተለያየ ሥፍር እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን፣ በባልና በሚስት መካከል በጋብቻ ሲተሳሰሩ የሚኖራቸውን ስምምነት ጋር አያይዞ ይናገራል። *"...እንደምወድሽ ቃል ገባሁልሽ፤ ከአንቺም ጋር የጋብቻ ቃል ኪዳን ገባሽ የእኔ የግሌ አደረ ሸሁሽ"* ይሆን የተናገረ ልውል እግዚአብሔር ነው" ይላል (ሕዝ. 16፥8)። ይህንኑ አሳብ በመያዝ ጳውሎስ *"ባሎች ሆይ! ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደና ራሱን ስለ እርስዋ አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ"* ይላል (ኤፌ. 5፥25)። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ፍቅር፣ በጋብቻ ላይ ያለውን ዓይነት ፍቅር እንደሆነ ይገልጻል። በጋብቻ የተሳሰሩ ክርስቲያን ባልና ሚስት፣ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ባለው ዓይነት ፍቅር መፋቀር አለባቸው።

ዝሙት ክፉ (መጥፎ) ነው

ዝሙት ክፉ ስለሆነ ነው ስባተኛውን ትዕዛዝ በግልጽ "አታመንዝር" ያለው። ክፉ የሆነበት አንደኛው ምክንያት የጋብቻን ቃል ኪዳን የሚያፈርስ በመሆኑ ነው። ባልና ሚስት ጋብቻቸው እንዳይጸና ከሚያደርጉት ከማንኛቸውም ዓይነት ስህተቶች የበለጠ ዝሙት የከፋ ነው። የከፋ የሆነ

በት አንደኛው ምክንያት፣ ለሌላው ወገን ያለውን ታማኝነት የሚያፈርስ በመሆኑ ነው። በዚህ ምክንያት የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አለው። ብዙዎች "ጋብቻ፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ እይደለም" ይላሉ። እርግጥ ነው በጋብቻ ሕይወት ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ ስፍራ ቢኖረውም፣ በዝሙት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈርስ እንደሚችል የታወቀ ነው። እግዚአብሔር በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ያለውን የጋብቻ እንድነት ሲገልጽ፣ *"ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበረው ስለዚህ ነው፤ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ"* አለ (ዘፍ. 2፥24)። ይኸው አሳብ፣ ማቴ. 19፥5 ላይ በተመሰላይ ሁኔታ ተገልጸ እናያለን። የጋብቻ ቃል ኪዳንን የሚያትመው (የሚያጸድቀው) አንድ አካል በመሆን ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ነው። አንድ አካል መሆንን፣ በአንድ ጊዜ ተፈጽሞ የሚያልቅ ሳይሆን ሂደት ነው። በሁለቱም ወገን ያሉት ሰዎች ለሌላው ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ መስጠት አለባቸው። አሳብን፣ ስሜትን ለሌላው ማካፈልን ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነቱ ነገር እያደገ የሚሄድ እንጂ በአንድ ጊዜ ተፈጽሞ አያልቅም።

ይሄ አንድ የመሆን ሂደት አስደናቂ የሚሆነው፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ ነው። እንድ ሰው ከሚወደው ሰው ጋር ራቁቱን ሲተኛ፣ ራሱን፣ ፍላጎቱንና ስሜቱን ገላልጦ ለሌላው ማሳየቱና መስጠቱ ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት የራሱ ቋንቋ አለው። በግብረ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ ያሉ ወንድና ሴት፣ በአካላቸው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የተለያየ ስሜታቸውን ይገልጻሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሰው በእካሉ ለሌላው ስሜቱን የሚገልጽበት ቋንቋ ነው። በእንግሊዝኛ "ቦዲ ላንጉጂ" ይሉታል። "በምድር ያለኝን ዕድሜዬን ሙሉ ለአንተ/ለአንቺ የተሰጠሁ ነኝ፤ በአንድነት የተካፈልነው ነገር፣ ለአንተ/ለአንቺ እንጂ፣ ለሌላው ሰው የምሰጠው ወይም የማካፍለው አይደለም" ማለታቸው ነው። ከዚህ ውጪ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ትክክል እንዳልሆነ ለመግለጽ ነው ሰባተኛው ትዕዛዝ ላይ "አታመንዝር" ያለው። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት ልክ እንደ መብላት ፍላጎት ነው የሚሉ እንዳንድ ሰዎች ጳውሎስን አጋጥመውት ነበር። በእነርሱ አባባል፣ ሁለት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት የራባቸው ወንድና ሴት፣ ለሚታቸው ሲቀለቀስ የሚፈጽሙት ተግባር እድርገው

የሚያዩ ነበሩ። ጳውሎስ በዚህ ነጥብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጠቃሚ ትምህርት ሲሰጥ፣ *"ሰውነታችሁ የክርስቶስ አካል ክፍል መሆኑን ታውቁ የለምን? ታዲያ የክርስቶስን አካል ክፍል ወስጄ የአመንዝራ ሴት አካል ክፍል እንዲሆን ላደርገው ይገባልን? ከቶ አይገባም! ከአመንዝራ ሴት ጋር በግብረ ሥጋ የሚተባበር ሰው ከእርሱዋ ጋር አንድ አካል መሆኑን ታውቁ የለምን? ምክን ያቱም ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ' ተብሎ ተጽፏል"* አለ (1 ቆሮ. 6፥ 15-16)።

በወንድና በሴት መካከል የሚፈጸመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሥጋ ቸው የሚገልጹት ቋንቋ (በዲ ላንጉጂ) ከሆነ፣ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ሰዎች መዋሸታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው። "አንድ አካል" ላይሆኑ፣ አንድ አካል ነን ማለታቸው ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ በእስራኤላውያን ባህል ለወንድና ለሴት እኩል የሆነ አመለካከት አልነበረም። ሴት ከባሏ ውጪ ከማንኛውም ወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግን ኙነት ብትፈጽም እንደ አመንዝራ ትቆጠራለች። ወንዱ ግን ባል ካላት ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም፣ በደል የሠራው በሌላው ወንድ ላይ ብቻ እንደሆነ ነው። ከዝሙት እዳሪ ጋር ወይም ባል ከሌላት ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም ግን እንዳመነዘረ አይቆጠርም ነበር። በእ ሥራኤል በሴትና በወንድ መካከል የነበረው አድልዎ ዋናው ምክንያት የቤተሰብን የደም ዝርያ እንዳይቀየጥ (እንዳይበረዝ) ለማድረግ ነበር።

ዝሙትን ኢየሱስ ሰፋ አድርጎ ያሳየናል

ኢየሱስ ሲመጣ ዝሙትን በሚመለከት አሳብ ላይ በወንድና በሴት መካከል፣ እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን አድሎ እላሳየም። ኢየሱስ ዝሙትን ሰፋ አድርጎ ሲገልጽ እናያለን። *"ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ 'አታመን ዝር' እንደተባለ ሰምታችኋል፤ ሴትን ተመልክቶ የተመኛት ሁሉ ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር እንዳመነዘረ ይቆጠራል"* አለ (የማቴ. 5፥27-28)። እዚህ ላይ "ዝሙትን" በሁለት አቅጣጫ ሰፋ አድርጎ ያሳያል፥

1) ሰው በአሳቡ ወይም በአዕምሮው የሚፈጽመው ዝሙት ነው። "ሴትን ተመልክቶ የተመኛት ያመነዝራል" ይላል። እዚህ ላይ መፈተን ኃጢአት ነው ማለቱ አይደለም። ኃጢአት እይሥራ እንጂ፣ ፍጹም ሰው የሆነው ኢየሱስ ከርስቶስም ተፈትኗል (ዕብ. 4፥15)። መፈተንና ለፈተና መሸነፍ

ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። ክርስቲያን ራሱን ወደ ፈተና ላለመክተት ዐይኖ ቹን መጠበቅ አለበት። ኢዮብ ራሱን ከፈተና ለመጠበቅ *"ቆንጆይቱን በፍ ትወት ዐይን እንዳልመለከት ቃል ኪዳን አድርጋለሁ"* አለ (ኢዮብ 31፥1)።

2) ኢየሱስ ዝሙትን ሰፋ እድርጎ ሲያቀርብ ሁለተኛው የገለጸው አሳብ እግብቶ መፍታት ትክክል አለመሆኑን ነው። *"ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ በሚስቱ ላይ አመንዝሮአል ማለት ነው። እንዲሁም ባልዋን ፈትታ ሌላ ወንድ የምታገባ ሴት አመንዝራ ሆናለች ማለት ነው"* አለ (የማር. 10፥ 11-12)። ይሄ ሁኔታ ያስደነገጣቸው ደቀ መዛሙርቱ *"ባልና የሚስት ሁኔታ እንዲህ ከሆነ አለማግባት የተሻለ ነው አሉ"* (የማቴ. 19፥10)። ደቀ መዛሙርቱ የተረዱት የጋብቻ ቃል ኪዳን ምን ያህል ጥብቅ እንደሆነና መሰበር እንደሌለበት ብቻ ሳይሆን፣ በሴትና በወንድ መካከል የነበረው ንም ልዩነትና እድልዎ የደመሰሰው መሆኑ ነው። ማቴዎስ የኢየሱስን አሳብ ሰፋ አድርጎ ሲያቀርበው እናያለን። *"ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ እንዲሁም ሚስ ቱን የሚፈታ ሁሉ የተፈታችበትን ምክንያት የሚገልጽ ጽህፍ ይስጣት' ተብሎአል። እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ፤ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ምክንያት ይሆንባታል። የተፈታች ውንም የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል"* ይላል አለ (የማቴ. 5፥31-32)። አሥርቱ ትዕዛዛት ላይ የምናየው አርዕስተ ዜና ብቻ ስለሆነ፣ ሰው ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ግልጽ የሆነ የበለጠ መረዳት አንዲኖረው ሰፋ አድርጎ አቅ ርቦታል። ዝሙት ወይም ማመንዘር ክፉ የሆነው፣ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መጥፎ በመሆኑ ላይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ የደነገገውን የጋብቻን መሠ ረት የሚያናጋ በመሆኑ ነው። የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በምንም ዓይነት ምክንያት መፍረስ የሌለበትን ጋብቻ፣ በወንድና በሴት መካከል የተመሠ ረተውን እንድነት የሚያጸና ነው። ከዚህ ውጭ የሚደረግ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነው። ዛሬ የአማኞች የት ድስና ሕይወት፣ የሞራል አቋም ምን ይመስል ይሆን?

በሰለጠነው ዓለም የምንኖር ሰዎች በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ታዋ ቂነት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች መጥፎ ድርጊት እንደፈጸሙ በየቀኑ መስ ማትን ስለተለማምድነው ምንም አይመስለንም። ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ የታወቁ መንፈሳዊ ድርጅቶችንና አብያተ ክርስቲያናትን የሚመሩ ታላላቅ ሰዎች የሞራል ድካማቸውን ስንሰማ የሚሰማን ስሜት፣ የምንጠይቀው ጥያቄ አለ። "በኃጢአት ወደቁ" በተባሉት ላይ ከመፍረድ ይልቅ "ጠንቃቃ፣

በቅድስና ሕይወቱን የሚመራ ሰው ነው" የተባለለት፣ ይህን የመሰለ ኃጢአት ከፈጸመ እንግዲያውስ ማን በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጸንቶ መቆም ይችላል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

የዝሙት ፈተና ማንንም አይመርጥም። ያገባ፣ ያላገባ፣ ወጣት፣ ሽማግሌ፣ የቆየ ክርስቲያን፣ አዲስ ክርስቲያን እይልም። ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች በሥጋ ፈተና ሲወድቁ እያየን፣ ከእኛ መካከል "እኔ በዚህ ፈተና አልሰናከልም ወይም አልወድቅም" ብሎ መናገር የሚችል ሰው ይኖራል ብለን አናምንም። ለዚህ ነው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች "ቆሜአለሁ የሚል እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ" በማለት የመከራቸው (1 ቆሮ. 10፥12)። ከጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። አሜሪካ ውስጥ በአንድ ሳምንት ውስጥ 35 ሚሊዮን አሜሪካኖች ከጋብቻቸው ውጪ በየመሥሪያ ቤታቸው የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሚፈጽሙ ታውቋል። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በዚህ እቅጣጫ ድካም ያለባቸው መስሎ እይታየንም ነበር። አዕምሯችን መቀበል ያቅተው እንጂ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መካከልም ዝሙት በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ እየበዛ መጥቷል። ዝሙት የድብቅ ኃጢአት ስለሆነ፣ በአደባባይ በግልጽ አይታይ እንጂ፣ የዝሙት ድካም በኢትዮጵያውያን መካከል የለም ማለት አይደለም።

ዝሙት በሰዎች ልጆች ላይ ውርደትን፣ በሽታን፣ ሞትን ያመጣል። ለሰዎች ጥቂትና ጊዜያዊ ደስታ ይሰጥና ያላቸውን መልካም ነገር እውድሞና ሰባብሮ ለወደፊት የሚሆናቸው ምንም ነገር ሳይተውላቸው ባዶ እጃቸውን ያስቀራቸዋል። ጀርመናዊው የሥነ መለኮት ሊቅ የነበረው ዲትሪክ ባንሆፈር ስለ ፍትወት ሲጽፍ፥

> "...በሁላችንም ሕይወት ውስጥ የተኛ የሚመስል ኃይለኛ የሆነ ለፍትወት ፈተና የመሸነፍ ዝንባሌ አለን። ማንም ተቆጣጥሮ ሊያቆመው ወይም ሊገታው በማይችል ኃይል ሥጋን ጨምድዶ ይይዛል። ፍጹም የማይታይ ይሁን እንጂ፣ ሲቀሰቀስ እንደሚዝገበገብ እሳት በኃይል ይነዳል" አለ።

በጦርነት ምክንያት ካለቁት ሰዎች ቁጥር ይበልጥ በሥጋ ፍትወት ምክንያት ያለቁት ሰዎች ይበልጣሉ። የመሬት መንቀጥቀጥና ጎርፍ፣ እንደዚሁም ኃይለኛ ንፋስ ካፈረሳቸው ቤቶች ይልቅ በሥጋ ፍትወት ምክን

ያት የፈረሱት ቤቶች እንደሚበልጡ ምሁራን ይናገራሉ። እግዚአብሔር "አታመንዝር" የሚለውን ሰባተኛውን ትዕዛዝ ለሰው የሰጠው ይህን ዓይነት ጥፋት በሕይወቱ እንዳይደርስበት ስለፈለገ ነው። እኔና እናንተ የሥጋ ፈተና ፈጽሞ እንዳይደርስብን የምናደርግበት አቅምም ሆነ ችሎታ የለንም። ሰይጣን በፈለገበት ጊዜና ቦታ ስፈለገው መንገድ ሊፈትነን ይችላል። እኛ የፈተናውን ዓይነትና ሁኔታ መምረጥ አንችልም። ሰይጣን ኃይለኛ ነው። እኛን ለመጣል በተለያየ አቅጣጫ ያለማቋረጥ ይጥራል። ይሁን እንጂ፣ ለሥጋ ፈተና "እምቢ!" ለማለት የሚያስችለን በውስጣችን ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ልዩ ኃይል ስላለን እንጠቀምበት።

Join our official telegram Channel for more
@AmharicSpritualBooks